

# በኢትዮጵያ ለሰላም ግንባታ አስተዋጽኦ ያላቸው ማኅበረ-ባህላዊ ዕሴቶችና ተቋማት ፋይዳዊ ምደባ


የሰላም ሚኒስቴር
MINISTRY OF PEACE

Sweden
Sverige

Life & Peace
INSTITUTE

የሰላም ሚኒስቴር
MINISTRY OF PEACE

Sweden
Sverige

Life & Peace
INSTITUTE

# በኢትዮጵያ ለሰላም ግንባታ አስተዋጽኦ ያላቸው ማኅበረ-ባህላዊ ዕሴቶችና ተቋማት ፋይዳዊ ምደባ

ነሐሴ 2014 ዓ.ም

## ማውጫ


| | |
|---|---|
| ምስጋና | 7 |
| መቅድም 1 | 7 |
| መቅድም 2 | 8 |
| የአጥኚዎቹ ማስታወሻ | 9 |
| መግቢያ | 10 |
| ማኅበራዊ ሀብቶች እንደ የሰላም መሠረተ-ልማት (Social Capital as Infrastructure of Peace) | 10 |
| የመረጃ አመዳደብና አደረጃጀት | 11 |
| ክፍል አንድ | 12 |
| ማኅበራዊ ትስስርና ተግባቦትን የሚያጠናክሩ ሥርዓቶችና ተቋማት | 12 |
| መግቢያ | 13 |
| ገዳ | 13 |
| የጌዴኦ የገዳ ሥርዓት | 13 |
| ሲንቄ | 14 |
| ጉዲፈቻ | 14 |
| ሞጋሳ | 14 |
| ቀነፋ | 14 |
| የጽዋ ማኅበር | 15 |
| ሰንበቴ | 15 |
| የክርስትና ልጅ/አባት | 15 |
| እድር | 16 |
| እቁብ | 16 |
| የንሥሐ አባት | 16 |
| የፈረስ አባት/ፈሪሴ ታበላ | 17 |
| የላም ራስ | 17 |
| የውሃ አባት (አኹታብላ) | 17 |
| ሃላሌ | 18 |
| ያካ | 18 |
| ሉዋ | 18 |
| ፊቼ ጫምባላላ | 18 |
| ካማኬሳ | 19 |
| አፊኒ | 19 |
| መድኣ | 19 |
| ዳጉ | 19 |
| አዳኘ የባሊ ቅናት ሴራ | 20 |
| መግቢያ | 22 |
| ሽምግልና | 22 |
| ዘወልድ፤ ሰንየሰገድ፤ ክፍሎ፤ መዘርድ | 22 |
| አቢጋር | 23 |
| እሩፎ መረባ | 23 |
| አባሀጋ፣ አባጋር፣ ሶራ አባ ኦርማ | 24 |
| አሬቅስጊእና መኸይ | 24 |
| የላም ራስ | 25 |
| ሽመርነይ/መርካባ | 25 |
| እውስ (አፈርሳታ፣አውጫጪኝ) | 25 |
| ገዳ | 26 |
| ጃርሱማ/ጃርሳቢያ | 26 |
| ሲንቄ | 26 |
| ጉማ | 26 |
| ጎንዶሮ | 27 |
| አዳ ያኢ ቢያ | 27 |
| ጃርሱማ/መንጉዶ | 28 |
| ሔር | 28 |
| ጌድፈዲሲ/ጌድሆስቲ | 29 |
| ሔራ | 29 |
| ትምባ | 30 |
| ጣሂኒዓያ | 31 |

| | |
|---|---|
| ኔሞ | 32 |
| አሾራ/አልቡራ | 33 |
| ሹምቡ | 33 |
| ሳንጋኔና | 35 |
| ደመርግራ-ገረቦ | 35 |
| ገረብ | 35 |
| ባይቶ | 36 |
| መድኣ | 36 |
| ማሮ | 36 |
| አፊኒ | 36 |
| ጉዱማሌ | 37 |
| ሀላሌ | 37 |
| ያካ | 37 |
| ሉዋ | 38 |
| ደረ-ዱለታ/ደረ-ዎጋ | 38 |
| ውርሳ | 38 |
| ኧታኧላቴ | 38 |
| ኼልታ | 39 |
| ሆቀተ | 39 |
| ሴራ | 40 |
| ገትሴራ | 40 |
| ቢታንቴ | 40 |
| ጎሜ | 40 |
| ጪማታነሊግነሶዎጋ | 41 |
| ጪማና አሊሶ ዎጋ | 41 |
| ግዲቾ ዎጋርሲ ጎንዶሮ | 41 |
| ዴሃእናቅማዩማ (ቅሙማ) | 42 |
| ጭሙንታንታ ሴራ | 42 |
| ቦኮ | 42 |
| ሻቲኒሳዛባ | 43 |
| ዎራፎ | 44 |
| ኦቶ | 44 |
| ቂሽ | 44 |
| ማገኖ | 45 |
| ኳር ሙን (Kuaar Muon) | 45 |
| መግቢያ | 47 |
| ሚቹ | 47 |
| ሆርማ ሆዳ | 47 |
| ገረብ | 47 |
| ጉርቲ | 48 |
| ጉዲፈቻ | 48 |
| ሞጋሳ | 48 |
| ጎንዶሮ | 48 |
| አዳያኢቢያ | 49 |
| ሔር | 49 |
| ሔር ዲብሌ (Xeer Dhiblee) | 49 |
| ማሮ | 50 |
| ፈእይማ | 50 |
| ከታይዛ | 50 |
| ሉዋ | 50 |
| ገትሴራ | 50 |
| ግዲቾ ዎጋርሲ ጎንዶሮ | 51 |
| ዴሃ እና ቅማዩማ (ቅሙማ) | 51 |
| ቦኮ | 51 |
| ምርቃትና ጸሎት | 52 |

# ምስጋና

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና በክልል ባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች የተሰበሰቡ ማኅበራዊ ሀብቶችን በአንድ ጥራዝ ለመሰነድና ጥቅም ላይ ለማዋል ይቻል ዘንድ ተጨማሪ የማዳበር፣ ግብአት የማሰባሰብና የድርሳናት ማጣቀሻ በማስፈልጉ ኤል.ፒ.አይ (LPI) በዘርፉ ከሚሰሩ ምሁራን ጋር በመተባበር ሥራውን እዚህ ምዕራፍ ላይ እንዲደርስ የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ ስለሆነም ይህ ሥራ ዕውን እንዲሆን በገንዘብና በሙያ አስተዋጽኦ ላበረከታችሁ የኤል.ፒ.አይ የሥራ ኃላፊዎችና ባልደረቦች እንዲሁም ምሁራዊ አበርክቶ ላደረጋችሁ ለዶ/ር ጥላሁን በጅቷል፣ ለዶ/ር ሞገስ ደምሴ፣ ለዶ/ር ተካልኝ አያሌው እና ለአቶ ሚናስ ፍሥሓ ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

# መቅድም 1

ኢትዮጵያውያን አብሮ በመኖር ባደረጓቸው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስተጋብሮች ያካበቷቸው ዘመናትን የተሻገሩ ድንቅ ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶችና እሴቶች እንዲሁም ተቋማትና ክዋኔዎች ባለቤቶች ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ የአስተዳደር፣ የሕግና የፍትህ ተግባራትን የሚከውንባቸው ሀገረ-ሰባዊ ባህልና ሥርዓት ባለቤት ነው፡፡ እነዚህን ሀገራዊ ዕሴቶችና ተቋማትን በመጠቀም ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ከመከወን ባሻገር በየጊዜው የሚገጥማቸውን አለመግባባቶችና ግጭቶች ለመፍታት እንዲሁም ሰላማቸውን ለማረጋገጥ እና አንድነታቸውን ለማጠናከር ሁነኛ መሳሪያ አድርገው ሲጠቀሙባቸው ኖረዋል፡፡

በመላው የሀገራችን ክፍል የሚገኙ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ዕርቅና ሰላምን ለማምጣት ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች አንዱ የሽምግልና ሥርዓት ነው፡፡ ይህ ሥርዓት በተለያዩ ስያሜዎች በሁሉም ማኅበረሰብ ዘንድ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን ለመፍታት እስካሁን ድረስ በስፋት በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ለአብነትም በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ የአስተዳደር፣ የሕግ፣ የፍትሕና የዕምነት መሰረት በሆነው የገዳ ሥርዓት ውስጥ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን ለመፍታት የሚያገለግሉት ጉማና ሲንቄ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተለይም በአማራ ማኅበረሰብ የሚዘወተሩት የሽምግልና፤ የዘወልድና የአበጋር ሥርዓቶች፣ በጉራጌ ማኅበረሰብ ዘንድ እርቅ የሚፈጸምበት የየጆካ ሥርዓት፣ በጋሞና በሲዳማ አባቶች የሚከወኑ የእርቅና የሽምግልና ሥርዓቶች ጥቂቶቶቹ ማኅበራዊ ሀብቶቻችን ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን የመሳሰሉ ነባር ማኅበረ-ባህላዊ ዕሴቶችንና ተቋማትን ለሰላም ግንባታና ለኅብረ-ብሔራዊ አንድነታችን ግብአት አድርጎ መጠቀም ለነገ የማይባል ተግባር ነው፡፡

እንደሚታወቀው ከለውጡ አስቀድሞ ስለብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ስላሏቸው ቋንቋና ማኅበራዊ ሀብቶች ዙሪያ በስፋት የተነገረ ቢሆንም ለእነዚህ ሀብቶች ተገቢው ትኩረት ባለመሰጠቱ ሰላምንና ኅብረ-ብሔራዊ አንድነትን ለማጽናት ለሚደረገው ጥረት የነበራቸው ሚና እምብዛም ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይልቁንም በመጤ ባህሎች ተወረው እንዲሸረሸሩ ሆኗል፡፡ በአንጻሩ ከለውጡ በኋላ ትኩረት ከተሰጣቸው እሳቤዎች መካከል እነዚህን ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶች በወጉ በመለየት፣ በማጥናትና በመሰነድ ለአዎንታዊ ሀገራዊ ሰላም ግንባታና ኅብረ-ብሔራዊ አንድነት ግብአት አድርጎ መጠቀም አንዱ ነው፡፡ ለሀገራዊ ችግሮች ሀገራዊ መፍትሔ ያስፈልጋል የሚል አቅጣጫ ተይዟል፡፡

በመሆኑም የሰላም ሚኒስቴር በአዋጅ ከተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች አንዱ ለሰላም ግንባታ አስተዋጽኦ ያላቸውን ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶች ከመጤ ባህሎችና ልማዶች ወረራ በመታደግ ለአዎንታዊ ሰላም ግንባታ መጠቀም ነው፡፡ ይህንን ተግባር ዕውን ለማድረግ የማኅበራዊ ሀብት ግንባታ ዴስክ ባለሙያዎች በየክልሉ ካሉ የባህልና ስፖርት ባለሙያዎች ጋር በመሆን የልየታና የምዝገባ ተግባር በማከናወን ከየክልሉ ከተውጣጡ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ከሚመለከታቸው ተቋማትና ባለሙያዎች ጋር በመሆን የዕውቅና፣ የግብአት ማሰባሰብ ምክክር በማድረግ እና ሰነዱን በማዳበር በዚህ መልኩ ለሕትመት በቅቷል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሰላም ሚኒስቴር ሚንስትር

# መቅድም 2

# የአጥኚዎቹ ማስታወሻ

ይህን ጽሑፍ በማዘጋጀት ሂደት አጥኚዎቹ ከየክልሎች የሰበሰቧቸውንና ከድርሳናት ያገኟቸውን የማኅበራዊ እሴቶች መፍለቂያ የኾኑትን ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማትና ልዩ፣ ልዩ ክዋኔዎች በመልክ፣ በመልክ ለማደረጃት የተከተሏቸው ሚናዊ ምደባዎች (functional categorizations) የራሳቸው ውስንነቶች እንዳሏቸው መገንዘብ ያሻል፡፡ ከውስንነቶቹ መካከል አንዱ፣ አንዳንድ ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማትና ሥርዓቶች ጥርት ብለው በአንድ ምድብ ብቻ ባለመግባታቸው አንድ ማኅበረ-ባህላዊ ተቋም ከአንድ በበለጠ ምድብ ስር መካተቱ የተወሰነ ድግግሞሽ ማስከተሉ አልቀረም፡፡ በሌላ በኩል ሌላ ማኅበረ-ባህላዊ ተቋም ወይም ሥርዓት ደግሞ በአመዛኙ የሚጫወተውን ሚና ከግንዛቤ በማስገባት የበለጠ ሊገልጸው ይችላል በተባለ ምድብ ውስጥ ቢካተትም ተቋሙ/ሥርዓቱ በሌላ ምድብ ውስጥ ያለን ሚና አይጫወትም ማለት እንዳልኾነ እንዲሁ ልብ ይሏል፡፡ በተጨማሪም በየምድቦቹ ለተቋማቱ ወይም ሥርዓቶቹ የተሰጡ አጫጭር መግለጫዎች አገልግሎት እየሰጡ ያሉባቸውን አካባቢዎች ወይም ሕዝቦች ለማካተት ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን በማኅበራዊ መስተጋብርና ሌሎች ምክንያቶች የተነሳ በሚፈጠሩ የባህል  መወራረሶች (cultural contacts) የተነሳ ይመስላል በአንድ አከባቢ በስፋት የሚታወቁ አንዳንድ ተቋማት ወይም ሥርዓቶች በተመሳሳይ ስያሜ ወይም በሌላ ስያሜ፣ ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ተመሳስሎ በሌሎች ሕዝቦችና አከባቢዎች ጭምር ይተገበራሉ ወይም ይገኛሉ፡፡ በዚህ የተነሳ እንደዚህ ያሉ ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማት ወይም ሥርዓቶችን የእገሌ ሕዝብ ወይም የእገሌ አከባቢ ብቻ ሀብቶች ናቸው ብሎ በባለቤትነት መስጠት አይቻልም፤ የዚህ ጥናት ዓላማም አይደለም፡፡ ከዚህ አንጻር በዚህ ሥራ ውስጥ የየክልሉ መረጃ አቀባዮች በሰበሰቧቸው መረጃዎች ላይ በመመሥረት ማኅበረ-ባህላዊ ተቋሙን ወይም ሥርዓተ ክዋኔውን እየተገለገሉባቸው ያሉ አካባቢዎችና ሕዝቦች ተጠቀሰዋል ማለት እነዚሁ ሀብቶች በሌሎች አከባቢዎችና ሕዝቦች ዘንድ አገልግሎት እየሰጡ አይደሉም ወይም የሀብቶቹ ብቸኛ ባለቤት በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት አከባቢዎችና ሕዝቦች ብቻ ናቸው ለማለት እንዳልሆነ በሚገባ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይልቁንም የጥናቱን አመክንዮ ግልጽ ለማድረግ እንደተሞከረው በሀገራችን ያሉ ማኅበራዊ ሀብቶቻችንን ተጠቅመን ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ማስፈን እስከኾነ ድረስ የማኅበረሰቦች ሰላማዊ መስተጋብር እንዲዘልቅ፣ አልፎ አልፎ አለመግባባቶችና ግጭቶች ሲከሰቱም እርቀሰላም እንዲወርድ ታላቅ አበርክቶ እየሰጡ ያሉ ማኅበራዊ ሀብቶቻችንን አስመልክቶ «የኔ ብቻ ሀብቶች ናቸው» መሰል የባለቤትነት ውዝግብ ምክንያት ተቋማቱና ሥርዓቶቹ ከቆሙለት ዓላማና ሚና በተቃራኒ መቆም እንደማይገባ አጥኚዎቹ በጽኑ ማሳሰብ ይወዳሉ፡፡ ይልቁንም እየተዳከሙ ያሉት እንዲጠናከሩና እንዲያገግሙ፤ በአንድ አከባቢና ሕዝብ ዘንድ በሚገባ አገልግሎት እየሰጡ ካሉ ተቋማትና ሥርዓቶች ደግሞ መልካም ልምዶችንና ተሞክሮዎችን በመውሰድ የሀገርን ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ አዋጪው መንገድ ነው፡፡

በሌላ በኩል ይህ ጥናት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመልክ፣ በመልክ በማደራጀት ሚናዊ ምደባ (functional categorization) ከማድረግ በዘለለ ጽንሰ-ሃሳብ ላይ የተደገፈ ጥልቅ ትንተና አላደረገም፡፡ የጽሑፉ ዋነኛ ዓላማም ለዘላቂ ሰላም አበርክቶ ያላቸውን ማኅበረ-ባህላዊ ሃብቶችን በመለየት ለሰላም ግንባታ ሥራዎች አመቺ በኾኑ ሚናዊ ምደባዎች ስር ከመሰደር ውጪ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ አካሄድ ስላልተከተለ ጽሑፉ ማጠቃለያ እና/ወይም መደምደሚያ እንደሌለው ልብ ይሏል፡፡ በተጨማሪም በዚህ የምደባ ጥናት ውስጥ የተካተቱ ማኅበራዊ ሀብቶችና ሥርዓተ ክዋኔዎች ሀገራችን ካሏት እጅግ በርካታ ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማትና በውስጣቸው ከያዟቸው እሴቶች አንጻር እጅግ ጥቂት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ሰነድ ለሰላም ግንባታ ትሩፋት ያላቸው ሀብቶች ላይ እንደ መነሻ ወይም አመላካች ይሆናሉ ተብለው ከየክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በተሰበሰቡና በተወሰነ ደረጃ ከዚህ ቀደም ከተሠሩ ጥናቶች የተገኙትን ብቻ ያካተተ በመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉንን ሀብቶች በምሉዕነት ለማንጸባረቅ አቅም የሚጎድለው መሆኑን አበክረን እናስገነዝባለን። ይልቁንም ይህንን ጅምር ሥራ የሚያጠናክሩ ጥረቶች በክልሎች፣ በሚመለከታው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ በትምህርት ተቋማትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ ወዘተ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም የባህል ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በዋነኝነት የተሰጠው የሥራ ኃላፊነት ቢሆንም ይህ ጥናት በተለየ መልኩ ትኩረት ያደረገው ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶቻችን ከዘላቂ ሰላም ግንባታ አንጻር ያላቸውን ሚና በመለየት የመሰነድና የሰላም ሚኒስቴር በአዋጅ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች ጋር አስተሳስሮ ማዘጋጀት ነው። በጥናቱ ሂደት ላይም ከባህል ሚኒስቴር ጋር ውይይት ከማድረግም ባሻገር የክልልና ከተማ አስተዳደሮች የባህል ቢሮዎች መረጃዎቹን በመሰብሰብ ሥራው ላይ በዋነኝነትና በባለቤትነት መንፈስ በመሳተፍ አስተዋጽኦ አድርገዋል። የሰላም ሚኒስቴርም ሂደቱን በተቀናጀ መልኩ በመምራትና የመጀመሪያው ረቂቅ ላይ በጎ አስተዋጽኦ በማድረግ የሚጠበቅበትን ሚና ተጫውቷል። በተመሳሳይ መልኩ ላይፍ ኤንድ ፒስ ኢንስትቲዩት በገንዘብ እንዲሁም ባለሙያዎች በሥራው ሂደት ላይ በማሳተፍ ከፍተኛ አበርክቶ አድርጓል። የአጥኚ ቡድኑም ሥራውን በሚሠራበት ወቅት ከሰላም ሚኒስቴር፣ ከባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ ከክልልና ከተማ አስተዳደር ባህል ቢሮዎች እና ከላይፍ ኤንድ ፒስ ኢንስቲትዩት ለተደረገለት ከፍተኛ እገዛ ምስጋናችንን ለማቅረብ እንወዳለን።

# መግቢያ

የሰላም ሚኒስቴር የፌደራል ተቋማት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ 1263/2014 መሰረት ከሚሠራቸው ሥራዎች መካከል አንዱ ማኅበራዊ ሀብቶቻችን (እሴቶቻችን) ለአዎንታዊ ዘላቂ ሰላም ግንባታና ለብሔራዊ መግባባት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው፡፡ በሀገራችን ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን በሰላም ግንባታና ብሔራዊ መግባባት ዘርፍ ስር የማኅበራዊ ሀብት ግንባታ ዳይሬክቶሬት/ዴስክን በማቋቋም የሀገር በቀል የእርቅና ሽምግልና ሥርዓቶችን መልሶ ለመገንባት ይረዳ ዘንድ የጋራ እሴቶቻችን እንዲጎለብቱና እንዲዳብሩ በማድረግ ከዘመናዊዉ የፍትህ አሰጣጥ ሥርዓት ጋር በማግባባትና በማወዳጀት መደማመጥ፣ መከባበር እና መቻቻል እንዲያድግ በማድረግ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የተለያዩ ሥራዎች ሲሠራ ቆይቷል፡፡

ይህን የማኅበራዊ ሀብቶች ቅኝት ጥናትም የሰላም ሚኒስቴር ከባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደር ባህልና ስፖርት ቢሮዎችን በማሳተፍ በየአከባቢው ያሉ ማኅበራዊ ሀብቶቻችን የሚሰንድ የዳሰሳ ጥናት ተካሄዷል፡፡የዳሰሳ ጥናቱ ሲካሄድ የሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ባህልና ስፖርት ቢሮዎች ጥናቱን የሚያከናውን የሚመለከተውን ኃላፊ ወይም ባለሙያ በመመደብ እንዲሁም በሰላም ሚኒስቴር በኩል አስፈላጊውን ክትትል በማድረግና በየክልሉ የዳሰሳ ጥናት ለሚያካሂዱት ኃላፊዎች ወይም ባለሙያዎች ተገቢው ገለጻ (ኦሪየንቴሽን) በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የሰላም ሚኒስቴር የማኅበራዊ ሀብት ባለሙያዎችም ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን በምድብ በመደልደል ሥራዉ በውጤታማነት እንዲጠናቀቅ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡ በተካሄደው የዳሰሳ ጥናት መሰረት በሁሉም ክልሎችና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች 40 ያህል ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማት እና ሥርዓቶች ከነመገለጫዎቹ ተሰብስበዋል፡፡ ይኹንና ሀገራችን ካሏት እምቅ የማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶች አንጻር የተሰበሰበው መረጃ መጠን ውስን መኾኑን በመረዳት የሰላም ሚኒስቴር ከላይፍ ኤንድ ፒስ ተቋም ባገኘው እገዛ አማካኝነት የሙያው ባለቤት የኾኑ አጥኚዎች ከተሰበሰበው መረጃ በተጨማሪ ከዚህ ቀደም የተደረጉ ጥናቶችንና ልምዶቻቸውን እንደ ግብዓት በመጠቀም ይህን ሰነድ አዘጋጅተዋል፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በኋላም በዚህ መልክ የተዘጋጀው፤

- ሀገራችን ካላት እምቅ ሀብት አንጻር እንደ መነሻ የሚታይና በቀጣይ እየዳበረ የሚሄድ፣
- በቀላሉ ተደራሽ የኾነ፣ እንደ ካታሎግ ወይም «ሚኒ-ኢንሳይክሎፔዲያ» የሚያገለግል፣
- በሰላም ግንባታ ዙሪያ ልዩ ምልከታ የሚያደርግ (ከግጭት መፍቻነት ባሻገር በዘወትር ሕይወት ለዘላቂ ሰላም ሚና የሚጫወቱትን ያካተተ)፣
- በቀላል አቀራረብ ተሰናድቶ በማኅበራዊ ሀብቶቻችን ዙሪያ መሠረታዊ መረጃ የሚሰጥ፣
- ለአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች፣ ለቅድመ-ማስጠንቀቂያና መሰል የሰላም ግንባታ ሥራዎች እንደ ምንጭ ("ሪሶርስ ቡክ") የሚያገለግል እንዲኾን ታስቦ ነው፡፡

# ማኅበራዊ ሀብቶች እንደ የሰላም መሠረተ-ልማት (Social Capital as Infra-structure of Peace)

የሰላም ሚኒስቴር ሰላምን ለማረጋገጥ የሚከተለው አስተሳሰብ ከቀደመው ሥርዓት በጉልህ የሚታዩ ልዩነቶች አሉት፡፡ ከዚህ ቀደም በአብዛኛው አሉታዊ ሰላም ላይ ያተኮረና በግጭት ዐውድ ትንተና (conflict analysis)፣ በግጭት ሃሰሳ (conflict mapping) እንዲሁም በግጭት ቅድመ-ማስጠንቀቂያ (conflict early warning) ላይ የተመሰረተ አስተሳሰብና አካሄድ ሰፍኖ የቆየ ሲሆን ከፖለቲካ ለውጡ አቅጣጫ ጋር የተናበበ የሰላም አተያይ መቅረጽ አስፈልጓል፡፡ በመሆኑም አዲሱ የሰላም አተያይ የሚከተሉትን መሰረታዊ ባህርያትን ያካትታል፡፡ በዋነኛነት የሰላም እሳቤው በሰላም ዐውድ ዳሰሳ (peace mapping) ላይ የተመሰረተ ሲሆን መገለጫዎቹም፤ i) ከሰላም ዐውድ ትንተና የሚነሳ፣ ii) በኢትዮጵያዊ ማኅበረ-ባህላዊ እሴቶች ላይ የተመሰረተ፣ iii) ለአወንታዊ ሰላም ግንባታ ቅድሚያ የሚሰጥ፣ iv) የግጭት ዐውድ ትንተና፣ የግጭት ቅድመ-ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ እና የግጭት ዘላቂ መፍትሄ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የዚህ ዓይነቱ የሰላም እሳቤ የሚገነባበትና የሚያብብበት ሥነ-ምህዳር እንደሚያስፈልገው ይታመናል፡፡ አዎንታዊ ሰላም ግንባታ የሚጀምረው በግለሰብ ደረጃ ሲሆን ማንኛውም ሰው የውስጥ ሰላም ከመገንባት አንስቶ በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብ፣ በተቋም እንዲሁም በሀገር ደረጃ ሰላም የሚተከልበትንና የሚጸናበትን አካሄድ ማስፈንን ይጠይቃል፡፡ ይህ ሁሉን አቀፍ የሰላም አተያይ አዎንታዊ ሰላምን ብቻ በማቀንቀን ተጠምዶ ለሚፈጠሩ አጣዳፊ ግጭቶች ጆሮ ዳባ የሚል ሳይሆን በሚፈጠረው ግጭት መጠን ተገቢውን ትኩረትና ምላሽ መስጠትን የሚያስቀድም ይሆናል፡፡

አዎንታዊ ዘላቂ ሰላም ማስፈን የሚቻለው ግጭቶች በተፈጠሩ ቁጥር በሚወሰዱ እርምጃዎች ሳይኾን የዜጎች የዕለተለት ሕይወት ውስጥ መተማመንን፣ ትብብርን፣ አብሮነት የመሳሰሉ እሴቶችን በማጎልበት በኩል ጉልህ ፋይዳ የሚጫወቱ ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማት ጥንካሬ እና ተቋማቱ ባሏቸው የሰላምና የማኅበራዊነት ልክ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር እነዚህን ተቋማት፣ ሥርዓቶች ወይም ልማዶች እንደ የሰላም መሠረተ-ልማት (infrastructres of peace) መመልከቱ ተገቢ ይኾናል፡፡ በአንድ ሀገር ወይም አካባቢ የልማት አውታሮች ወይም መሠረተ-ልማቶች በተሟሉበት እና በአስተማማኝ አቋም ላይ በተገኙበት ዐውድ የተሳለጠ ልማት፣ እንቅስቃሴ እና ግንኙነት ማድረግ ውጤታማ እንደሚያደርግ ሁሉ የሰላም፣ የእርቅ፣ የአብሮነት፣ የመደጋገፍ፣ ወዘተ መሠረተ-ልማቶች የኾኑት ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማት ጠንካራ በኾኑባቸው አካባቢዎች ወይም ማኅበረሰቦች ዘንድ ዘላቂ ሰላም ማስፈን፤ አልፎ አልፎ ግጭቶችና አለመግባባቶች ሲፈጠሩም የከፋ ጉዳት ሳይደርስ መፍትሔ ማበጀት እንደሚቻል እሙን ነው፡፡ ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶችን ከዚህ አንጻር ማየት ሲቻል ግጭትን እየተከተሉ መፍትሔ ከመፈለግ ባሻገር ማኅበረ-ባህላዊ

እሴቶች በማጠናከርና የሰላም ሥራን በዘወትር ሕይወት ውስጥ ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ አዎንታዊ ዘላቂ ሰላምን ማምጣት ያስችላል፡፡ ይህን በማድረግ ጥረት ውስጥ ደግሞ በየማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶችን መለየት፣ መሰነድ፣ ማጥናት፣ ማስተዋወቅ፣ መጠበቅ አስፈላጊ ሲኾን በዚህ ሰነድ በቀላል አቀራረብና በሀገርኛ ቋንቋ የተወሰኑትን ሀብቶች በመለየትና በመመደብ ለቀጣይ ተመሳሳይ ሥራዎች መነሻ እንዲኾን ተሞክሯል፡፡

# የመረጃ አመዳደብና አደረጃጀት

አጥኚዎቹ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ከየክልሎቹ የተሰበሰቡትን እና ከዚህ ቀደም በተናጠል፣ አልፎ አልፎም በክልል ማዕቀፍ ጥናት የተካሄደባቸውን ልዩ፣ ልዩ ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማትና ሥርዓቶች በመጨመር በሦስት ሚናዊ አመዳደብ (functional classification) ለማጠናቀር ሞክረዋል፡፡ እነዚህ ምድቦችም፤

- ክፍል አንድ፤ ማኅበራዊ ትስስርና ተግባቦት የሚያጠናክሩ ሥርዓቶችና ተቋማት፣
- ክፍል ሁለት፤ ድኅረ-ግጭት ለሰላምና እርቅ ሚና የሚጫወቱ ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶች፣
- ክፍል ሦስት፤ ድንበር-ዘለል ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶች ሲኾኑ ምንነታቸውም እንደሚከተለው ተብራርቷል፡፡

ማኅበራዊ ትስስርና ተግባቦት የሚያጠናክሩ ሥርዓቶችና ተቋማት ስንል በሀገራችን ልዩ፣ ልዩ አካባቢዎችና ማኅበረሰቦች እርስበርስ የሚያደርጉትን መስተጋብር ጤናማና ሰላማዊ ለማድረግ፣ አብሮነታቸውን፣ አጋርነታቸውን፣ አንድነታቸውን፣ ወንድማማችነታቸውን በአጠቃላይ ማኅበራዊ ትስስሮቻቸውን ለማጽናት በዘመናት ሂደት የፈጠሯቸው፣ ያዳበሯቸው እና የነዚህ እሴቶች መፍለቂያ የኾኑ ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማትንና ልዩ፣ ልዩ ሥርዓቶችን ማለታችን ነው፡፡

ድኅረ-ግጭት ለሰላምና እርቅ ሚና የሚጫወቱ ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶች፣ ይህኛው ምደባ ደግሞ ማኅበረሰቦች በውስጣቸውም ኾኑ ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር አለመግባባቶች እና ግጭቶች ሲፈጠሩ ችግሮቹን በመፍታት፣ እርቀ-ሰላም በማውረድ ማኅበራዊ ሕይወት ወደቀድሞ ኹኔታ እንዲመለስ የሚስችሉ ልዩ፣ ልዩ ብልሃቶችንና እሴቶችን አምቀው የያዙ ተቋማትንና ሥርዓቶችን ይመለከታል፡፡

ድንበር-ዘለል ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶች፣ ይህኛው ምድብ ሀገራችን ኢትዮጵያ ባህለ-ብዙኅ የኾኑ ማኅበረሰቦቿ በተለያዩ የፖለቲካ ሥርዓቶች አማካኝነት በሚፈጠሩ የአስተዳደር ወሰኖች የየራሳቸው መልከዓምድራዊ ወሰኖች ያሏቸው ቢኾኑም በዕለተለት ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶቻቸው የተነሳ ወሰን ተሻጋሪ እሴቶችን አዳብረዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በተለይ አዋሳኝ ሥፍራዎች ላይ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች የየራሳቸው ቋንቋ፣ ባህል፣ ወግ ቢኖራቸውም ወሰን ተሻግረው መግባባት፣ መሸጥና መለወጥ በጋብቻም መተሳሰር ብቻ ሳይኾን በእነዚህ ግንኙነቶች ውስጥ አለመግባባት ወይም ግጭት ሲፈጠርም ከሁለቱም ባህል በተቀዱ ብልሃቶችና ተቋማት አማካኝነት ችግሮቻቸውን ይፈታሉ፡፡ በዚህ ምድብ የቀረቡትም አንድም ማኅበረሰብን ከማኅበረሰብ፣ ጎሳን ከጎሳ በማዛመድ ወይም በማገናኘት የአብሮነት ሚና የሚጫወቱ፤ አንድም ድንበር የሚዋሰኑ ሕዝቦች በጋራ የመሠረቷቸው የግጭት መፍቻና የእርቀ-ሰላም ማውረጃ ተቋማት፣ ልማዶችና ሥርዓቶች ናቸው፡፡

# ክፍል አንድ

# ማኅበራዊ ትስስርና ተግባቦትን የሚያጠናክሩ ሥርዓቶችና ተቋማት

# መግቢያ

በሃገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የራሳቸው ማንነትና ባህል ያላቸው በርካታ ማኅበረሰቦች እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ማኅበረሰቦች እርስ በርስ የሚያደርጉትን መስተጋብር ጤናማና ሰላማዊ ለማድረግ በዘመናት ሂደት የፈጠሯቸውና ያዳበሯቸው ማኅበረ-ባህላዊ ሃብቶች ያላቸው ሲሆን እነዚህም ማኅበረሰቦቹ የእርስበርስ ግንኙነቶቻቸውን፣ አብሮነታቸውን፣ አጋርነታቸውን፣ አንድነታቸውን፣ ወንድማማችነታቸውን በአጠቃላይ ማኅበራዊ ትስስሮቻቸውን በማጽናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተውላቸዋል፡፡ ከዚህ በታች የተካተቱት ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማትና ሥርዓቶችም በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ ኢትዮጵያውያን ሲጠቀሙባቸው የነበሩና አሁንም እየተጠቀሙባቸው የሚገኙ ግጭት ከልካይ ማኅበረ-ባህላዊ እሴቶች ናቸው፡፡

# ገዳ

የኦሮሞ ህዝብ ከጥንት ጀምሮ ሲጠቀምባቸው የነበሩና አሁንም ግልጋሎት እየሰጡ ያሉ የበርካታ ግጭት ከልካይ ማኅበረ-ባህላዊ ሃብቶች ባለቤት ነው፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ሃብቶች የኦሮሞን ህዝብ እርስበርስ ያጋመዱና ሰላማዊ መስተጋብርን ማጽናት የቻሉ ከመሆናቸውም ባሻገር ከከሌሎች ወንድም ህዝቦችና ጎረቤቶቹ ጋር በሰላም አብሮ መኖር እንዲችል ማህበረ-ባህላዊ ምህዳሩን አመቻችተውለታል፡፡ ከነዚህ መካከል የሚከተሉት ማኅበረ-ባህላዊ ሃብቶች በግጭት ከልካይነታቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከታሉ በሚል የተጠቀሱ ናቸው፡፡ የገዳ ስርዓት የኦሮሞ ህዝብ ከመሠረታቸውና ካዳበራቸው ሁሉን አቀፍ የአስተዳደር ስርዓቶች መካከል ከፍተኛው ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንደታዋቂው የኦሮሞ ህዝብ የፖለቲካ ታሪክ ጸሐፊ አስመሮም (1973) ገለጻ ገዳ የፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የአምልኮ ሥርዓቶችን በማካተት በየስምንት ዓመቱ እርስበርሳቸው በሚተካኩ የመደብ (ሉባ) ስርዓት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እያንዳንዱ የገዳ መደብለተወሰነ ጊዜ (ገዳ) በስልጣን ላይ የሚቆይበት ይህ ስርዓትበመደበኛ የስልጣን ማስተላለፍ ሥነ-ስርዓት የሚጀመርና የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡

የገዳ ስርዓት የርስ በርስ ሚዛናዊ ክትትልና ቁጥጥርን፣በየስምንት ዓመቱ በተከታታይ የሚደረግ የስልጣን ሽግግር፣የስልጣን ክፍፍል (በአስፈፃሚ፣ በሕግ አውጭ እና በፍትህ አካላት)፣ ሚዛናዊ ተቀናቃኝ (በአምስት ፓርቲዎች መካከል) እና በከፍተኛ እና ዝቅተኛ መካከል የሥልጣን መጋራት መርሆዎች አሉት፡፡ የአስተዳደራዊ አካላት ስልጣን በአፋኞች እጅ እንዳይወድቅ ይከላከላል፡፡ ከዚህ አንጻር በየጊዜው የሚካሄዱ ምርጫዎች፣ ተጠያቂነት የሚሰፍንበት አሠራር፣ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር የሚከናወንበት አካሄድ፣ ሀሳብን በነፃነት መግለፅ፣ እንዲሁም መግባባትን ታሳቢ ያደረጉ ረጃጅምና የተዋቀሩ ክርክሮች የማኅበረ-ባህላዊ ሃብቱን (የገዳ ስርዓትን) ዴሞክራሲያዊነት የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ እነዚህ የስርዓቱ ገፅታዎች የኦሮሞ ህዝብን ውስጣዊ አንድነት ከማጠናከር ባለፈ የተለያዩ ባህሎች፣ ሃይማኖቶች እና የፖለቲካ ፍላጎቶች ባሏቸው ህዝቦች መካከል የውይይት ባህልንበማጠናከር ሰላማዊ ግንኙነቶችን አዳብረዋል፡፡ የሥርዓቱ መርሆዎች የሁሉም ጎሳዎች፣ የዘር ሐረጎች፣ ክልሎች እና ኮንፌዴሬሽኖች ሚዛናዊ ውክልና፣ የመሪዎች ተጠያቂነት፣ በእርቀሰላም አለመግባባቶችን መፍታት እና መሰረታዊ መብቶች እና ነፃነቶች መከበራቸዉን ያካተቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም የገዳ ስርዓት ግጭትን ከመከላከል አንጻር የጎላ ሚና ይጫወታል፡፡ ለምሣሌ "የገዳ ምክር ቤት ከአንድ ባህላዊ ክዋኔ በፊት ወይም በክዋኔው ወቅት የሚፈጠሩ ቀውሶችንና ማንኛውንም ዓይነት ግጭቶችን (ልማዳዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሞራላዊ፣ ህጋዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ) ይፈታል" በማለት አስመሮም በጽሁፉ ያብራረል (1973፡ 86)፡፡

ገዳ በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች በተለያየ ደረጃ እስካሁን እየተተገበረ የሚገኝ ህያዉ ስርዓት ነዉ፡፡ የኦሮሞን የዓለም አተያይ፣ ሥነምግባር፣ እሴቶችን እና ደንቦችን በመቅረፅ እንዲሁም የኦሮሞን ህዝብ እርስበእርስ እና ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር በማስተሳሰር ረገድ ወሳኝ አስተዋጽኦ ያበረከታል፡፡ በገዳ ስርዓት ውስጥ ያሉ ተቋማት ማህበራዊ ትስስር እና ውህደት ለመፍጠር፣ የጋራመግባባት፣ ግጭቶችን እና አለመግባባቶችን በሰላም ለመፍታት፣ የሰብአዊ መብቶችን ማክበር እንዲሁም ማህበራዊ መረጋጋት እና ዘላቂ የህብት አያያዝን ለመፍጠር የታቀዱ ናቸው፡፡

# የጌዴኦ የገዳ ሥርዓት

የጌዴኦ የገዳ ሥርዓት በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የጌድኦ ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደርና ዳኝነት ሥርዓት ነው። የጌዴኦ የገዳ ሥርዓት የተለያየ የስልጣን እርከን ባላቸው ክፍሎች የተደለደለ፣ሁሉም የየራሳቸውን የሥራ ድርሻ ሊያከናውኑ በሚችሉበት መልክ የተዋቀረ በመሆኑ ሥርዓቱ በባህሪው በጣም ዲሞክራሲያዊ እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ ይነገራል። ይህ የጌዴኦ የገዳ ሥርዓት ዘጠኝ አባላት የሚገኙበት ጠቅላላ ጉባኤ ያለው ሲሆን አመራር የሚሰጠው በጠቅላላ ጉባኤው በብሔረሰቡ ቋንቋ በ«ያአው» ነው። የያአው አባላት ልዩ ልዩ የስልጣን ደረጃዎች ያሏቸው ሲሆን እነዚህ የስልጣን እርከኖች በተዋረድ "አባገዳ" ፣ "ጃላባ"፣ "ሮጋ"፣ "ጃልቃባ"፣እና "ሀይቻ" በመባል ይታወቃሉ። የሁሉም የበላይ የሆነው አባገዳ የሥርዓቱ የበላይ መሪ እና ለሕዝቡ ሰላምን፣ ብልጽግናን፣ ፍቅርን ጤናን የሚለምን በመሆኑ በሕዝቡ ዘንድ ከማንኛውም ኃጢአት መጥፎ ሥራ የነፃነው ተብሎ ይታመናል። ሁለተኛው የስልጣን እርከን "ጃላባ" የሚባለው የአባገዳው ምክትል ሲሆን ዋና ተግባሩ ከአባገዳው መልዕክት እየተቀበለ ለ"ሮጋ"ዎች የሚያቀብልና ከሌሎችም አካላት መልዕክት በመቀበል ለአባገዳው የማድረስ ስልጣን የተሰጠው ነው። ሌሎች እርከኖች እንደዚሁ የየራሣቸው ኃላፊነትና የሥራ ድርሻ ያላቸው ሲሆን በዚህ መልኩ የተዋቀረው የጌዴኦ የገዳ ሥርዓት በየስምንት ዓመቱ የስልጣን ርክክብ እንዲደረግ ያዛል። ወቅቱ ሲደርስ ይህን የስልጣን ርክክብ የሚያከናውኑ"ራባ" ዎች ተብለው የሚጠሩ ሲሆን ስልጣን ተረካቢው "ሉባ"፣ ስልጣን አስረካቢው ደግሞ "ዮባ" በመባል ይታወቃሉ።

# ሲንቄ

ሲንቄ በኦሮሞ ህዝብ ማህበረ-ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ የሴቶች ፖለቲካዊ፣ አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሰብአዊ መብቶችን ለማስጠበቅ የሚያገለግል በተለይም በአርሲ ኦሮሞዎች ዘንድ የሚገኝ ገለልተኛ የሴቶች ተቋም ነው፡፡ ሲንቄ በሠርግ ቀን በበረከት ሥነ-ሥርዓት ላይ በእናቷ ለሙሽሪት የሚሰጥ የጋብቻ በትር ነዉ፡፡ ሴቶች ሲንቄን ለተለያዩ ሥነ-ሥርዓቶች የሚጠቀሙባቸው ሲሆን ከነዚህም መካከል፤

- ደረጃቸውን እና ክብራቸውን ለማሳየት፣
- መብቶቻቸውን ለማስጠበቅ እና
- ከጋብቻ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ውዝግብ እስከነሳ ግጭት ድረስ ያሉ ግጭቶችን ለመፍታት ይጠቀሙበታል፡፡

በተጨማሪም ሲንቄ የተለያዩ ምሳሌያዊ ውክልናዎች ያሉት ሲሆን፤ የኦሮሞ ሴቶች የጋብቻ ምልክት፣ የኦሮሞ ሴቶች ኃይል፣ የግጭት አፈታት ዘዴ፣ የጸሎት እና ለተለያዩ ሥነ-ስርዓት ዓላማዎች የሚያገለግል የአምልኮ ዱላ ወይም ብትር ነዉ፡፡ በገዳ ስርዓት ውስጥ የተመሰረተው የሲንቄ ተቋም የኦሮሞ ሴቶች እኩልነትን፣ ማህበራዊ ፍትህን፣ አብሮነትን እና ዘላቂ ሰላምን እና እድገትን ለማጎልበት የሚያስፈልጓቸዉን መዋቅራዊ ለዉጦች ያበረታታል፡፡ በመሠረቱ ሲንቄ የሰላም ምልክት በመሆኑ በተግባር ስለሰላም ለማስተማርና የህብረተሰብ ግንኙነቶችን የሚያሳድጉ ድልድዮችን ለመገንባት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በመሆኑም በሲንቄ ኃይል አማካኝነት ማህበራዊ ትስስርን ያጠናክራሉ እንዲሁም ያፀኑታል፡፡ ሲንቄ ሴቶችን ለማብቃት የሚያስችል ውጤታማ ዘዴ ሲሆን አሁንም ቢሆን በኦሮሞ ህዝብ ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

# ጉዲፈቻ

ጉዲፈቻ በኦሮሞ ህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ አስደናቂ ከሆኑት የገዳ ስርዓትና ሌሎች አስፈላጊ ተቋማት መካከል የሚመደብ ማህበራዊ የውህደት ተቋም ነዉ፡፡ ይህ ስርዓት ሞጋሳ ከሚባለው ሌላው የኦሮሞ ማኅበረ-ባህላዊ ሀብት ጋርም አንፃራዊ ቅርርብ አለዉ፡፡ በጉዲፈቻ ስርዓት ልጆች የሌሏቸው መሃን የሆኑ ባልና ሚስቶች ወይም ቤተሰቦች ከሌላ ቤተሰብ የመጡ ልጆቻቸውን ጉዲፈቻ (ማደጎ) የሚያድርጉበት ነው፡፡ በዚህ ስርዓት መሠረት የጉዲፈቻ ልጆች (ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች) በህጋዊ ጋብቻ ከሚገኙ ወንዶች ወይም ሴቶች ልጆች ጋር እኩል መብቶችና ግዴታዎች ይኖራቸዋል፡፡ጉዲፈቻ ልጅ ለሌላቸው ጥንዶች ማህበራዊ ዘርን በመስጠት ልጅ እንዲኖራቸውና ወራሾች እንዲያገኙ በማስቻልከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዋናነት የጉዲፈቻ ባህል በእርጅና ወይም በጤንነት ጊዜ የንብረት ወራሽ እና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ እንዲያገኝ የቤተሰብንቀጣይነት ማረጋገጥ ነው፡፡ የጉዲፈቻ አሠራር የሕፃናት ችግርን ለማስወገድ በሰፊው ልንጠቀምበት የምንችለው ሃገር-በቀል የጣልቃገብነት ስልት ነው፡፡ እንደ አገርበቀል የሕፃናት እንክብካቤ በአጠቃላይ ሕፃናትን እና ወላጅ አልባ ሕፃናትን እንዲሁም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናትን በማዋሃድ እና በማስተዋወቅ የማስተሳሰር ስራ ይሰራል፡፡ ዘላቂ ሰላም ግንባታን መሰረት ያደረገ የተገፉ ህብረተሰብ ክፍሎችን መሰረት ያደረገ ስርዓት በመሆኑ ሰላምን ሲያፀና ቆይቷል፡፡

# ሞጋሳ

የኦሮሞ ህዝብ ከኅብረተሰቡ ጋር እንዲዋሃዱ ለግለሰቦች እና ለጎሳዎች አዲስ ስም የሚሰጥ ልዩ የማኅበራዊ ጉድኝት ዓይነት ነዉ፡፡ በኦሮሞ ማኅበረሰብ ውስጥ ሞጋሳ ልዩ እና ጉልህ የሆነ ባህላዊ ባህሪ ያለዉ ስርዓት ሲሆን የሌላው (ኦሮሞ ያልሆነ) ማህበረሰብ ተወላጅ ወደ ኦሮሞ የሚቀላቀልበት ማህበራዊ ዘዴ ነው፡፡ ሞጋሳ በኦሮሞ ጎሳዎች መካከልም ሊከናወን ይችላል፡፡ ይህ ከአንድ ጎሳ ወደ ሌላው ጎሳ ለመሰየም የግለሰቦችን ጥያቄ በራሱ ብስለት ውስጥ የገባበት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት አሠራሩ በተለይ ሞጋሳ በማህበረሰብ ደረጃ መጠኑ የቀነሰ ቢሆንም በግለሰቦች ደረጃ አሠራሩ እየቀጠለ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የገዳ ውህደት ገጽታ ከሰው ልጆች ግንኙነት ሥነ-ምግባራዊ ልኬቶች ባሻገር ለተፈጥሮ እና ለፈጣሪ የመግባባት እና የአብሮነት ስልቶች ይዘልቃል፡፡ ሞጋሳ ለሰላም ግንባታ አስፈላጊ ለሆኑ ማህበራዊ ትስስሮች እና ምንጮች ማፈላለጊያ ባህላዊ ስልት ነው፡፡

# ቀነፋ

ቀነፋ የሴቶች መብት ምልክት ሲሆን በተለይ በአርሲ ኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ የተለመደ ነው፡፡ ቀነፋ ገና ልጅ ለምትወልድ ሴት ግንባሯ ላይ የሚለበስ ጌጥ ሲሆን ሴቶች እሱን በመልበሳቸው ኩራት ይሰማቸዋል፡፡ በዚህ ደንብ መሠረት አንዲት ሴት ልጅ ከወለደች በኋላ ከአራት እስከ አምስት ወር ትለብሰዋለች፡፡ የመልበስ ዓላማው ለወለደች ሴት እረፍት እና ህክምና ለመስጠት እና ከማንኛውም ግዴታ ነፃ እንድትሆን ለማድረግ ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት አንዲት ሴት በእርግዝና ወቅት ብዙ ጉልበት ስለምታጠፋና በወሊድ ጊዜ ደም ስሚፈሳት በድህረ-ወሊድ ወቅት አካላዊ ድካም ይሰማታል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡የቀነፋ ስርዓት በሥራ፣ በቤትና በየትኛውም ቦታ የሴቶች መብትን በደንብ ያስጠብቃል፡፡ ቀነፋ ለባሽ ሴትን ባለቤቷ እንኳ ቢሆን ሊነቅፋት አይችልም፡፡ ይህ ስርዓት እንደወትሮው ምክንያታዊ ባልሆኑ ጉዳዮች ሴቶችን ሊገጥሟቸው ከሚችሉ ወከባዎችና በደሎች በእርግዝናና በድህረ-ወሊድ ወቅት የመጠበቅ ዓላማ እና ውጤት ያለው ነው፡፡ በተጨማሪም በማህበረሰቡ ዉስጥ ሴቶች ካላቸዉ ብዛት አንጻር ማኅበራዊ ፍትህን በማስጠበቅ ከፍተኛ ሚና የሚጫወትና በሴቶችና ወንዶች መካከል መተማመንን መሰረት

ያደረገ ትስስርና ግንኙነትን ያረጋገጠ ባህላዊ ምልክት በአሁኑ ነዉ፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ በሙሉ ፈቃዱ ተቀብሎ የሚተገብረዉና ባህላዊ እምነቱ በመሆኑ ዘላቂ ሰላምን በሴቶችና ቤተሰቦቻቸዉ በኩል የሚገነባና የሚያረጋግጥ ዕንቁ ወግ ነዉ፡፡ ይህ ሀብት ቀደም ሲል በአርሲ ኦሮሞ ማህበረሰብ አካባቢ በስፋት የሚተገበር ቢሆንም ጥንካሬዉ ባሁን ወቅት እየተዳከመ እንደሚገኝ መታዘብ ይቻላል፡፡

# የጽዋ ማኅበር

በኦርቶዶክስ ክርስቲያን እምነት ዘንድ ያለና በአብዛኛው ሴቶች የሚመሠርቱት የማኅበራዊ ሀብት ዓይነት ነው፡፡ ማኅበሩ የሚመሠረተው በአከባቢያቸው በሚገኝ ቤተክርስቲያን (አጥቢያ) ሲኾን የማኅበሩ ስያሜም በአብዛኛው የአጥቢያ ቤተክርስቲያኑን ታቦት ስም፣ አለያም የሌሎች ቅዱሳን ስም ሊኖረው ይችላል (Flemmen & Zenebe 2016)፡፡ ማኅበሩ ስያሜውን ያገኘበት ቅዱስ ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ ክብረ-በዓልን አስመልክቶ አባላት በዙር ከሚያደርጉት የምግብና የመጠጥ አቅርቦት በዓሉን ሃይማኖታዊና ዘልመዳዊ ትውፊት በጠበቀ መልኩ ከማክበር በዘለለ አባላቱን በማኅበራዊ ሕይወት የማስተሳሰር ከፍተኛ ሚና የሚጫወት፣ በመላው ሀገራችን በእምነቱ ተከታዮች እየተተገበረ ያለ ማኅበራዊ ሀብት መፍለቂያ ተቋም ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ይህ ማኅበራዊ ሀብት በአመዛኙ በሃይማኖታዊ ማኅበራዊ ሀብት ሥር የሚመደብ ቢኾንም በርካታ ትሩፋቶች አሉት፡፡ ለአብነት ያህል ማኅበሩ በአብዛኛው ሴቶች የሚሠባሰቡበት እንደመኾኑ የሴቶችን አብሮነትና አጋርነት በማጠናከር፣ ለሴቶች ከማጀት ውጪ አንድነተቻውንና መረዳዳታቸውን የሚሳዩበት ብሎም ከዘወትር አድካሚ የሥራ ኃላፊነቶቻቸው በማስተንፈስ እፎይታ የሚያገኙበት ዐውድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የማኅበሩ አባላት የጤና፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ (ለምሳሌ የጋብቻ) እንቅፋቶች ሲያጋጥሟቸው ከሥነልቡናዊ ድጋፍ አንስቶ የተለያዩ እርዳታዎችን የሚያገኙበትን እድል የሚፈጥር ማኅበር ነው፡፡ በተጨማሪም በአባላት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችና ግጭቶችም እንዲፈቱ የራሱን ሚና የሚጫወት ማኅበር ሲኾን በውስጥ ያለው አደረጃጀት እና አመራር በራሱ የሴቶችን ራስ-በራስ የማስተዳደር አቅም ያሳያል፡፡ የጽዋ ማኅበሩ መሪ «ሙሴ» የሚል ስያሜ ያላት ሲኾን የዕለቱን ምግብ በማከፋፈል፣ የአባልነት ክፍያ በማሰባሰብ እና ማንኛውንም ማኅበሩን የሚመለከቱ ጉዳዮች የማቀላጠፍና የማስተባበር ሚና ትጫወታለች፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የጽዋ ማህበር በመሠረታዊነት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትያን አባላት የሚመሠረትና ከወር ውስጥ በጽዋ ማህበሩ ስያሜ ቀን ተገናኝተው ከሃይማኖታዊ እስከ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብሎም የሰላምና ደህንነት ጉዳዮችን አንስተው የሚወያዩባቸው ጠንካራ ተቋም ነው፡፡ ይህ ተቋም ምንም እንኳን በዋነኛነት በአማራ ክልልና ህዝብ ዘንድ ጥቅም ላይ የሚውል ቢሆንም በሌሎቹም ክልሎችና ህዝቦች በስፋት የሚገኝና የሚጠቀሙበት ነው፡፡ የጽዋ ማህበር የሴቶችና የወንዶች ተብሎ ለየብቻ የሚደራጅና የሚጠቀሙበት ሲሆን ለማህበራዊ ግንኙነትና ትስስር መጠናከር፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለማስወገድ እንዲሁም የሰላምና ደህንነት ችግሮችን በመከላከል ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ይነገራል (Tilahun and Moges 2021)። IIRR የተባለ ተቋም በጉዳዩ ላይ ያካሄደው አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው ማህበሩ በአባላት በሚመረጥ/በምትመረጥ ሙሴ አማካይነት ጠንካራ አመራርና አቅጣጫ መሠረት እንደሚመራ ሲያብራራ «ብልህና ልምድ ያላትን ሴት እንደ መሪያቸው እንድታገለግል ሙሴ አድርገው ይመርጧታል፡፡ ሙሴው/ዋ ክህሎት ያላት አደራዳሪ፣ የቡድን ውሳኔ ሰጪ እንዲሁም የማኅበረሰብ ሰላም አውራጅ መሆን አለበት/አለባት»። (2009:38) ሲል ይገልጻል፡፡ በመሆኑም የጽዋ ማህበር ማህበራዊ ትስስር አጠናካሪ ማህበረ-ባህላዊ ተቋም ከመሆኑም በላይ ዘርፈ-ብዙ እሴቶችና ፋይዳዎች ያሉት አሁንም ድረስ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኝ ጠንካራ ተቋም ነው፡፡

# ሰንበቴ

በተለይ በገጠራማ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባላት የሚመሠረት የማኅበር ዓይነት ነው፡፡ ስያሜው እንደሚያመለከትው በሳምንት አንድ ቀን ማለትም በዕለተ-ሰንበት (ሰንበት-ሰንበቴ) ከቅዳሴ በኋላ እያንዳንዱ አባል በተራ ማለትም በዙር በሚያዘጋጁት ጠበል ጠዲቅ (ምግብና መጠጥ፣ በአብዛኛው ቆሎ፣ ዳቦ፣ እና ጠላ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ እንጀራና ወጥ ጭምር) በማኅበሩ አባላት በማዘጋጀት የአብሮነት ጊዜ የሚያሳልፉበት የማኅበር ዓይነት ነው፡፡ ይህ የማኅበር መሠረታዊ መነሻው ሀይማኖታዊ ቢኾንም አባላትን በማኅበራዊ ሕይወት በማስተሳሰር፣ ማኅበራዊ ችግሮች፣ አለመግባባቶች፣ ወዘተ ሲከሰቱም አባላቱ በጋራ ችግሩን እንዲፈቱ እንደ ሌሎች ተቋማት (እንደ እድር) የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በሌላ በኩል ይህ ማኅበር የሚያካትተው የምግብና የመጠጥ አቅርቦት በአብዛኛው በቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ የሚካሄድ በመኾኑ የዕለት ጉርስ የሌላቸው ነዳያን ምግብና መጠጥ የሚያገኙበትን እድል በመፍጠር በአንጻሩ ያላቸው ለሌላቸው ማካፈል እንዲችሉ እድል የሚፈጥር የማኅበር ዓይነት ነው፡፡

# የክርስትና ልጅ/አባት

በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ወላጆች ሴት ልጃቸውን በ80ኛ ቀን ወንድ ልጃቸውን ደግሞ በ40ኛ ዕለት የማስጠመቅ (ክርስትና የማስነሳት) ሥርዓት ያለ ሲኾን ከዚህ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ጎን ለጎን አንድ ቤተሰብ ከሌላ ቤተሰብ ማኅበራዊ ትስስሩን የሚጠናከርበት ሥርዓት ነው፡፡ ይኸውም ክርስትና የሚያስነሱ ወላጆች ልጃቸውን በክርስትና አባትነት ወይም እናትነት (እንደ ልጁ ጾታ ሁኔታ፣ ሴት ልጅ ከኾነች የክርስና እናት፣ ወንድ ልጅ ከኾነ የክርስትና አባት) ለሌላ ቤተሰብ በመስጠት ሁለቱ ቤተሰቦች ጠንካራ ማኅበራዊ ተስስር ይፈጥሩበታል፡፡ በዚህ መንገድ ልጁ/ልጅቷ የክርስትና ልጅ ሲባል/ስትከል፣ ክርስትና የምታነሳዋ ሴት የክርስትና እናት፤ ክርስትና የሚያነሳው ወንድ ደግሞ የክርስትና አባት ይባላል፡፡ ይህ ሥርዓት በዋነኛነት ሃይማኖታዊ ቢኾንም ክርስትና የሚያስነሳው ቤተሰብ እና የሕጻኑ የክርስትና አባት ወይም እናት የሚኾነው

ቤተሰብ መካከል ማኅበራዊ ትስስር ይፈጥራል፡፡ እንደ ሥርዓቱ ከኾነ የክርስትና አባቱ ወይም እናቱ የክርስትና ልጃቸውን እንደ ልጃቸው በማየት አድጎ ለቁም ነገር እስከሚደርስ ድረስ ከወላጅ ያልተናነሰ እንክብካቤና ትኩረት እንዲሰጡ ይጠበቃል፡፡ ሁለቱ ቤተሰቦችም በደስታም ኾነ በመከራ ወቅት እንደ አንድ ቤተሰብ እንዲረዳዱና እንዲደጋገፉ እድል የሚፈጥር ሥርዓት ነው፡፡ ከማኅበራዊ ሀብት ትወራ አንጻር በአንድ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ጥምረት (bonding) መመስረቻ ቢኾንም በሃይማኖቱ የተለያዩ ማኅበራዊና ባህላዊ ዳራ (እንደ ብሔር) ያላቸው፣ በስጋ የማይዛመዱ ቤተሰቦችን በሃይማኖቱ ትውፊት ሰበብ እንደ ድልድይ (bridging) ማኅበራዊ ሀብት የማስተሳሰር ሚና ይጫወታል፡፡

# እድር

ይህ ሀገር በቀል ተቋም በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ማኅበረቦች በፈቃደኝነት የሚመሰርቱት ሲኾን ከቀዳሚ ዓላማዎቹ መካከል የሞተን መቅበር፣ ሀዘንተኛውን ደግሞ ማስተዛዘን ይገኙበታል፡፡ ተቋሙ የሚተዳደርበት ደንብ ማለትም የአባላት ግዴታዎችና መብቶች፣ እንደ መዋቅር ደግሞ ሊቀመንበር፣ ገንዘብ ሰብሳቢ ወይም ገንዘብ ያዥ ወዘተ ያለው ከማኅበራዊ ሀብት አንጻር መተማመን፣ መደጋገፍ፣ የጋራ ግንዛቤና ዓላማ ያሉት፣ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች፣ በከተማም ኾነ በገጠር እድሜ ጠገብ ተቋም ነው ማለት ይቻላል፡፡ እድር በአብዛኛው የእድሩን አባል ወይም የአባሉን ዘመድ ቀብር ከማስፈጸም እና አባሉን ከማጽናናት ጋር ቢቆራኝም ተቋሙ ከነዚህ ተግባራት በዘለለ ሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መደጋገፍ የሚታይበት ነው፡፡ ከሞት በዘለለ አባላት የተለያዩ አደጋዎችና እክሎች ሲገጥሟቸው የመተጋገዝ፣ በደስታም ለምሳሌ አባሉ ሠርግና መሰል ኩነቶች ሲኖሩት የእድር አባላት ትብብር አይለየውም፡፡ በተጨማሪም እድር ዜጎች የማኅበራዊ ሀብት እሴቶች መካከል መዋጮን እና ተሳትፎን በሚገባ የሚተገበሩበት ተቋም ነው፡፡ በአጠቃላይ እድር በሥነልቡናዊ ፋይዳው ያዘኑ የሚጽናኑበት፣ ከማኅበራዊ ሕይወት አንጻር አብሮነት፣ መተባበርና መደጋገፍን መሠረት ያደረገ ተስስር የሚፈጠርበት፣ ብሎም የሕይወት መድኅን (ኢንሹራንስ) ባልዳበረበት ወይም ጭራሽ በሌለበት ማኅበረሰብ ውስጥ እንደ ሕይወት መድኅን በማገልገል እስከዛሬ ድረስ በሀገራችን በከተማም ኾነ በገጠር ከፍተኛ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እየተጫወተ ያለ ታላቅ ተቋም ነው፡፡

# እቁብ

እቁብ ከባህላዊ የፋይናንስ ተቋማት መካከል ተጠቃሽ ሲኾን ግለሰቦችን ቁጠባን፣ መደጋገፍን እና መተማመንን የሚያዳብሩበት ቋሚ ያልኾነ ተቋም ነው፡፡ ቋሚ ያልኾነ ማለት በአንድ ወቅት የተጀመረ እቁብ እያንዳንዱ አባል እኩል «የሚጥለው» የገንዘብ መጠን በዙር ለሁሉም አባል በተራ ከደረሰ በኋላ የሚያበቃ የተቋም ዓይነት ነው፡፡ ይኹንና እነዚሁ አባላት ወይም ሌሎች ተጨምረው ወይም ከነባሮቹ ተቀንሰው ሌላ እቁብ ሊጀመር ይችላል፡፡ እቁብ የመጀመሪያውና የመጨረሻው አባል «የሚበሉት» (የሚያገኙት) ገንዘብ ከዋጋ ግሽበትና መሰል ጉዳዮች ጋር በማያያዝ ተመሳሳይ አለመኾኑን፣ የአባላቱ ስብስብ ቋሚ አለመኾኑን (ad hoc መኾኑን) ወዘተ በመጥቀስ አንዳንድ ምሁራን የተቋሙን ደካማ ጎን ያነሳሉ፡፡ ይኹንና እቁብ ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ባሻገር የማኅበራዊ ሀብት ምንጭነቱ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ በቅድሚያ እቁብ መደበኛው የፋይናንስ ሥርዓትና ባንኮች ተደራሽ ባልሆኑባቸው አከባቢዎች፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ላይ ለተሰማሩ፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች በኢመደበኛ መንገድ ገንዘብ እንዲቆጥቡ የሚያስችል ተቋም ነው፡፡ ከማኅበራዊ ሀብት አንጻር ጉልህ የኾነው የእቁብ ባሕርይ ግለሰቦች ኢኮኖሚያዊ ችግር፣ ኪሳራ ወዘተ ሲገጥማቸው አለያም አንዳች ዓላማ ማሳካት ሲነሳሱ ለግለሰቡ ቅርበት ያላቸው ሰዎች በመሰባበስ የሚጣለውን ገንዘብ በመወሰን የመጀመሪያውን ዙር ለዚህ ግለሰብ የሚሰጡት ልማድ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ሚናው ተጠቃሽ ነው፡፡ በዚህ ሂደት መጀመሪያ እና መጨረሻ «በሚበሉት» ግለሰቦች መካከል በዋጋ ግሽበት ወይም ከጊዜ አንጻር በሚኖረው የገንዘብ እሴት ልዩነት ረገድ የሚነሳው ልዩነት ለማኅበራዊ ሕይወት የሚከፈል ዋጋ መኾኑን ልብ ይሏል፡፡ ከዚህ ባሻገር አባላት የሚያሳዩት መተማመን ደግሞ የማኅበራዊ ሀብቱ ዋነኛ አስኳል እሴት ነው ማለት ይቻላል፡፡

# የንሥሐ አባት

በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ሃይማኖቱ አንድ ምእመን ወይም ቤተሰብ የንስሐ አባት እንዲኖረው ያስገድዳል፡፡ እኚህ አባት (ካህን) ለግለሰቡ ወይም ለቤተሰቡ ሃይማኖታዊ መርሆዎችን፣ ክርስቲያናዊ እሴቶችንሥነ-ምግባርንና ግብረገብነትን የማስተማር ግዴታ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የንስሐ ልጆቻቸው ልዩ፣ ልዩ ሃይማኖታዊ እና እንደ ሰርግ፣ ቀለበት፣ ጽዋ ማኅበር ወዘተ ያሉ ማኅበራዊ ኩነቶች ሲኖሯቸው እኚህ አባት በቤተሰቡ መሃል በመገኘት ቡራኬ (ጸሎት) ያደርሳሉ (Flemmen & Zenebe 2016፣ ገጽ 11)፡፡ ይህ ሥርዓት ከላይ እንደተጠቀሰው ሃይማኖታዊ ቢኾንም ከሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ፋይዳ ባሻገር በቤተሰብ አባላት መካከል አለመግባባት ሲከሰት፣ በባልና ሚስት መካከል ግጭት ሲኖር፣ ከቤተሰብ ውጪም በተለይ ተመሳሳይ ሃይማኖት ካለቸው ግለሰቦች ጋር አለመግባባት ሲፈጠር የንስሐ አባት በአብዛኛው በቀዳሚነት ችግሩን (አንዳንዴም በሚስጥር) የሚካፈሉ፣ ጉዳዩ ወደሽማግሌ ከመሄዱ በፊት በተግሳጽ፣ በምክርና በጸሎት ለመፍታት የሚሞክሩ በመሆናቸው በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ የሚጫወተው ማኅበራዊ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

# የፈረስ አባት/ፈሪሴ ታበላ

በአዊ ዞን የሚገኘው ይህ «የፈረስ አባት/ፈሪሴ ታበላ/» የሚል ስያሜ ያለው ተቋም በቀጥታ የሚቆራኘው «ከሰባት ቤት አገው የፈረሰኞች ማህበር» ጋር ነው፡፡ በጥንካሬውና በግዙፍነቱ በስፋት የሚነገርለት የሰባት ቤት አገው የፈረሰኞች ማህበር የተመሰረተው በ1933 ዓ.ም ነው፡፡ አመሰራረቱም ከጣሊያን ወረራ ጋር የተያያዘ መሆኑን ቃላዊ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ እንደ አፋዊ መረጃዎች ምስክርነት ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት የጠላት ጥቃት በማየሉ የአዊ ህዝብ ቤተክርስቲያን ሂዶ በመጸለይ ላይ እንዳለ ቅዱስ ጊዮርጊስ በፈረስ እየጋለበና እየተዋጋ ጠላት ተቆጣጥሮት የነበረውን ቦታ ሲያስለቅቅ ይገለጽለታል፡፡ከዚያ ወዲህ «የጊርጊስ ፈረሰኞች ማህበር» በሚል መጠሪያ ለመጀመሪ ጊዜ ተመሰረተ፡፡ ከዚያም እየተጠናከረ መጥቶ «የሰባት ቤት አገው የፈረሰኞች ማህበር» የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ይገኛል፡፡ ማህበሩ በመጀመሪያ ሲጠነሰስ ዓላማው ጣሊያንን በፈረስ ተዋግቶ ከአገራችን ከማባረር ያለፈ አልነበረም፡፡ ከጠላት መባረር በኋላ ግን በርካታ ሰናይ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህም መካከል አንደኛው በዓመታዊ የንግስ በዓላት ላይ መሳተፍ ሲሆን ዋንኛው ደግሞ በህብረተሰቡ አባላት መካከል የሚፈጠሩ ማናቸውንም ዓይነት ግጭቶች ወይም አለመግባባቶች በባህላዊ መንገድ በመፍታት፤ የሚካሰውን በማስካስ፤የህብረተሰቡን ሰላም የማስጠበቅ ተግባር ያከናውናል፡፡ ይህ ሃብት አሁንም በስፋት እየተከወነ ይገኛል፡፡ እንዲያውም የመንግስትና የድጋፍ ሰጪ አካላት በመተባበር በዓሉ በየዓመቱ በድምቀት በመከበር ላይ ይገኛል፡፡ በማህበሩ የተጣላ ካለ የሚታረቅበት፤ሀብት ንብረት የተሰረቀበትም ካለ የሚያስመልስበት፤ አባቶች ያቆዩትን ታሪክ ለትውልድ የማስተላለፊያ መድረክ በመሆኑ ማህበረ-ባህላዊ ሚናው የጎላ ነው፡፡ በህዝቡ የተጣላ ካለ የሚታረቅበት፤ በህዝቡ ዘንድ የጠበቀ የወንድማማችነት ስሜትን፤ የእርስበርስ መረዳዳትንና መተሳሰብን የሚፈጥር በመሆኑ ከሰላም ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት አለው፡፡

# የላም ራስ

ከአዊ ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህና የአስተዳደር ተቋማት አንዱ «የላም ራስ» ነው፡፡ የላም ራስ በአንድ አካባቢ ወይም ጎጥ ተሰባስበው የሚኖሩ አርሶ አደሮች ከብቶቻቸውን በጋራ ለማስጠበቅና የግጦሽ መሬታቸውን ለማሁራት/ለማዳበር/፤ይህንንም በተደራጀ አኳኋን ማከናወን እንዲችሉ የሚመርጡት ሰው ነው፡፡ በላም ራስ የሚገለገሉ ስፍራዎች በብሔረሰቡ ውስጥ ህዝቡ ተሰብስቦ የሚኖርባቸው ሰፋፊ ጎጦች ናቸው፡፡ የላም ራሱ የሚመረጠው ከሰው ጋር በመግባባት ችሎታው በቅንነቱና በታጋሽነቱ ሌሎች አባላትን ለማስተባበርና ሀላፊነቱን ለመወጣት ባለው ብቃትና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ባለው ተደማጭነት ነው፡፡ አንድ የላምራስ ከ10-20 የሚደርሱ አባላት ሊኖሩት ይችላል፡፡ እያንዳንዱ አባል በላም ራሱ አማካኝነት የሚጣልበትን ሀላፊነትና ግዴታ መወጣት ይኖርበታል፡፡ በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከብቶቻቸውን አሰባስበው በጋራ የሚያስጠብቁና የሚያሳድሩ የአባዎራዎች ስብስብ «ጉዲ» ይባላል፡፡ «ጉዲ» የአዊኘ ቃል ሲሆን ትርጉሙም «መንደር» ወይም «ጎጥ» ማለት ነው፡፡ በአንድ መንደር በአንድ ላም ራስ ስር ያሉ አርሶአደሮች የአንድ «ጉዲ» አባላት ይሆናሉ፡፡ የላም ራስ ሆኖ የተመረጠው ሰው አዳዲስ ጎጆ ወጪ ወጣቶች ወደማኅበሩ ለመግባት ሲያመለክቱ ጥያቄያቸውን ተቀብሎ የማስተናገድ ተግባራትን ያከናውናል፡፡ እንዲሁም በየዓመቱ ሀምሌ 8 ቀን (ኪሮስ ዕለት) «ችፌ» (ዕርድ) እንዲደረግና በነዋሪዎች መካከል የተከሰቱ ግጭቶችን የመፍታት ሃላፊነት ተግባር ያከናውናል፡፡ በነዋሪዎች አስተያየት «የላምራስ» በነዋሪዎች መካከል ያሉ አፈንጋጮችን ይቀጣል፡፡ ወይንም ከማኅበሩ ያሰናብታል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ግጭት ውስጥ ገብተው አልታረቅም ብለው የሚያስቸግሩ አባላትን ከማኅበሩ እንዲገለሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡ አንድ የላም ራስ ጥፋት ሲገኝበት የጉዲው አባላት ከኃላፊነቱ ሊያስነሱት ይችላሉ፡፡ የአንድ የላም ራስ የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ነው፡፡ ይህ ሃብት አሁንም በስፋት እየተከወነ ይገኛል፡፡ በየሁለት ዓመቱ በሚደረገው የዙር ምርጫም ማኅበረሰቡን እያገለገለ ይገኛል፡፡ በያመቱ በሚከናወነው «ችፌ ( ዕርድ)»ና ግጭቶች ሲከሰቱ የተጣላ ካለ የሚታረቅበት፤ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር የሚከናወንበት በመሆኑ ማኅበረ-ባህላዊ ሚናው የጎላ ነው፡፡ በነዋሪዎች መካከል የተከሰቱ ግጭቶች የሚፈቱበት፤ አፈንጋጮች የሚቀጡበት፤ በተለያዩ ምክንያቶች ግጭት ውስጥ ገብተው አልታረቅም ብለው የሚያስቸግሩ አባላትን ከማኅበሩ እንዲገለሉ በማድረግ መቀጣጫ ስለሚያደርግ፤ መደበኛውን የፍትህ አሰጣጥ በመደገፍ ረገድም ከፍተኛ ሚና ስላለው ከሰላም ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት አለው፡፡

# የውሃ አባት (አኹታብላ)

ከአዊ ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህና የአስተዳደር ተቋማት አንዱ «የውሃ አባት» ነው፡፡ የውሃ አባት በሚል መጠሪያ ሹመት የሚሰጠው ውሃ ገብ በሆኑ (በመስኖ በሚለሙ) አካባቢዎች ነው፡፡ የመስኖ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ውሃውን በፍትሐዊነትና በአግባቡ እንዲጠቀም የማድረግ ሀላፊነት አለበት፡፡ በአባላቱ መካከል በውሀ አጠቃቀምና መሰል ሰበቦች ግጭት ሲፈጠር የመፍታት ሃላፊነት የእርሱ ነው፡፡ እንደ ላም ራስ ሁሉ የውሀ አባትም የሚሾመው በማስተዳደርና በማስተባበር ችሎታው በብልሀቱ ፤በህብረተሰቡ ዘንድ ባለው ቦታና ተሰሚነት ነው፡፡ የውሀ አባት ወንዝ መገደብ በሚያስፈልግበት ጊዜ ህዝብ በተሰበሰበበት በቤተክርስቲያን ቁሞ ይናገራል፡፡ ወንዙ (ምንጩ) ከተገደበ በኋላ ውሃው በመጀመሪያ ለውሃ አባቱ ይሰጣል፡፡ ከዚያም ተራ በተራ ለሌላው ሰው ይዳረሳል፡፡ ይህም በአብዛኛው የሚከናወነው በጥቅምት ወር ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በቀረበው እንደተመለከትነው የዳኝነት አካላቱ መዋቅራዊ ቅርጽ ከሞላ ጎደል ይህን ይመስላል፡፡ይህ ሃብት አሁንም በስፋት እየተከወነ ሲኾን የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ፍትሃዊነትን በሚያሟላ መንገድ መከናወኑ፤ ወንዙ ሲገደብም በህዝብ ተሳትፎ መሆኑ፤ ባህላዊ የሹመት አሰጣጡ ሳይዛነፍ መካሄዱ ማህበረ-ባህላዊ ሚናው የጎላ ነው፡፡ በአብዛኛው ውሃ ገብ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ዘንድ ከግጭት መንስኤዎች መካከል ዋንኛው በውሃ አጠቃቀምና መሰል ሰበቦች መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ እረገድ ግጭት ሲፈጠር የመፍታት ሂደት ስለሚከናወን፤ መደበኛውን የፍትህ አሰጣጥ በመደገፍ ረገድም ከፍተኛ ሚና ስላለው ከሰላም ጋር ያለው ቁርኝት ከፍተኛ ነው፡፡

# ሃላሌ

በሲዳማ ማኅበረሰብ ዘንድ ትልቅ ስፍራ ከሚሰጣቸው ባህላዊ እሴቶች መካከል  አንዱ ሀላሌ ሲሆን ሀላሌ ማለት “እውነት” ማለት ነው፡፡ ማኅበረሰቡ በሂደት ሀላሌን በእውነት ወደ መኖር መርህ ያሳደገው ሲሆን ይህም የሰዎችን ሀቅ ያለ ውሸት፣ ያለማዳላት፣ ለራስ ብቻ ከማለት ይልቅ ሌሎችንም ተሳቢ ማድረግና በእውነት ህሊና መመላለስን ያካተተ ሰፋ ያለ እሳቤ መሆን ችሏል፡፡ የሀላሌ መርህ የሰዎችን፣ የእንስሳትን በአጠቃላይ የተፈጥሮን መብት  ከማክበርና ከማስከበር ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ በሁሉም ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ በስፋት በሀላሌ በመመላለስ ማህበረሰቡ እርስ በርስ ያለዉን ትስስር እንዲያጠናክር ሚናዉ የጎላ ነዉ። በአሁኑ ሰዓት ሀላሌ በሲዳማ ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ ያለውና እየተተገበረ ያለ ሀገር በቀል ዕውቀት ነው፡፡ ሀላሌ (Halaale) በማህበረሰቡ መካከል እርስ በርስ አመኔታን በመጨመር ለሰላምና ለመልካም ጉርብትናም ሆነ ለመልካም የዕለት ተዕለት ተግባር ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል ፡፡

# ያካ

ያካ የሲዳማ ማህበረሰብን ውስጣዊ መስተጋብር የሚያጠናክርና ከፍተኛ ማህበራዊ ፋይዳ ያለው እሴት ነው፡፡ ያካ ወንዶች በሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ገደብ የጣሰና አስነዋሪ ድርጊት ሴቶች ቢጋራ በመሆን ለማውገዝና ለመቅጣት የሚገለገሉበት የተቃውሞ ሥርዓት ነው፡፡ የሚመራውም “ቃሪቾ” (Qaricho) በተባለች የሴቶች መሪ አማካኝነት ሲሆን በትዳር ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ሴቶች የሚያቅፍ ነው፡፡ እነዚህ የሲዳማ ሴቶች በያካ ተቋም ስር በመሆን ሲቆ (Siqoo) የተባለውን ዱላ በመጠቀም መብታቸውን/ክብራቸውን ለማስጠበቅ ይሰራሉ (IIRR 2009)፡፡ ዓለም እንደ ዛሬው ባልሰለጠነበት ጊዜ የሲዳማ ሴቶች መብታቸውን የሚያስከብሩበትና  ያቆዩአቸውን ሰላምና ደህንነት የሚጠብቁበት ሥርዓት በመሆኑ ሴቶች ሰላማቸውና ደህንነታቸው ከቤት ጀምሮ ሲከበር እንደሀገር ሰላም መሆን ስለሚቻል የሥርዓቱ ማህበራዊ ፋይዳው ከፍተኛ እንደሆነ ይነገራል፡፡ የያካ ሥርዓት በአሁኑ ጊዜ ተዳክሟል ማለት ይቻላል፡፡

# ሉዋ

ሉዋ የሲዳማ ብሔር አባላት የሆኑ ወንዶች ከየጐሳቸው ተወጣጥተውና በትውልድ ዑደት ተደራጅተው በማህበረሰቡ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ የላቀ ተሳትፎ ለማድረግ የሚሰበሰቡት ባህላዊ ተቋም ነው፡፡ የሉዋ ሥርዓት በአባልነት የሚያቅፋቸው ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ጥንካሬን፣ አርአያነትን፣ አስታራቂነትን፣ ለሰላም መቆምን ወዘተ ያሉ በጐ ምግባራትን እንዲቀስሙ ያደርጋል፡፡ ሕዝቡን ከውጪ ጠላት ወረራ የመከላከል ተግባር በሉዋ አባላት ይመራል፡፡ በአንድ የሉዋ ስልጣን ዘመን በማህበረሰቡ መካከል ሰላም፣ ደህንነትና አንድነት እንዲሰፍን የሉዋ ሥርዓት መሪዎች በተለይም ጋዳና “Gadaana” ከፍተኛ ሃላፊነት ይጣልበታል፡፡ የሉዋ ስርዓት በተለያዩ ማኅበራዊ ደረጃዎች የሚከናወን ሲሆን በየስምንት ዓመቱ የሚወራረስ ወይም የሚዞር የስልጣን እርከኖች አሉት፡፡ በተጨማሪም ይህ ስርዓት በተለያዩ ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ማህበረሰቡን የሚወክሉ አዋቂ ሰዎች የሚወጡበት ተቋም በመሆኑ ለሰላም ያለዉ ሚና ከፍተኛ ነዉ፡፡ የሲዳማ ሉዋ ሥርዓት ከኦሮሞ የገዳ ስርኣት ጋር በእጅጉ የተቀራረበ አወቃቀርና እሳቤ ያለው ተቋም እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል፡፡ የሁን እንጂ በአሁኑ ሰዓት ይህ ስርዓት እየተዳከመና እየቀዘቀዘ የመጣ ነዉ ለማለት ይቻላል፡፡

# ፊቼ ጫምባላላ

ፊቼ የሲዳማ ብሔር የዘመን መለወጫ ክብረ በዓል ሲሆን በርካታ ዕሴቶችን በዉስጡ ይዟል፡፡ ከእነዚህ ዕሴቶች መካከል አንደኛው የተጣላ የሚታረቅበት፣ የተለያየ ሚገናኝበትና አዲስ ተስፋና አዲስ የሰላም ርዕይ የሚሰነቅበት ይገኝበታል፡፡ በመሆኑም በፊቼ እንደግለሰብም ሆነ እንደ ማኅበረሰብ የተጣላ፣ ቂምና ቁርሾ ተይዞ መሻገር ስለማይቻል ሁሉም ማለት በሚቻል ደረጃ ዕርቅ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በበዓሉ አከባበር ጊዜየተጣሉ ሰዎች ሳይታረቁ ማለፍ የማኅበረሰቡን ዕሴት እንደ አለማክበር ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም የፍቼ ጨምባላላ በዉስጡ በያዛቸዉ በርካታ ዕሴቶች ምክንያት ለሰላምና ለሀገር ግንባታ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛነው፡፡ በአሁኑ ጊዜም ፊቼ ጨምባላላ ከሲዳማ ማኅበረሰብም አልፎ የዓለም ቅርስ በመሆን በዩኔስኮ ከማይዳሰሱ የሰው ልጆች ወካይ ቅርስ አንዱ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በዓሉ ከአዲስ ዓመት ዘመን መለወጫነት ከሲዳማ ብሔር ማንነት መገለጫነቱ ባሻገር በበዓሉ ግለሰብ ከግለሰብ፣ ቤተሰብ ከቤተሰብ፣ ጎሳ ከጎሳ ብሎም ሰውና ተፈጥሮ እርቅ የሚያወርዱበት ስልሆነ ለሰላም ግንባታ፣ ለአብሮነትና ወንድማማችነት የመሳሰሉ እሴቶች ዳግም የሚታደስበት ክብረ በዓል ነው ማለት ይቻላል። አከባበሩም በምርቃት፣በመልካም ምኞት፣ በጸሎትና በይቅርታ የታጀበ ነው። በአጭሩ የፊቼ ጨምበላላ በዓል የሰላም፣ የፍቅር፣ የአንድነት በዓል ሲኾን በአሁኑ ሰዓት በከተማም ሆነ በገጠር የሲዳማ ሕዝብ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የሚጠቀመውና ያልተሸረሸረ የባህል እሴት ነው።

# ካማኬሳ

በደ/ም/ኢ/ሕክልል በየም ብሄረሰብ መስከረም 14 ቀኑ «ካማ ኬሳ» ይባላል፡፡ ‹ከማ› ማለት ትርጉሙ በብሐረሰቡ ቋንቋ ማር ማለት ሲሆን «ኬሳ» ማለት ደግሞ መውጣት እንደማለት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ቀን በቤተሰብ ውስጥም ሆነ በዘመድ አዝማድ መካከል የተፈጠረ ቅራኔና የሰነበተ ቂም ካለ በሽማግሌዎች አማካይነት የእርቀ ሰላም ስርዓት የሚፈፀምበት ቀን ነው፡፡ይህ «የካማ ኬሳ» ሥርዓት የሚደረግበት ዋነኛ ምክንያት ቂም ይዞ ወደ አዲሱ ዓመት መሻገር የተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶችን ሊፈጥር ይችላል ተብሎ ስለሚታመን በመካከላቸው ቅራኔ ያላቸው ግለሰቦች በሽማግሌዎች ፊት ቀርበው ይቅር ይባባላሉ፡፡ በመቀጠልም ይቅርታ ለመጠያየቃቸው ተምሳሌት የሚሆን ከሁለቱ ወገን መስዋዕት የሚሆን ማር ይቀርባል፡፡ የቀረበላቸውን ማር በቅጠል ይዘውበጎሳ መሪያቸው ፊት ቀርበው እንዲቀምሱ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም «ሹማ»ቦርዴን በአንድ ዋንጫ በጋራ እንዲጠጡ ይደረጋል፡፡ ይህ የሚደረግበት ምክንያት ከአሁን በኋላ ታርቀናል፤በፍቅር እንኖራለን የሚል ተምሳሌት ስላለው ነው፡፡ በዚህ መልክ ሁሉም በየአካባቢው በበዓሉ ዋዜማ ዕለት የእርቅ ስርዓት በመፈፀም በአዲስ መንፈስ በደስታ በዓሉን በጋራ ያከብራሉ፡፡ይህ እሴት ለዘላቂ ሰላም በማውረድ ግንባታ ከፍተኛ ቦታ ያለው  በመሆኑ በብሔረሰቡ ዘንድ እስከዛሬ  ያለማቋረጥ እርቀ-ሰላም ማውረዱ ረገድ ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት የሚያገለግል እሴት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሥርዓት ተጠናክሮ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ይህ ባህላዊ ሀብት በማህበረሰቡ ወስጥ አንድነትን በማጠናከርና ሰላምን በማስፈን ፤ ማህበረሰቡ ሰላማዊ ህይወት እንዲኖረው በማድረግ እንዲሁም ባህሉን ከማሳደግ አንጻር ጉልህ ሚና አለው፡፡

# አፊኒ

በሲዳማ ባህል መሠረት ሰዎች ሲነጋገሩ “አፊኒ” በማለት ማሳወቅ ግዴታ ሲሆን ጥሬ ትርጉሙም “ሰማቹ ወይ ሰማችሁ ወይ” ማለት ነው፡፡ አፊኒ ለግለሰብም ሆነ በቡድን ተሰብስበው ላሉ አልያም ከአጠገቡለሚገኝ ሌላ ሰውሀሳብን ለማንሸራሸርና ለማሰባሰብ የሚጠቀሙበት ንግግር ነው፡፡ በውይይትና በውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥም ሌሎችን ለማሳተፍና ተበዳዩ ግለሰብም ሆነ ቡድን ነገሩን ሌሎች እንዲያውቁለት የማድረጊያ ዘዴ ነው፡፡ በሌላ በኩል የተጣላ ሰዉ አፊኒ ሳይል እርምጃ የወሰደ እንደሆነ በባህሉ መሠረት ሴራ(seera) ማህበራዊ ገደብ (social sanction) ይጣልበታል፡፡ አፊኒ እውነትን ከመፈለግና ከፍትህ አሰጣጥ ስርዓት ጋር በእጅጉ የተሳሰረነው፡፡ ስርዓቱ ለሲዳማ ማኅበረሰብ ቁልፍ ሲሆን ከዕለት ተዕለት ተግባራት መከወኛዎች እንደ አንዱ መቁጠር ይቻላል፡፡ አንድ ግለሰብ ከሰዎች መሀል ቢጠራህ አብረውህ ያሉትን “አፊኒ” ሳትል አትነሣም፤ ምግብ ቀርቦ በዙሪያህ ያሉ ሰዎችን “አፊኒ” ሳትል እጅህን ምግቡ ጋርአትዘረጋም፤እንዲሁም አንድ ግለሰብም ሆነ ቡድን የአንተ የሆነን አልያም የማህበረሰቡ ዕሴት ላይ ጉዳት ሲያደርስ “አፊኒ” ሳትል አፀፋ አትመልስም፡፡ የአፊኒ ሥርዓት ለእርቅ መከዎወኛ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የዕለትተዕለት ተግባራት ዉስጥ ይተገበራል፡፡የአፊኒ ሥርዓት በአሁኑ ጊዜ በሲዳማ አካባቢ በከፍተኛ ደረጃ እየተተገበረ ያለ ሀገር በቀል ዕሴት ነው፡፡ በመሆኑም በሰላም ወቶ ለመግባት እንዲሁም ከሰዎች ጋር ተግባብቶ ለመኖር የአፊኒ ስርዓት ፋይዳዉ የጎላ ነዉ፡፡

# መድኣ

መድአ የአፋር ህዝብ ማኅበራዊ፣ መንፈሳዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ እንዲሁም የፍትህና የዳኝነት ጉዳዮችየሚቀርቡበትናስርዓት የሚይዙበት የባህል ህግ ነው፡፡ ይህ የባህል ህግ በሁሉምዓይነት የህብረተሰብ ችግሮች ላይ መፍትሄ የሚሰጡ ዳኞች፣ ባለስልጣኖችና የጎሳ መሪዎች በሚሰጡት ውሳኔ መሠረት ፀጥታንለማስከበርና ወንጀልንለመከላከል ያስችላል፡፡ መድአ ከማንኛውምአካባቢ በተሻለያልተሸረሸረ፣ አሁንም በስራ ላይ ያለና ህዝቡ የሚያምንበት ስርዓት ነዉ ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ባህላዊ የህግ ስርዓቱ የክልሉን ሰላም ከመጠበቅና በአካባቢው ለሚፈጠሩ ማንኛውም ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች መፍትሄ ይሰጣል፡፡

# ዳጉ

የአፋር ህዝብ የመረጃ አቀባበል ስርዓት ዳጉ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ማንኛውም ሰው በመንገድ ላይ ሲገናኝ ወይንም እንግዳ ሰው ሲመጣ ዳጉ ሳይደረግ መለያየት አይቻልም፡፡ መንገደኞች የሰላምታ፣ የደስታና የመልካም ምኞት ልውውጥ አድርገው ወደ መንገዳቸው ይሄዳሉ፡፡ በዚህ መሠረት በመጀመሪያ ከታየውና ከተሰማው መረጃ በተጨማሪ ከተለያዩ ሰዎች የተገኘው መረጃ እየተጨመረ የብዙ መረጃ ባለቤት ይሆናሉ፡፡ ይህ መረጃና እውቀት ለኑሮና ለህይወት ትልቅ መሳሪያ ከመሆኑ ባለፈ ለሀገርና የህዝብ ደህንነት ለመጠበቅ አይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ በሌላ በኩል ዳጉ የመረጃ ስርዓት ማንኛውም ፓለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ወደ ህበረተሰቡ እንዲወርዱ የማድረግ አቅም አለው፡፡ የዳጉ የመረጃ ስርዓት አስፈላጊ የሚባሉ መረጃዎችን በእውነት ላይ በመመስረት ልውውጥ ማድረግ ስለሚያስችል ባህላዊና ማኅበራዊ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ የዚህ የመረጃ አቀባበል ስርዓት በአሁን ስዓት እያደገና በይበልጥ እየተጠናከረ ያለ በመሆኑየህብረተሰቡ ምልክት ሆኗል፡፡ በመጨረሻም ዳጉ ሰላም ከማስፈና፣ የህዝቦችንና የሀገር ደህንነትን ከመጠበቅ አንፃር የመረጃ ልውውጥ ሰለሚከናወን ከሁሉም የበለጠ የወሳኝነት ሚና ይጨወታል፡፡

# አዳኘ የባሊ ቅናት ሴራ

በጠንካራ አስተሳሰብና ፍትሃዊነት ላይ የተመሰረተው/የጎለበተው/ የስልጤ ማህበረሰብ የባህላዊ ዳኝነት ስርዓት የረቀቁና የጎለበቱ መመሪያና ህገ-ደንቦች የነበሩት በመሆኑ ምክንያት ለዘመናት በህዝቡ ዘንድ ሰላምን ለማስከበር እንዲሁም ትክክለኛ ፍትህን ለማስፈንከፍተኛ አስተዋፅኦ ሲያበረክት ቆይቷል፡፡ አዳኘ የባሊቅናት ሴራ የባህላዊ የሽምግልና ስርአት ሲሆን ስልጤዎች ከቅድመ አያቶቻቸዉ ከወረሷቸዉ እሴቶች መካከል ይህ አንዱና ዋነኛው ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህ እሴት ለመቻቻልና ለሰላም እንዲሁም ለሁለንተናዊ አኗኗር ቀዳሚ አማራጭ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን ስለሚያስወግድ ከሰላም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡

# ክፍል ሁለት

# በድኅረ-ግጭት ወቅት ለሰላምና እርቅ ሚና የሚጫወቱ ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶች

# መግቢያ

በሀገራችን የተለያዩ ማኅበረሰቦች በውስጣቸውም ኾኑ ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር አለመግባባቶች እና ግጭቶች ሲያጋጥሟቸው ችግሮቹን ፈትቶ፣ እርቀ-ሰላም በማውረድ ማኅበራዊ ሕይወት ወደቀድሞ ኹኔታ እንዲመለስ የሚስችሉባቸው ልዩ፣ ልዩ ብልሃቶችንና እሴቶችን አምቀው የያዙ ተቋማትና ሥርዓቶች አሏቸው፡፡

# ሽምግልና

ይህ ሥርዓት ስያሜው ከቋንቋ ቋንቋ ወይም ከአከባቢ አከባቢ ይለያይ እንጂ በሀገራችን የተለያዩ ማኅበረሰቦች ዘንድ በተለይ ደግሞ በአማራ ክልል ሕዝቦች ዘንድ የሚተገበር፣ በማንኛዉም ጉዳይ ላይ የሚከሰቱ ግጭቶችና አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያገለግል ተቋም ነው፡፡ ግጭት ወይም አለመግባባት ሲከሰት ወዲያውኑ ሳይውልና ሳያድር፣ ስር ሳይሰድና ማኅበራዊ ህይወትን ወደሚያውክ ደረጃ ሳይደርስ መፈታት እንዳለበት ይታመናል፡፡ ግጭቱን መፍታትና ሰላማዊ ኑሮን መጠበቅ የማኅበሩ አባላት የነፍስወከፍ፤ የወል ሃላፊነትና ግዴታ ቢሆንም ራሱን የቻለ ባህላዊ የዳኝነት ስርአት አለ፡፡ ስለሆነም የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች በተለያዩ ግጭት ውስጥ ሲገቡ በባህላዊ ሽምግልና ግጭቱ ይፈታል፡ ፡ከቀላል እስከ ከባድ ግጭቶችን በማስወገድ እርቅ ያወርዳሉ፡፡ ሰላም ያሰፍናሉ፡፡ በእነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች በባህላዊ ሽምግልናው ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጠው የሰው ነፍስ ሲጠፋ ነው፡፡ የባህላዊ ሽምግልና ሂደቱ ከሁለቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች በአንደኛው ጥያቄ ወይም ስለማህበራቸው ደህንነት በሚቆረቆሩና ከጉዳዩ ጋር ምንም አይነት አግባብ በሌላቸው ሰዎች አሳሳቢነት ሊጀመር ይችላል፡፡ በተጠቃሚው ህዝብ ማበረሰባዊ ስነልቦናና እሴት ሽምግልና ከፍተኛ ግምት፤ ተቀባይነትና ክብር የሚሰጠው ተቋም ነው፡፡ ብይኑ ፍትሐዊ ዉሳኔው ገዥና የማይጣስ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በሠጠው በዚህና ሌሎች ከፍተኛ ብቃተ-ወንች ሽምግልና አጥፊን ይቀጣል፡፡ተበዳይ እንዲካስ ያደርጋል፡፡ፍጹም እርቅና ሰላም ያውጃል፤ወይም ማህበረሰባዊ ተአቅቦና መገለል ይጥላል፡፡የዚህ የሽምግልና ስርአት የሽማግሌዎች ቁጥር ከ7-12 ሲሆን ለነፍስ ግድያ ከሆነ ከዘጠኝ ዝቅ አይልም፡፡ የሽማግሌዎች መምረጫ መስፈርት በእድሜ አዛውንት መሆን፣ ጾታ በተመለከተ ወንድና ሴቶች፣ ማኅበራዊ ደረጃቸው ግን አይለይም፡፡ባህላዊ ሽምግልናው አሁንም በስፋት በመከወን ላይ ይገኛል፡፡ ከዘመናዊ ፍርድ ቤት ጋርም በመተባበር በሰፊው እየተሰራበት ነው፡፡ ይህ ማህበራዊ ሃብት በህዝቡ ዘንድያላውተቀባይነት፤ ተደራሽነቱና ትክክለኛ ፍርድን ከመስጠትአንፃር ሲታይ፤ እንዲሁም በእርቁ ስነስርአት ወቅት የሚቀርቡ ቁሳቆሶች/መስቀል፤ ጠመንጃ…/ በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ እምነት ስለሚጣልባቸው ሃብቱ ማህበረ-ባህላዊ ሚናው የጎላ ነው፡፡ማህበረሰቡከእራሱ አብራክየወለደው ይህ ማህበራዊ ሃብት ዋንኛው ተግባሩ የተፈጠረውን አለመግባባት አስወግዶ ሰላምና መረጋጋት መፍጠር ነው፡፡ ግጭት ውስጥ በገቡ ወገኖች መካከል እርቅ እንዲወርድ በማድረግ የተወሰነ ሳይሆን ለግጭቱ ዘላቂ መፍትሄ በመፈለግ በማህበረሰቡ ዘንድ በግጭቶች ምክንያት ደፍርሶ የነበረውን ሰላም መልሶ ያመጣል፡፡ በግጭት ምክንያት የተቋረጡ ማህበራዊ ግንኙነቶች በመጠገን በማህበረሰቡ ዘንድ ዘላቂ የሆነ ሰላማዊ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ በእምነት ስርዓቶች እና በምግባር መካከል የጠበቀ ግንኙነት ስላለዉ ነው፡፡ ስለዚህ ከሰላም ጋር ያለው ቁርኝት በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

# ዘወልድ፤ ሰንየሰገድ፤ ክፍሎ፤ መዘርድ

በሰሜን ወሎ ዞን የራያ ቆቦ አካባቢዎች በሰዎች መካከል አለመግባባቶችና ችግሮች ሲከሰቱ «የወንዝ አባቶች» ተብለው በሚጠሩ ሽማግሌዎች፡ - በህዝቡ ዘንድ ፍርድ አያጓድሉም ተብለው በሚታመኑ እና በሚከበሩ ሰዎች እልባት የመስጠት የቆየ ባህላዊ ዳኝነት ሥርዓት አለ፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች አራት የወንዝ አባቶች (ዘወልድ፤ሰንየሰገድ፤ክፍሎ፤መዘርድ) የሽምግልና ሥነ-ስርዓቶች ያሉ ሲሆን አራቱም በጥንት ጊዜ ከላስታ እንደመጡ እና በራያ ሰፍረው ቦታ(ግዛት) እንደተከፋፈሉ አፈታሪኮችን ጠቅሰው የወንዝ አባቶች ይናገራሉ፡፡ እነዚህ የሽምግልናና የዳኝነት ስነስርአቶች የአሰራር ሂደታቸውና የፍርድ አሰጣጥ ስልታቸው ተመሳሳይ ቢሆንም አንዱ በአንዱ ካልተፈታለት ወደሌላኛው የወንዝ አባት ሂዶ አቤቱታውን የሚያቀርብበት ሂደትም አለ፡፡ ብዙ ጊዜም ዘወልድን እንደበላይ ቅሬታ ሰሚ እና ይግባኝ ማያ ተደርጎ ይታያል ሲሉ መረጃ ሰጪዎች ይናገራሉ፡፡ የወንዝ አባቶች ሁሉንም የዳኝነት ሥርዓቱን የሚፈጽሙት በወንዝ ዳር ላይ ተቀምጠው ነው፡፡ አፈጻጸሙም በአካባቢው በሚገኝ ወንዝ ዳር በሚደረግ ስብሰባ ነው፡፡ በአካባቢው ካሉ የአገር ሽማግሌዎች መካከል ቀደም ሲል «ዘዉዴ እና አብዩድ» ተብለው ከሚጠሩ የዘር ሐረጋት መሰረት አድርጎ በሥነምግባራቸው የተመሰገኑ አንደበተ-ርቱዕ እና ሃሳብ አፍላቂ ጀግና የሆኑ፤እንዲሁም የኅብረተሰቡን ይሁንታ ያገኙ ሰዎች መሆን የነበረባቸው ቢሆንም አሁን ላይ ግን ከላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች እንዳሉ ሆነው የዘር ሃረጉ ግን እንዲቀር መደረጉን መረጃ ሰጪዎች ይናገራሉ፡፡ በዘወልድ የዳኝነት ስርአት ሁለት የግድያ አይነቶች ተነጣጥለው ይታያሉ፡፡ የመጀመሪያው ቀይ ደም ሲሆን በዚህ የሚጠራው ግድያ በድንገተኛ ሳይታሰብ፤ በአልሞት ባይ ተጋዳይ፣ በቀልድ ወዘተ የሚፈጸም ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ወንጀሉ ታስቦበት፤ ሆን ተብሎና በቂም በቀል አባሪ ተባባሪ በመሆን ቦታንና ጊዜን አመቻችቶ የሚፈጸም ግድያ ከሆነጥቁር ደም ተብሎ የሚታወቀው ነው፡፡ ሁለቱም ጥፋቶች ሲፈጸሙበገዳይና በሟች ቤተሰብ መካከል ችግር እንዳይከሰት በቀል እንዳይንሰራፋ የገዳይ ቤተሰቦች ወደ ዘወልድ አባቶች ዘንድ ቀርበው ሁኔታውን በማስረዳት ሽምግልናው የሚታይበት ሂደት ነው፡፡ ማኅበራዊ ሃብቱ በአሁኑ ሰዓት ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ጋር በመቆራኘትና ጊዜው የሚጠይቀዉን መሻሻል በማሳየት በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ እነዚህ «የወንዝ አባቶች» በበዳይና ተበዳይ መካከል ከቂምና በቀል በጸዳ መልኩማኅበራዊ ግንኙነኙነታቸውንስለሚያጠናከሩ፣ በህዝቡ ከባህል ጋር የተያያዙ ብዙ ክዋኔዎች፡- በማህበረሰቡ ዘንድ በዳይ የተበዳይን ወገን ጣትና ጡት መጥባት ዳግመኛ ጥፋት ላለመስራት ስለሚያገለግሉ ማህበረ-ባህላዊ ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ የነዚህ ማህበራዊ ሃብቶችዋንኛ ተግባር በህዝቡ ዘንድ የሚፈጠሩ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን እንደየሁኔታው በመፍታት በበዳይና ተበዳይ መካከል ከቂምና በቀል በጸዳ መልኩ የነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ግንኙነትን ከማንኛውም የህግ አካለት በላይ ዘላቂ ሰላም የሚመልስ በመሆኑ

ከሰላም ጋር ያለው ቁርኝት ከፍተኛ ነው፡፡

# አበጋር

በደቡብና የሰሜን ወሎ አከባቢዎች ዘንድ በተለይ ግድያ ሲከሰት እርቅ ለመፈጸም ኡማዎችን (ከየጎጡ የተመረጡ ሽማግሌዎችን) በሰብቢነት የሚመራና «ዱኣ በማድረግ» የሚከወን ሥርዓት ነው፡፡ «አበጋር» የሚለው ቃል « አብ» ና «አገር» የሚሉትን ቃላት በማጣመር የተበጀ ሲሆን ትርጉሙም «የአገር አባት» ማለት ነው ሲሉ መረጃ ሰጪዎች ይናገራሉ፡፡ ይህም ማለት የአገር ሽማግሌ ወይም መሪ ተብሎ ስለሚጠራ «የማእረግ ስም ነው» ይላሉ፡፡ በአጠቃላይ ከመረጃ ሰጪዎች መረዳት እንደሚቻለው «አበጋር» ሁሉንም ግጭቶች ለመፍታት ኡማዎችን በሰብሳቢነት የሚመራ አካል ማለት ነው፡፡ የአበጋር ስነስርአት ከትንሽ አለመግባባት ጀምሮ እስከ ነፍስ ግድያ ከዚያም በላይ በሆኑ፣ በፍርድ ቤት እልባት ያላገኙ መረጃ የታጣባቸውን የወንጀል ድርጊቶች ባህላዊና ልማዳዊ የማወጣጫ መንገዶችን በማስቀመጥ የወንጀል ሰንሰለቶችን በመፍታት በዳይ የሚቀጣበት ተበዳይ ደግሞ የሚካስበትን መንገዶች የሚያመቻቹበት ስርአት ነው፡፡ ስለዚህ አበጋር የምንለው ከትንሽ ጀምሮ እስከ ትልቅ ችግር የሚዳኝ አሳቢ አሰባሳቢ እንደማለት ነው ብለው ይተርካሉ፡፡ አበጋር ወንዶች ብቻ የሚሳተፉበት የባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቱ ተቋም መጠሪያ ስያሜና የዳኝነት ሥርዓቱን የሚከውኑ ግለሰቦች የማዕረግ ስም ነው፡፡ በማህበረሰብ ውስጥ የሚከሠቱ የተለያዩ ግጭቶችን የመፍታትና የማስታረቅ ስልጣንና ይሁንታ ያገኙ ሰዎችን የያዘ ተቋም ነው፡፡ አበጋርነት በሁለት መንገድ ይገኛል፡፡ አንደኛው ከዘር የሚወረስ ነው፡፡ በዘር የሚገኘው አበጋርነት ከጥንት ጀምሮ ከአባት ወደ ወንድ ልጅ በቅብብሎሽ የሚወረስ ነው፡፡ ስራውን ተንቀሳቅሶ መስራት ሳይችል ሲቀር በማህበረሰቡ ዘንድ ችግር እንዳይፈጠር በመስጋት ስልጣኑን ያወርሳል፡፡ ሁኔታውን ለአካባቢው ማህበረሰብ ያሳውቃል፡፡ ሁለተኛው የአበጋርነት ማዕረግ ደግሞ በመመረጥ የሚገኝ ነው፡፡ከአካባቢው ማህበረሰብ መካከል ተደማጭነት፣ ተቀባይነት፣ የሚከበርና ተግባቢነት ያለውን ግለሰብ ማህበረሰቡ በመምረጥና በመሰየም የሚሰጠው ማዕረግ ነው፡፡

የአበጋር ስርአት አሁንም በስፋት በመከወን ላይ ይገኛል፡፡ ከዘመናዊ ፍርድቤቶች በመተባበርም ግጭቶችን አስወግዶ ሰላም በማስፈን ላይ ባህላዊው የግጭት አፈታት ስርአት ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ የአበጋር ስርአት በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ የስነልቦና ጫና ከሚፈጥሩባቸው መንገዶች ዋንኛዎቹ «ድቢ ድብደባ» ና «ሙስባህ መላክ » ናቸው፡፡ ድቢድብደባ /በቆዳ የተሰራ ከበሮ መሰል/ የግራ ቀኝ ጠላቶች የሆኑ ሰዎች ልባቸው ራርቶ፤ ወደ እርቅ እንዲመጡ፤ ባይመጡ ግን በራሳቸው ላይ መዓት እንደሚመጣባቸው ስለሚያስቡ እርቁን አይገፉትም፡፡ በሌላ በኩል «ድቢድብደባው» እንደነጋሪት የሚቆጠርና በአንድ አካባቢ ወንጀል ከተፈጸመ ሰው የገደለ ሰው ስላለ እሱን አቅርቡ የሚል እንደመቀስቀሻ መሳሪያ የሚጠቀሙበት ነው፡፡ በአንጻሩ « ሙስባህ/ከቅል የተሰራች/መላክ» ደግሞ የታወቀ ወንጀለኛ ወደ እርቅ አልቀርብም ሲል እንደመጥሪያ የሚያገለግል መሳሪያ ነው፡፡ ሙስባህ የተላከበት ወንጀለኛም ይህን ጥሪ አክብሮ ወደአበጋሩ ይመጣል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ የባህላዊ ዳኝነት ስርአት የቆየና የተደራጀ የሽምግልና ስርአት በመሆኑ፤ ስርቆትን ከመከላከል ባሻገር ማህበረሰቡን ከሌብነት ለማዳን ስለሚያግዝና መልሶ በማህበረሰቡ ዘንድ አብሮነትን ስለሚያጠናክር፤ የተጋጩት አካላት እርቁን የሚፈጽሙት በመሃላና አብረው ከሚኖሩት ህብረተሰብ ፊት ስለሆነ ማህበረ- ባህላዊ ሚናው የጎላ ነው፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ የማህበራዊ ሃብቱ መኖር በተለያየ ምክንያት የተጋጩ አካላትን በማስማማት ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ያገለግላል፡፡ ከጊዜ ገንዘብና ጉልበት አንጻርም ገንዘብና ጉልበትን በቆጠበ መልኩ ግጭቱ ይፈታል፡፡ የተጋጩት አካላት እርቁን የሚፈጽሙት በመሃላና አብረው ከሚኖሩት ህብረተሰብ ፊት ስለሆነ ለውሳኔው ተገዢ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ማህበራዊ ሃብት ጥፋተኞች የሚታረሙበት፤ ጠበኞችም ወደቀደመ ሰላማቸውና ቂም በቀልን አስቀርቶ በበዳይና ተበዳይ መካከል ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረጉ ባሻገር የአብሮነት ህይወታቸው እንዲመለስ የሚያደርጉበት የቆየና የተደራጀ የሽምግልና ስርአት በመሆኑ ከሰላም ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት አለው፡፡

# እሩፎ መረባ

«እሩፎ መረባ» በአማራ ክልል የኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ ያለ ሥርዓት ሲኾን «እሩፎ መረባ» ማለት ጌታ ሆይ ምስጋና ይገባሃል ማለት ሲሆን «ሄ መረባ» ማለት ደግሞ ዱኣችንን/ጸሎታችንን/ ተቀበለን እንደማለት መሆኑን ከዋኝ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡ በዱበርቲዎች የሚከናወነው ይህ « የእሩፎመረባ» ስነስርአት አንዱና በህዝቦች መካከል ግጭት ሲነሳ የሚያስታርቅ ስርአት ነው፡፡ ዱበርቲ የኦሮምኛ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም ሴት ማለት ነው፡፡ እሩፎ በአንዲት አጢ ቃጤ /በእድሜ ትልቅ በሆነች እናት የሚመራ የዱበርቲዎች ስብስብ ነው፡፡ ስርአቱም በእነዚህ ስብስብ ዱበርቲዎች የሚከወን ነው፡፡ የእሩፎ መረባ ስርዓተ-ክዋኔ «እሩፎ መረባ---ሄ መረባ» እየተባለ በምልልስ መልክ የሚከወን ነው፡፡ የእሩፎ መረባ ሥነ-ስርዓት የሚከወንበት የራሱ ጊዜና ምክንያቶች ያሉት ሲሆን ከምክንያቶቹ መካከል በአካባቢው ግጭት ሲፈጠር የተጣሉትን ለማስታረቅ በእርቅ ጊዜ የሚደረግ «የእሩፎ መረባ» ስነ-ስርዓት ነው፡፡ በምርቃን የታጀበተለማምኖ በመሆኑ እርቀሰላም ይፈጠራል፡፡ ክዋኔው የአካባቢው ዱበርቲዎች /ሴቶች/ ተለይተው የሚታወቁበትና የስርዓተ ክዋኔውም ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ ክዋኔው አሁንም በስፋት እየተተገበረ ይገኛል፡፡ የእሩፎ መረባ ሥነ-ስርአት ማህበረሰቡ በእምነት እንዲገዛና ውሸት እንዳይፈጠር፤ በተለይም የእሩፎ መረባ ሥነስርአት የሚከወነው በዱበርቲዎች/ ሴቶች/ በመሆኑ በእለት ተእለት ማህበራዊ ህይወትና ክንውን ውስጥ የሴቶችን ሚና ፤የተቀብሎሽና የተሰሚነት ደረጃ በእጅጉ የሚያሳይ በመሆኑ ማህበረ-ባህላዊ ሚናው የጎላ ነው፡፡ ይህ ማህበራዊ ሃብት ጸብን በማስወገድ በምትኩ መግባባትና መስማማትን ስለሚያስከትል፤ በተለያዩ የግጭት መንስኤዎች የተፈጠሩ አለመግባባቶችን ወደ ዳግም ሰላም ለመመለስ ስለሚያስችል ከሰላም ጋር ያለው ቁርኝት ከፍተኛ ነው፡፡

# አባሀጋ፣ አባጋር፣ ሶራ አባ አርማ

ይህም በአማራ ክልል የኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ የሚተገበር ስርዓት ሲኾን በዞኑ ባሉ ወረዳዎች  አባሀጋ፤ አባጋርና ሴራአባኦርማ የተባሉ ባህላዊ የእርቅና የዳኝነት ስርአቶች በስፋት የሚተገበሩ ናቸው::: ‹‹አባሀጋ›› ከሁለት ቃል የተመሰረተ ሲሆን ‹‹አባ›› ማለት መሪ፤የበላይ ጠባቂ ‹‹ሀጋ›› ማለት ደግሞ ሀቃ ከሚለው ቃል ጋር ተወራራሽ ሆኖ ፍትህ፤ ህግ ማለት ነው:: አባሀጋ በጥቅሉ የስነስርአቱ መሪ /ህግ አስከባሪ የወጣቶችና የልጃገረዶች የጋራ ዳኛ ማለት ነው:: በወጣት ወንዶችና በልጃገረዶች መካከል ጸብ ሲፈጠር የሚዳኝ ማለት ነው:: አባሀጋ የሚሆነው በወጣትነት እድሜ ላይ ያለ ሲሆን አንድ ወጣት በአባሀጋ ለመመረጥ በሀቀኝነቱ፤ በሕዝቡ ዘንድ ያለው የተቀባይነት ሁኔታ በቅድሚያ ተገምግሞ ሲመረጥ የአባሀጋ ሹመት ይሰጠዋል:: ‹‹አባጋር››  በአንድ አካባቢ የሚከሰትን ግጭት በሃይማኖታዊም ይሁን በባህላዊ መንገድ ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ የመዳኘት ስልጣን ያለው አስታራቂ አባትም ማለትም ነው:: የአባጋር የእርቅና የዳኝነት ስነስርአት ከአባሀጋው የሚለየው አባጋር ሁሉን አቀፍ መሆኑ ነው:: በወጣቶች ብቻ የሚወሰን አይደለም:: በአባሀጋው መዳኘት ያልተቻለ ወደአባጋር ተላልፎ ጉዳዩ እልባት ያገኛል:: አባጋር ለመሆን የራሱ መስፈርት ያለውና በእድሜ እረገድ ከወጣትነት የዘለለ ከጉልምስናም ያለፈ ሽማግሌ ነው:: አባጋር ከቤተሰብ ሲወርድ ሲዋረድ በሚመጡ በውርስ የሚገኝ ስልጣንና ሹመት ነው::

በአባጋር መዋቅር ውስጥ ሁለት ዓይነት አባጋር ያለ ሲሆን የመጀመሪያው አባጋር ‹‹አባጋር ዲጋ›› የሚለው ነው:: የዚህ አበጋር ዋንኛ ተግባር ዕርቅ መፈጸም ሲሆን የደም አስታራቂ /ደም አድራቂ በመባል ይታወቃል:: በዚህ ሽምግልና ወቅት በትላልቅ ወንጀሎች ለምሳሌ ህይወት ሲጠፋ ለእርቁ ማስፈጸሚያ ‹‹ፋጂ /ባንዲራ/›› ይይዛል:: ህብረተሰቡም አባጋር ፋጂ ይለዋል:: ፋጂ ተተክሏል ተብሎም ይፈራል:: ከዚህ በተጨማሪ አንድ ወንድ አንዲትን ሴት ለጋብቻ ቢፈልግና አባጋሩ ዘንድ ይዞ ቢሄድ ከቤተሰብ ጋር አስማምቶ በራሱ ቤት የሚድር ነው:: በጥቅሉ ከቀላል ግጭቶች አስከከባድ የህይወት መጥፋት ድረስ ያሉ ችግሮችን ይፈታል:: ከፍተኛ ስልጣን ያለው ነው:: አባጋር ጠበኞችን /ጥፋተኞችን በገንዘብ አይቀጣም :: የሚቀጣው በዓይነት/በባህላዊ ምግብ ነው:: በበሬ፤ፍየል፤ወይም በግ-በግ እርድ በገንፎ፤በወተት፤አልያም በዱዓ/በጸሎት ብቻም ሊያስታርቅ ይችላል::አባጋር ከእነዚህ ሁሉ ስልጣን በላይ ተፈጥሯዊ ስልጣንም እንዳለው ይነገራል::ለምሳሌ ሰርዶ በበረት ውስጥ ቢበቅል፤አካሉ የጎደለ ጥጃ ቢወለድ አባጋር ተጠያቂ ይሆናል ይላሉ:: ሁለተኛው አባጋር ‹‹ አባጋር ቶልቻ›› በመባል ይታወቃል:: የዚህ አባጋር ዋና ተግባር ዱኣ/ጸሎት ማደረግ ሲሆን ዱኣዉን በሰረርግ ጊዜ፤ለተለያዩ የግል ጉዳዮች ለአገር ሰላም፤ወዘተ...እንደአስፈላጊነቱ የሚከናወን ነው ሲሉ መረጃ ሰጪዎች የስልጣን ደረጃውን ያስረዳሉ::

‹‹ሶራ አባ ኦርማ›› በውስጡ ሁለት ዓይነት ህጎችን የያዘ ነው:: የመጀመሪያው ህግ ‹‹ጀላ›› በመባል ሲታወቅ ሁለተኛው  ህግ ደግሞ ‹‹ቡዳ›› በመባል ይታወቃል:: ‹‹ጀላ››  ማለት ትልቅ መንገድ እንደማለት ሲሆን ሰፋ ባለመልኩ ሲታይ ደግሞ ባህላዊ  አስተዳደሩ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣና ለረጅም ጊዜ ሲሰራበት የቆየ ነው:: በዚህ ህግ መሰረት አንድሰው ሌላውን የሚጎዳ ከሆነ እንደጉዳቱ መጠን ጥፋተኛው ተለይቶ የሚታወቅበትና የሚዳኝበት ነው:: “ቡዳ” በተባለው ህግ ደግሞ በአካባቢው የማይታወቅ /ድብቅ ወንጀል የሰራ ሰው የሚዳኝበት ነው:: ድብቅ የተባለበት ምክንያት ጉዳዩ ለሽማግሌዎች ያልተነገረ ከዚህ በፊት ያልታወቀና ያልተሰማ መሆኑን ለመግለጽ ሆኖ በዚህ የሚዳኝ ነው:: በብሔረሰብ ዞኑ በየደረጃው በተዋቀሩ ሽማግሌዎች የሚከወነው የሽምግልና ስርአት ከኦሮሞ ሕዝብ ባህል መገለጫነት ባለፈ የማህበረሰቡ የዘላቂ ሰላም ዋስትና በመሆኑ አሁንም እየተተገበረ ይገኛል:: እንደግጭቶቹ  ቅለትና ክብደት አባሀጋ፤ አባጋር፤ እንዲሁም ሴራአባኦርማ በሚል ከወጣት እስከ ሽማግሌ በየደረጃው በተዋቀሩና በተደራጁ ሽማግሌዎች አማካኝነት በተለያዩ የግጭት መንስኤዎች የሚከሰቱ አለመግባባቶችን ስር ሰደው የከፋ ችግር ከማምጣታቸው በፊት እንደ ግጭቱ ቅለትና ክብደት ግጭቱ እልባት የሚያገኝበት፣ ጥፋተኞች የሚታረሙበት ጠበኞችም ወደቀደመ ሰላማቸውና የአብሮነት ሕይወታቸው እንዲመለሱ የሚያደርጉበት የቆየና የተደራጀ የሽምግልና ስርአት በመሆኑ ማኅበረ ባህላዊ ሚናቸው የጎላ ነው:: በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ለመፍታት በተለይም ወጣቶች ላይ በተለያየ አደረጃጀት ስለሚሰራ ከሰላም ጋር ያለው ቁርኝት ከፍተኛ ነው::

# አሬቅስጊእና መኸይ

ይህ በአማራ ክልል የአዊ ማኅበረሰብ ዘንድ የሚተገበር የሽምግልና ስርአት በአውኚ ቋንቋ ‹‹አሬቅስጊ እና መኸይ›› እየተባለ ይጠራል:: ቃሎቹ በቀጥታ የሚገልጹት የሽማግሌዎችን ስብስብና አሰራር ነው:: ‹‹ሹማጌልካ›› (ሽማግሌዎች) ባለጉዳዮች (በበዳይና በተበዳይ) የሚመረጡ፣ ጉዳዮችን አይተውና ተነጋግረው መፍትሔ የሚያሰጡ፤ የሚያስታርቁ፤ ካሳ የሚገባውን የሚያስከሱ ሲሆኑ ‹‹ሽምግልና›› ደግሞ እነዚህ ሰዎች ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሚያከናዉኑትን የፍትህ ስራ የሚገልጽ ሂደት ነው:: በአዊ የሽምግልና ባህል በስርቆት፤ በዘረፋ በድብደባ፤ በአካል ማጉደል፤ በግድያ፤ በባልና ሚስት ጉዳይ በጉርብትና ግጭቶች ወዘተ ጉዳዮች ላይ የእርቅ ስራ የሚከናወንበት ነው:: ሽምግልና በብሔረሰቡ የእርቅ ስርአት ዋንኛውን ድርሻ ቢወስድም ‹‹የፈረስ አባት፤ የላም ራስና የውሃ አባት›› በመባል የሚታወቁት ተቋማት ባህላዊውን የሽምግልና ስርአት በመደገፍ ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው:: በተለይም በግጭት አፈታቱ ሂደት ሕጻናት እንዲታደሙ መደረጉ የስርአቱን ቅብብሎሽ የሚያሳይ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው::ሥርዓቱ አሁንም እየተከወነና ለማኅበረሰቡ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል:: ባህላዊ የሽምግልና ስርአቱ  በእለት ተእለት የኑሮ  ገጠመኝ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን የሚፈታ፤ በሽምግልና ስነስርአቱ ላይ ሕጻናት ስነስርአቱን እንዲከታተሉና ባህል ወጋቸውን እንዲያውቁ መደረጉ ማህበረ-ባህላዊ  ሚናው የጎላ እንዲሆን አስችሎታል:: ባህላዊ የሽምግልና ሥርዓቱ ካሳ የማይከፈልበት፤ቂም በቀል የሌለበት በመሆኑ  ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ያለው ሚና ከፍተኛ ነው::

# የላም ራስ

ከአዊ ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህና የአስተዳደር ተቋማት አንዱ ‹‹የላም ራስ›› ነው፡፡ የላም ራስ በአንድ አካባቢ ወይም ጎጥ ተሰባስበው የሚኖሩ አርሶ አደሮች ከብቶቻቸውን በጋራ ለማስጠበቅና የግጦሽ መሬታቸውን ለማሁራት/ለማዳበር/፤ይህንንም በተደራጀ አኳኋን ማከናወን እንዲችሉ የሚመርጡት ሰው ነው፡፡ በላም ረስ የሚገለገሉ ስፍራዎች በብሔረሰቡ ውስጥ ህዝቡ ተሰብስቦ የሚኖርባቸው ሰፋፊ ጎጦች ናቸው፡፡ የላም ራሱ የሚመረጠው ከሰው ጋር በመግባባት ችሎታው በቅንነቱና በታጋሽነቱ ሌሎች አባላትን ለማስተባበርና ሀላፊነቱን ለመወጣት ባለው ብቃትና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ባለው ተደማጭነት ነው፡፡ አንድ የላምራስ ከ10-20 የሚደርሱ አባላት ሊኖሩት ይችላል፡፡ እያንዳንዱ አባል በላም ራሱ አማካኝነት የሚጣልበትን ሀላፊነትና ግዴታ መወጣት ይኖርበታል፡፡ በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከብቶቻቸውን አሰባስበው በጋራ የሚያስጠብቁና የሚያሳድሩ የአባዎራዎች ስብስብ ‹‹ጉዲ›› ይባላል፡፡ ‹‹ጉዲ›› የአዊኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ‹‹መንደር›› ወይም ‹‹ጎጥ›› ማለት ነው፡፡ በአንድ መንደር በአንድ ላም ራስ ስር ያሉ አርሶአደሮች የአንድ ‹‹ጉዲ›› አባላት ይሆናሉ፡፡ የላም ራስ ሆኖ የተመረጠው ሰው አዳዲስ ጎጆ ወጪ ወጣቶች ወደማኅበሩ ለመግባት ሲያመለክቱ ጥያቄያቸውን ተቀብሎ የማስተናገድ ተግባራትን ያከናውናል፡፡ እንዲሁም በየዓመቱ ሀምሌ 8 ቀን (ኪሮስ ዕለት) ‹‹ችፊ›› (ዕርድ) እንዲደረግና በነዋሪዎች መካከል የተከሰቱ ግጭቶችን የመፍታት ሃላፊነት ተግባር ያከናውናል፡፡ በነዋሪዎች አስተያየት ‹‹የላምራስ›› በነዋሪዎች መካከል ያሉ አፈንጋጮችን ይቀጣል፡፡ ወይንም ከማኅበሩ ያሰናብታል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ግጭት ውስጥ ገብተው አልታረቅም ብለው የሚያስቸግሩ አባላትን ከማኅበሩ እንዲገለሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡ አንድ የላም ራስ ጥፋት ሲገኝበት የጉዲው አባላት ከኃላፊነቱ ሊያስነሱት ይችላሉ፡፡ የአንድ የላም ራስ የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ነው፡፡ይህ ሃብት አሁንም በስፋት  እየተከወነ ይገኛል፡፡ በየሁለት ዓመቱ በሚደረገው የዙር ምርጫም ማኅበረሰቡን እያገለገለ ይገኛል፡፡ በየዓመቱ በሚከናወነው ‹‹ችፊ ( ዕርድ)››ና ግጭቶች ሲከሰቱ የተጣላ ካለ የሚታረቅበት፤ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር የሚከናወንበት በመሆኑ ማኅበረ-ባህላዊ ሚናው የጎላ ነው፡፡ በነዋሪዎች መካከል የተከሰቱ ግጭቶች የሚፈቱበት፤አፈንጋጮች የሚቀጡበት፤ በተለያዩ ምክንያቶች ግጭት ውስጥ ገብተው አልታረቅም ብለው የሚያስቸግሩ አባላትን ከማኅበሩ እንዲገለሉ በማድረግ መቀጣጫ ስለሚያደርግ፤መደበኛውን የፍትህ አሰጣጥ በመደገፍ ረገድም ከፍተኛ ሚና ስላለው ከሰላም ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት አለው፡፡

# ሽመርነይ/መርካባ

የዋግህምራ ብሐረሰብ በተለያዩ መንስኤዎች የሚከሰቱ ከቀላል እስከ ከባድ ግጭቶችን የሚፈቱበት የራሳቸው የሆነ የሽምግልና ስርአት አላቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል የባልና ሚስት ግጭቶች ፤የቤተሰብ (የአባትናልጅ)፤የጎረቤት ግጭት የምንላቸውን በቀላል ግጭቶች መፈረጁ ሲሆን መንስኤዎቻቸውም የኋሮ/የእርሻ፤ድንበር፤አስተዳደራዊ ችግር ፤ባልበሚስት ላይ መደረብ ሲሆኑ ነፍስ ግድያ ግን ከከባድ ግጭት የሚፈረጅ ሆኖ መንስኤውም ቂም በቀል የእለት ግጭትና ሞቅታ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡ በተለይ ደግሞ በደም እርቅ ወቅት የሽማግሌዎችን ቃል አልቀበልም ያለ የሽማግሌዎች ዓይን ይብላህ ተብሎ ይረገማል፡፡ ይገለላል፡፡ ሽማግሌዎችን የማይሰማ ተብሎ ይወገዛል፡፡ ስለዚህ መገለልና መወገዝን  ስለሚፈሩ የሽማግሌዎች ቃል ይከበራል፡፡ ይህም በመሆኑ የእርቅ ስነስርአቱን አልፈልግም የሚል አይኖርም፡፡ በብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቱም አሁንም እየተከወነ ይገኛል፡፡ በክወኔው ጉዳዩ ወደህግ እንኳ ቢያመራ ዞሮ፤ዞሮ ለዘላቂ ሰላም ሲባል  በሽምግልና እንዲያልቅ ይደረጋል፡፡ ይህ ባህላዊ ግጭት አፈታት ከእምነትም፤ይዞት ሲወርድ ሲወራረድ ከመጣው ባህልም አኳያ ሽምግልናውን አልቀበልም ብሎ የሚገፋ ባለመኖሩ፤በማህበረሰቡ ውስጥ በልዩ በልዩ የመከሰቻ አጋጣሚዎች የሚፈጠሩ ችግሮችን እንደየሁኔታው ጊዜና ጉልበትን በቆጠበ መልኩ ግጭቶች እንደተከሰቱ ችግሩን ለመፍታት ተበዳይ ቤት ድረስ በመሄድ ሰላም እንዲመጣ ማድረጉ ማህበረ-ባህላዊ ሚናው የጎላ አድርጎታል፡፡ በበዳይና ተበዳይ መካከል ቂምናበቀል እንዳይኖር ጠበኞችን ወደሰላማዊ ህይወት መመለሳቸው፤ ቤተሰብ እንዳይበትን፤ በጎረቤታሞች መካከልም በጋራ ችግርን ለመወጣት ስለሚረዳ ከሰላም ጋር ያለው  ቀጥተኛ ቁርኝት ከፍተኛ ነው፡፡

# እውስ (አፈርሳታ፤አውጫጪኝ)

በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት  ከባህላዊ የግጭት ማብረጃና መፍቻ ተቋማት መካከል አንዱ አውስ ወይም አፍርሳታ ነው፡፡አንዳንዴም አውጫጪኝ ይባላል፡፡ በድብቅ ሰው የገደለ፤ቤት ያቃጠለን፤ንብረት፤ገንዘብ፤ከብት የሰረቀን ለይቶ ለማውጣት የሚካሄድ የምርመራ ተግባር ነው፡፡

የአገር ሽማግሌዎች እንደሚሉት እውስ  በጨለማና በድብቅ ማንም አያየኝም በማለት የሰረቀን፤ ቤት ያቃጠለን፤ወይም የገደለን ሰው ሴት፤ ወንድ፤ሕጻን ሽማግሌ ሳይባል በተበደለው  ሰው አሳሳቢነት በጉልተገዢው ሰብሳቢነት መርፌና ክር፤ ወፎች እንዲሁም ዝምጭጭ በሚባሉ መንገዶች ጥፋተኛው በህዝብ ፊት የሚለይበትና የሚጋለጥበት ስርአት ነው፡፡ በእውስ አማካኝነት በድብቅ የተፈጸመን ወንጀል በባህላዊ መንገድ የመፍታት ሂደትና ክዋኔ በአሁኑ ጊዜ በህብረተሰቡ ዘንድ አይሰራበትም፡፡ ስርአቱ የቀረው ደርግ ወደስልጣን ከመጣ ወዲህ እንደሆነ ይነገራል፡፡ እየሰራ ስላልሆነ መህበራዊና ባህላዊ ፋይዳውን መገመት  ባይቻልም በድብቅ የተፈጸመን ወንጀል አጋልጦ ለመስጠት የሚደረገው ስርአተ ክዋኔ ማህበራዊና ባህላዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ እንደገና ቢጠናና ወደተግባር ቢገባበት በተለይ በድብቅ የተሰራን ወንጀል ስለሚያጋልጥ ሰላም የሰፈነበት ማህበረሰብ ለመፍጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ከሰላም ጋርም ቀጥታ ግንኙነት ሊኖረው ይችላል፡፡

## ገዳ

የኦሮሞ ህዝብ ግጭትን ለመከላከልና ሰላምን በዘለቄታው ለመገንባት የገዳ ስርዓትን ከመጠቀሙም ባሻገር ግጭቶች ሲከሰቱ የሚፈቱባቸውን አሠራሮች በዚሁ ስርዓት ውስጥ አካቶ ሲገለገልባቸው ቆይቷል፡፡ ከዚህ አንጻር ገዳ የሃብት ክፍፍልን ከመበየን ጀምሮ በጎረቤታሞች መካከል የሚፈጠርን ግጭት እስከመፍታት የሚደርስ ሚና እንደሚጫውት ይታወቃል፡፡ በተለይም ሉባ የሚባለው የአዋቂዎች መደብ (ከ40-48 እድሜ ያሉት) በቡድኖችም ይሁን በግለሰቦች መካከል የሚነሱትን ግጭቶች በመፍታትና የሃብት ክፍፍልን፣ የወንጀል ቅጣትን፣ የሃብት ጥበቃን፣ ስርቆትንና ወዘተ... የሚመለከቱ ህጎችን ይተገብራል (ደሳለኝ እና ሌሎች 2007)፡፡ ይህንን ሃሳብ የበለጠ ለማብራራት ዋትሰንን (2001) ጠቅሰው ደሳለኝና ሌሎች እንደጻፉት "በጎረቤታሞችና በመንደሮች መካከል ወይም በምንጮች ላይ ግጭት ሲፈጠር ጉዳዩን የሚወስነው አባ ገዳው ነው፡፡ በተለያዩ ብሄረሰቦች መካከል ግጭት ከተፈጠረ አባ ገዳው ሰላም እንዲያወርድ ይጠራል" (2007፣ 151)፡፡ በተመሣሣይ በገዳ ስርዓት ስር ያለው አንዱ ንዑስ-መዋቅር የህግ አባት (Abbaa Seraa) የሚባል ሲሆን ይህም በግለሰቦች፣ በቡድኖች፣ በጎሣዎችና ንዑስ-ጎሣዎች መካከል የሚነሳን ማንኛውንም ግጭት እንደሚያዩና እንደሚፈታ አረባ እና ብርሃኑ (2008) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ገዳ ከፍተኛ ማኅበራዊ ፋይዳ ያለው የግጭት አፈታት ስርዓትን በውስጡ የያዘ የዳበረ ማኅበረ-ባህላዊ እሴት እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡

## ጃርሱማ/ጃርሳቢያ

በኦሮሞ ባህል መሰረት ግጭቶች ወይም አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በቶሎ መፈታት አለባቸዉ። ይህ ካልሆነ አለመግባባቶች ወደግጭቶች ሊያድጉ፣ሌሎች አካላት ሊገቡበትና እየሰፉ በመሄድ ሰላምን ሊያናጉ ይችላሉ። በተለይም የገዳ ስርዓት ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ እያዋለ በማይገኝባቸው አንዳንድ ቦታዎች ግጭቶች በጃርሱማ ወይም በጃርሰ ቢያ ይፈታሉ (አረባ እና ብርሃኑ)፡፡ ጃርሱማ (ሽምግልና) እጅግ የታወቀ የግጭት አፈታትና እርቅ የማዉረድ ባህላዊ ስነ-ስርዓት ሲሆን ጃርሰ ቢያ ደግሞ ይህንን ሥነ-ሥርዓት የሚመራው የሃገር ሽማግሌ ማለት ነው፡፡ ጃርሱማ የሚከናወነዉ ባህላዊ ዕዉቀት፣በማኅበረሰቡ ዉስጥ ከበሬታ ባላቸዉ፣ ፍትህዊ፣ ሁሉን ሰዉ በእኩልነት በሚመለከቱና ለእዉነት በቆሙ በሳል ሽማግሌዎች ነዉ። ጃርሱማ በየደጁና በትላልቅ አደባባዮች ወይም በኦዳ (Odaa) ዛፍ ጥላ ስር ሊሆን ይችላል።

ጃርሱማ በቤተሰብ፣ በጎረቤት፣ በባልና በሚስት፣ በጎሳና ወዘተ...መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ወይም ግጭቶችን ለመፍታት የሚደረግ የእርቅ (Araaraa) ስርዓት ነዉ። አብዛኛዉን ጊዜ ለጃርሱማ የሚቀመጡ ሰዎች ከሦስት እስከአምስት ይሆናሉ። ለእርቅ የሚመረጡ ጃርሶች ከባለጉዳዮቹ ጋር ዝምድና የሌላቸዉ ገልልተኛ አካላት ናቸዉ። ሽማግሌዎች በእርቅ ወቅት ማስረጃን/ምስክርን ሳይሆን እዉነትን /ሀቅን/ በማፈላለግ አጣርተዉ ሀቅ ላለዉ ፍርድ ይሰጣሉ። ጃርሱማ በተለያዩ ጎሳዎችና ተጎራባች ማህበረሰቦች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን ለመፈታትም ይካሄዳል። በእርሻ መሬት፣ በግጦሽ፣ በዉሃ፣ ወዘተ አጠቃቀም ዙሪያ በተለያዩ ወገኖች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በመፍታት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አለዉ።

የጃርሱማ ስርዓት አሁንም በመላዉ ኦሮሚያ ግጭቶችንና ያለመግባባቶችን ለመፍታት ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል። እንደቦረናና ጉጂ ባሉ ዞኖች ዛሬም ማህበረሰቡ ጉዳያቸዉን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ይልቅ በባህላዊ ስርዓት በሽምግልና መፍታት እንደሚመርጡ ጥናቶች ያሳያሉ። የክልሉ መንግስትም ይህ ባህላዊ የዳኝነትና እርቅ ስርዓት እዉቅና አግኝቶ ከመደበኛዉ የመንግስት ተቋም ጎን እንዲሰሩ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ማህበረሰቡ በሚኖርበት አካባቢ የሚፈጠሩትን አለመግባባቶችንና ግጭቶችን በራሱ ባህላዊ ስርዓቶችና ደንቦች መሰረትበራሱ መንገድ ፍትህዊነትና ሀቅ ላይ የተመሰረተ እርቅና መፍትሄ ይሰጣል። መተማመንን በማጎልበት እንዲሁም ጊዜና ወጪ ቆጣቢ በመሆኑም በማህበረሰቡ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት አለዉ። በሽምግልና ጉዳያቸዉ እልባት ያገኙ አካላት ሁሉም አሸናፊ የሚሆኑበት እንጂ አንዱ ወገን አሸናፊ ሌላዉ ተሸናፊ አይሆንም፡፡

## ሲንቄ

ከማህበራዊ ግንኙነት አጠናካሪ ተቋምነቱ በተጨማሪ የኦሮሞ ሴቶች ሲንቄን እንደአንድ የግጭት አፈታት ተቋም ይጠቀሙበታል፡፡ በተለይም በተለያዩ ማኅበራዊ ቡድኖች መካከል (በትዳር ጓደኛ፣ በእናትና በልጅ መካከል፣ በጎሳዎች መካከል፣ በኦሮሞ እና በተለያዩ ብሄረሰቦች መካከል ወዘተ...)ግጭት ሲፈጠር ሴቶች ከሲንቄአቸው ጋራ ሆነዉ ይፈታሉ፡፡ የሲንቄ ተቋም እንደአጠቃላይ ለዘላቂ ሰላም ወሳኝ የሆኑ የሥርዓተ-ፆታ አቅሞችን የሚያበለፅጉና አስፈላጊ የአገር በቀል እሴቶችን የያዘ ነው፡፡ በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥሴቶች እንደሽምግልና እና የሰላም ግንባታ ምልክት ተደርገው ስለሚወሰዱ ለሰላም ያለዉ ፋይዳ የጎላ ነዉ፡፡ ይሁንና ይህ ማኅበራዊ ሀብት የቀድሞውን ያህል ተጽዕኖ መፍጠር በሚችልበት ደረጃ ላይ ነው ማት አይልም፡፡ በአንጻሩ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ሀብቱ በራሱ በኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ የቀድሞውን ተቀባይነት እንዲያገኝ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ የማስተዋወቅ ሥራን የሚሠሩ ጥቂት እናቶች እያደረጉት ያለው ጥረት የሚበረታታ ቢሆንም ሀብቱ ግጭትን በማብረድና ተያያዥ ማኅበረ-ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት ወደሚያስችለው ወደቀደመ ጉልበቱ እንዲመለስ ሰፊ ሥራ መሥራት ይገባል፡፡

## ጉማ

በኦሮሞ የጉማ ስርዓት ላይ የተመሠረተ የግጭት አፈታት በአጠቃላይ በይነ-ተገናኝ እና አሳታፊ ሂደት ነው፡፡ ጉማ ልዩነቶችን የመፍታት እና

የመፈወስ፣ እንደገና የመቀላቀል፣ እርስበእርስ የመተማመን እና የማረጋጋት ሁኔታን ለመገንባት በትብብር እና በሂደት ላይ የተመሠረተ አካሄድ ነው፡፡ በተጨማሪም መተማመንና ሐቀኝነት፣ክፍትና የተሻሻለ ግንኙነት፣ትብብርና ችግር ፈቺነት እንዲሁም ማረጋገጫ የግንባታው መሰረቶች ናቸው፡፡ ተዋንያን በመተባበር በፍትህ ተግባራት ላይ ይሰማራሉ፡፡ በጉማ ስርዓትና ሥነ-ምግባር መሠረት ተጎጂው፣ ወንጀለኛውና ህብረተሰቡ ጥገናን፣ እርቅንና ካሳን የሚያበረታቱ መፍትሄዎችን በመፈለግ ላይ ተሳትፎና ትኩረት ያደርጋሉ። ወንጀለኞች እንደገና ወደ ማኅበረሰባቸው የሚቀላቀሉበት ሂደትና ማኅበረሰቦቹ ራሳቸውን ከመጥፎ ባህርያት የሚያድኑበት አሰራር ነው፡፡ በጉማ ላይ የተመሠረተ የግጭት አያያዝ እና አፈታት ዋና ዓላማ የኅብረተሰብ መልሶ መቀላቀል፣ የእርስበእርስ ግንዛቤ፣ የቡድን መልሶ ማቋቋም እና ርህራሄ ነው፡፡ የጉማ ስርዓት ውስብስብና በሂደት ላይ የተመሠረተ መልሶ የማቋቋም ፍትህ ሲሆን ዋነኛ ግቡም ግለሰቦችን መቅጣት፣ ማስደሰት ወይም የግልፍላጎቶችንና ምኞቶችን ዒላማ ማድረግ አይደለም፡፡ ይልቁንም ይህ ከተሃድሶ ፍትህ መሰረታዊ መርሆዎች ጋር የሚስማማ በመሆኑ የጉማ ስርዓት የደም ገንዘብን ከማስተካከል በላይ ነው፡፡ ለወንጀለኞች እውነተኛ ተጠያቂነት እና ህግን ወደሚያከብር ህብረተሰብ እንደገና የመቀላቀል እድል ይፈጥራል፡፡ በሌላ አገላለጽ የግጭት አያያዝና የመፍትሄ ሂደቶች የግል እና ማኅበራዊ ፈውስን ለማጎልበት፣ መደበኛ ሁኔታን እና የጋራ ደህንነትን እንደገና ለመገንባት ይጠቅማል፡፡

# ጎንዶሮ

የጉጂ ኦሮሞና የጌዴኦ ህዝቦችተጎራባቾች ሲሆኑ በባህል፣ በቋንቋ፣ በኢኮኖሚ፣ በመልክዓ-ምድር፣ በማህበራዊና በታሪክ እጅግ የጠበቀ ትስስር አላቸዉ። ሁለቱ ህዝቦች ታላቅና ታናሽ ወንድማማቾች እንደሆኑ በአፈ ታሪካቸዉ ይነገራል። የየራሳቸዉ የገዳ ስርዓት ያላቸዉ ሲሆን የጌዴኦ የገዳ መሪዎች ምርቃት የሚወስዱት ከጉጂ መንፈሳዊመሪ (አባ ቃሉ) ነዉ። ይህ የቅርብ ትስስር ሰላማዊ ግንኙነት እንዲኖራቸዉና በግጭት አፈታትና በሰላም ግንባታ ረገድ የጋራ ባህላዊ እሴት እንዲኖራቸዉ አድርጓል። ጎንዶሮ በጉጂ ኦሮሞና በጌዴኦ ብሄረሰብ ዘንድ የሚታወቅ የግጭት አፈታትና የእርቅ ባህላዊ ስርዓት ሲሆን በማህበረሰቡ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት አለዉ። ይህ ስርዓት በሁለቱም ማህበረሰቦች ቋንቋ በተመሳሳይ ጎንዶሮ ተብሎ ይታወቃል። ጥሬ ትርጉሙም "ዳግም ሊፈጠር የማይገባ ድርጊት ወይም ሁኔታ" እንደማለት ነዉ። ጎንዶሮ በግለሰብም በማህበረሰብ መካከል የተፈጠረ ግጭት ወይም ጥፋት እንደጸጸት ተወስዶ በእርቅ መፍትሄ የሚሰጥበት ባህላዊ ስርዓት ነዉ። ይህ የግጭት መፍቻ ስርዓት-እርቅ በዋናነት ከዘር (ከትዉልድ) እርግማን የማንጻት የጋራ እምነት ላይ የተመሰረተ ነዉ።

የማህበረሰቡ መሪዎች እንደሚገልጹት በድሮ ጊዜ በጉጂ ኦሮሞና በጌዴኦ ህዝቦች መካከል በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ግድያና ግጭት እንዳይኖር ቃለ-መሀላ (Oath) ተግባብተዉ ነበር። በአጋጣሚም ከተፈጠረ እርቀ-ሰላም የሚያደርጉበት ጎንዶሮ ተብሎ የሚጠራ ስነስርዓት እንደመሰረቱ የሁለቱ ህዝቦች አዛዉንቶች ይናገራሉ። ይህ ቃልኪዳን ከትዉልድ ወደትዉልድ ሲተላለፍ የመጣ ሲሆን ቃልኪዳኑን የሰበረ ሰዉ ወይም አካል ይረገማል። ጎንዶሮ ከትዉልድ እርግማን (ancestral curse) የሚነጻበትና ዳግም ጥፋት እንዳይፈጸም ቃልኪዳን የሚታደስበት ባህላዊ የእርቅ ስርዓት ነዉ። ይህን ባህላዊ የእርቅ ስርዓት በዋናነት የሚመራዉ የጉጂ አባቃሉ ሲሆኑ ከሁለቱ ማህበረሰብ የገዳ አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች በስርዓቱ ክንዉኖች ዉስጥ ሰፊ ተሳትፎ አላቸዉ።

ጎንዶሮ ዛሬም በጉጂ ኦሮሞና በጌዴኦ ህዝቦች መካከል በግለሰብም ሆነ በማህበሰብ ደረጃ ግጭት ለመፍታት የሚጠቀሙበት ስርዓት ነዉ። እአአ በ1998 ዓም በጉጂ ኦሮሞና በጌዴኦ ህዝቦች መካከል ደምአፋሳሽ ግጭት ተፈጥሮ ነበር። የፌዴራል መንግስት መጀመሪያ በሀይል ጣልቃ ገብቶ ለማቆም ሞክሮ አልተሳካም ነበር። በመቀጠልም በመንግስት የተደረጉ የሰላም ኮንፈረንሶች መፍትሔ አላመጡም ነበር። በመጨረሻም መንግስት ሁለቱ ህዝቦች በባህላቸዉ እንዲፈቱ ዕድል ሰጠ። በዚሁ መሰረት ሁለቱ ህዝቦች ግጭቱን በጎንዶሮ ስርዓት ፈትተዉ ለረጅም ዓመታት አንጻራዊ ሰላም ለመፍጠር ችለዋል። ይህም በሰላም ግንባታና በግጭት አፈታት ሂደት ዉስጥ ማህበረሰቡ በራሱ ባህላዊ ስርዓት መሰረት መሳተፍ ከላይ ከሚመጣ አሰራር የተሻለ ዉጤታማ መሆኑን ያሳያል፡፡

# አዳ ያኢ ቢያ

በምስራቅ ኢትዮጵያ የሚገኙ የኦሮሞ ሕዝቦች በማንኛውም ጊዜ የሚከሰቱትን ግለሰባዊም ሆነ ቡድናዊ ችግሮችን (ግጭቶችን) ለመፍታት ወይም መፍትሔ ለመሻት የራሳቸው የሆነ የሽምግልና ሥርዓት አላቸው፡፡ ይህ የሽምግልና ሥርዓት «አዳ ያኢ ቢያ» ወይም «ሴረ ኦሮሞን ኢቲቡልቱ» በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ሥርዓት በምስራቅ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ሌሎችሕዝቦች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ከሱማሌ የሽምግልና ሥርዓት «ሔር»ጋር አቻ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ በአዳ ያኢ ቢያም እንደ ገዳ ሥርዓት ሁሉ ዕድሜ ለማሕበራዊ ክንዋኔና ለሃላፊነት መለኪያ ያገለግላል፡፡ በአሁኑ ወቅት በምስራቅ ሐረርጌ ኦሮሞ ህዝብ መካከል የሚከሰቱ ማሕበራዊ ችግሮችን (ግጭቶችን) ለመፍታትይህ«አዳ ያኢ ቢያ» በመባል የሚታወቀው ባህላዊ የሕግ ሥርዓት ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡ በአካባቢው የክርክር ሥርዓት የሚል አቻ ትርጉም ያለው ይህ ባህላዊ ሥርዓት በማናቸውም ቤተሰቦች ወይም ጎሳዎች መካከል የሚፈጠሩ ማሕበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በአካባቢው የዕድሜ ባለፀጎች (ሽማግሌዎች) የችግሩ ምንጭ ተፈልጎ ችግሩ ሳይባባስ መፍትሔ ይፈለግለታል፡፡ የችግር አፈታት ሥርዓቱም እንደሚከተለው ነው፡፡ በክርክሩ ወቅት ሽማግሌዎቹ ባህላዊ ፍርድ ከመስጠታቸው በፊት ከሁለቱ ወገኖች የተነሱ ፍሬ ሃሳቦች ወይም ጭብጦች በመስማት ቃላቸውን ይቀበላሉ፡፡ ቀጥሎም ከሁለቱ ወገኖች የሚነሱትን ቃልና እንደሁኔታው የምስክሮችን ቃል በመቀበልና አጠቃላይ ሁኔታውን በጥሞና ተመልክተውና መርምረው ፍትሃዊ የሆነ የፍርድ ውሳኔ ያስተላልፋሉ፡፡ በዚህ ባህላዊ የፍርድ ሂደት ላይ የሽማግሌዎቹ ጥልቅ የትኩረት አቅጣጫ ውሳኔ የመስጠት ጉዳይ ሳይሆን የውሳኔውን ፍትሃዊነት ማረጋገጥና ከአድሎና ከወገናዊነት ነፃ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ባህላዊ የሽምግልና ሥርዓት የገዳ ሥርዓት ቅሪት በመሆኑ የጋራ አመራርና የጋራ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡

# ጃርሱማ/መንጉዶ

የኦሮሞ ህዝብ ለረጅም ጊዜ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን የሚያከናውንበት፣ ባህላዊ አስተዳደሩንየሚመራበት፣ እርቅ የሚፈጸምበትና ማኅበረሰቡን የሚያስተሳስርበት ሥርዓት የነበረው ሲሆን አሁንም የዚህን ባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓት እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ የመንደር ሽማግሌዎች ከአካባቢያቸው ተነስቶ ወደ እነሱ የሚመጡ ጉዳዮችን የማስተዳደርና ለጉዳዩ አስፈላጊውን መፍትሔ የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው፡፡ በብሔሩ ባህልና ሕግ መሠረት በመንደር ውስጥ የሚነሱትን ማናቸውንም ችግሮች የሚፈቱ የሽማግሌዎች ቡድን «መንጉዶ» ወይም «ጃርሶቲቢያ» ይባላሉ፡፡

ሽማግሌዎቹ ስለግጭቱ ጉዳይ በተጨባጭ መረጃ ሲደርሳቸው ወደ ሥፍራው በመሄድ ሁኔታውን ለማረጋገጥ ይሞክራሉ፡፡ ቁጥራቸው ግን የተወሰነ ባለመሆኑ ሁለትና ከዛ በላይ ሆኖ መሄድ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው በሌላኛው ላይ የከፋ አካላዊ ጉዳት አድርሶበት ከሆነ የተበዳዩ ወገን (አባት) በሽማግሌዎች አማካኝነት ወደ በዳዩ ወገን እንዲህ የሚል መልዕክት ይልካሉ፡፡ «ልጃችሁ በልጃችን ላይ አካላዊ ጉዳት ስላደረሰ ግድያ ከሆነ ስለገደለ በአፋጣኝ መጥታችሁ ጉዳዩን እንድትመለከቱ» ይላሉ፡፡ የበዳዩ ወገን (አባት) በደረሳቸው መልዕክት መሠረት «ደሚና» ተብሎ የሚጠራ የጎሳውን አንጋፋ ከሽማግሌዎች ጋር ይልኩና ጉዳዩን እንዲያጣሩ ያደርጋሉ፡፡የተጎጂው ወገን ሽማግሌዎች የእርቅ ጥያቄ ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ በተጎጂው ወገን እሽታ የተደሰቱ ሽማግሌዎች ከምስጋና ጋር ለእርቅ ቀጠሮ ይይዙና ወደ ተቀራኒው ወገን ቤት ይመለሳሉ፡፡በዚህም መሠረት የጎሳው አንጋፋ (ደሚና) ከጎሳው ጋር በመነጋገር በእርቁ ዙሪያና በካሳ አከፋፈልና በካሳ አሰባሰብ ዙሪያ ይመካከራሉ፡፡በቀጠሮውም መሠረት ሁለቱ ወገኖች ይገናኙና በምስክሮች በመደገፍ የነገሩን ግራና ቀኝ በዝርዝር በማየት ጥፋተኛው እንዲታወቅና ፍርድ ተሰጥቶ ላደረሰው የአካል ጉዳት ወይም ጥቃት ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

የካሳ አከፋፈሉ እንደጥፋቱ ዓይነት የተለያየ ሲሆን ከግድያ ውጭ ለሌሎች አካላዊ ጉዳት ወይም ጥቃት የሚከፈለው ካሳ «ዲያ» (ቀለል ያለ ካሳ በመባል ይታወቃል፡፡ ጥፋተኛው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተላለፈበት በኋላ አንድ አንድ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ካሳው ሊቃለልለት የሚችል ሲሆን ይህም «ማልቀሎ» በመባል ይታወቃል፡፡ በመጨረሻም እርቁን ለመፈጸም መንጉዶዎች (ሽማግሌዎች) መጀመሪያ በዳዩን በማስነሳት ቀጥሎም ተበዳዩን በማስነሳት እጅ ለእጅ ተጨባብጠው እንዲሳሳሙ ያደርጋሉ፡፡ በሌላ በኩል በብሔሩ ባህል መሠረት ከአማቹ ጋር የተቀያየመ ወይም የተጋጨ ግለሰብ ጉዳዩ ሽማግሌዎቹ ጋር እንዲደርስ በማድረግ ግለሰቡ በሽማግሌዎች ጥሪ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ ጤናማ ግንኙነትን ለመፍጠር ጥፋተኛው ጥፋቱን ተቀብሎ አማቹን ይቅርታ በመጠየቅ እርቁ ይፈጸማል፡፡ ከአባቱ ጋር የተጋጨ ሰው አባቱን ይቅርታ እንዲጠይቅ ይደረጋል፡፡ ከአባቱ ጋር የተጋጨው ግለሰብ ያላገባ እንደሆነ ይገረፍና አባቱን ይቅርታ ሊጠይቅ ይገባል ይላሉ የአካባቢው ሽማግሌዎች፡፡ ግለሰቡ ያገባ ከሆነ አባቱን የሚያስታርቀው ሙሉ ልብስ በማልበስ ይሆናል፡፡

# ሔር

ሶማሌዎች በርካታ ጎሣዎችና ንዑስ-ጎሳዎች ያላቸው ህዝቦች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ የዳሮድ ጎሣ (Darood) በኢትዮጵያ ከሶማሌ ብሄራዊ ክልል ከዘጠኙ ዞኖች በ7ቱ ይኖራሉ፡፡ ከነዚህ 7 ዞኖች ደግሞ ኦጋዴን (Ogaden) በስድስት ዞኖች የሚኖር በመሆኑ ሔር-ዳሮድ ሁሉም ኦጋዴኖች የሚጠቀሙበት ህግ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በተመሣሣይ ኢሳ ከሶማሌ ዋና ዋና ጎሳዎች መካከል አንዱ ሲሆን ጎሳው ማንኛውም የሚፈጠሩ ማሕበራዊ ችግሮችን የሚፈታበት ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት አለው፡፡ በዳሮድም ይሁን በኢሳ ጎሣዎችና ንዑሳን-ጎሳዎች መካከል የሚነሳ ፀብና አለመግባባት ሔር (Xeer) ተብሎ በሚጠራ ባህላዊ ሕግ (አስተዳደር) መሠረት ችግሩ ተወግዶ መፍትሔ ያገኛል፡፡ ሞሃመድና ዘውዴ የሔርን አመጣጥ እንደሚከተለው አብራርተውታል፡፡ "ሶማሌዎች የራሳቸውን ጎጆዎች/ቤቶች በመስራት ይታወቃሉ፡፡ ቤቶቹ በርካታ ቁሳቁሶችን የያዙ ሲሆን እነዚህም ዙሪያቸውን ሄር በሚባል ረጅም ገመድ ይታሰራሉ፡፡ በተመሣሣይም ሶማሌዎች የሚጋጩ ፍላጎቶች ያላቸውን አባላት አንድ ላይ የሚያስተሳስሩት ሄር በሚባለው ህግ ወይም ስምምነቶች ነው" (2008:185-199)፡፡

ይህ ባህላዊ ህግ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን የተከተለና በማንኛውም ጊዜ መፍትሔ የሚያስገኝ ጠንካራ ህግ ነው፡፡ ህጉ ሚዛናዊ ከመሆኑ የተነሳ ሁሉም ንዑሳን ጎሳዎች ይዳኙበታል፤ ችግራቸውንም ይፈቱበታል፡፡ በዚህ መሠረት ማንኛውም አጥንቱ ተሰብሯል፤ ስጋዬ ተቆርጧል ያለ ሰው በሔር (xeer) መዳኘቱ ግድ ይሆናል፡፡ በሕጉ መሠረት በቀል የተከለከለ ሲሆን ሁለቱ የተጣሉ ወገኖች (ቡድኖች) በሕጉ መዳኘትና የሕጉን የፍርድ ውሳኔ መጠበቅ ግድ ይላቸዋል፡፡ ሕጉ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. ሔር ዲግ (Xeer Dhig)፤ ይህ ሕግ የግድያ ጥፋት የሚዳኝበትና የደም ካሳ ሕግ ሲሆን የራሱ የሆነ ለየት ያለ አካሄድአለው፡፡ የሕግ ስርዓቱ የሚጀምረው ግድያው እንደተፈጸመ ወዲያውኑ ድርጊቱ ለሽማግሌዎች በአፋጣኝ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ተጠያቂው የገዳዩ ጎሳ እንደመሆኑ መጠን የገዳዩ ወገኖች ሁኔታው ወደ አደገኛ የደም መፍሰስ እንዳይሄድ ለማድረግ ሲባል በሟቹ መቃብር ላይ እርድ ይፈጽማሉ፡፡ ይህ ማለት ሰላም ይውረድ በሟቹ ምትክ ካሳ እንከፍላለን የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ነው፡፡ ይህንን እርድ ማንም የማይመገበው ሲሆን ሌላ የማስታረቂያ ተብሎ በግ ይታረድና ሁለቱም ወገኖች በጋራ በአንድ ማዕድ እንዲመገቡ ይደረጋል፡፡ይህ የግድያ ፍርድ ረጅም ጊዜ ሳይወስድ በአስራ አምስት (15) ቀን ውስጥ የሚጠናቀቅ ሲሆን አስራ ሁለት (12) የሽማግሌዎች አባላትን የያዘ የኢሳ ቤት (Assembly) ገዳዩን ይዳኛሉ፡፡ በሱማሌ ብሔረሰብ ዘንድ ትልቁ ወንጀል ግድያ ሲሆን ግድያ የፈጸመ ወገን (ሰው) ካሳ ይከፍላል፡፡ ገዳዩ ካሳውን የሚከፍለው በግሉ ሳይሆን ከጎሳው በሚሰበሰበው ግመል ይሆናል፡፡ ለካሳ የሚከፍለው እንደ ግመል፣ በሬና በግ ሲሆን የሚከፍለው ካሳ በግ ከሆነ አስራ ሁለት (12) በግ በአንድ ግመል ስሌት ይሆናል፡፡ ለካሳ የሚከፍለው የግመል ቁጥር እንደየጾታው ይለያያል፡፡ ሟቹ ወንድ ከሆነ ለካሳ የሚከፍለው የግመል ቁጥር ሰባ ሰባት (77)

ወይም መቶ (100) ሲሆን ሟች ሴት ከሆነች ሐምሳ (50) ግመሎች ብቻ ለካሳ ይከፍላል፡፡ ከግድያ ውጭ ሌሎች ወንጀሎች ፍርድ የሚዳኙ የሽማግሌዎች ቁጥር ከሶስት እስከ ስድስት (3-6) ይሆናሉ፡፡ በግድያ ምክንያት በተከሰተ ግጭትን የሚፈቱ የሽማግሌዎች ቁጥር ከአስራ ሁለት (12) በታች መሆን የለበትም፡፡ አንድ ሰው ከጎደለ ምንም አይነት የፍርድ ውሳኔ አይሰጥም ምክንያቱም ግድያ ከባድ ወንጀል ከመሆኑ የተነሳ ነው፡፡ የዳኝነት ሂደቱ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ ምስክሮች ይቀርባሉ፤ የሟችና የገዳይ ጎሳም የሚቀርቡ ሲሆን ገዳይ ግን ጉዳዩ መፍትሔ እስኪያገኝ አይቀርብም፡፡

ለ. ሔር ደቃቀል (xeer Dhaqaaqal); በሔር ደቃቀል ንብረት ነክ የሆኑ ጉዳዮች ይዳኙበታል፡፡ የዚህ ግጭት የእርቅ ሥነ-ሥርዓት እንደ ሔር ዲግ (xeer dhig) በአስራ ሁለት (12) ሽማግሌዎችና በካሳ ሳይሆን ሽማግሌዎቹ የግጭቱን መነሻ ከለዩ በኋላ በባህሉ ሥርዓት እርቅና ሰላም እንዲወርድ መወሰን ብቻ ነው፡፡ ይህንን እርቅ የሚያከናውኑ የሽማግሌዎች ቁጥር ከሦስት እስከ ስድስት ይሆናል፡፡ ይህ የእርቅ ሥነ-ሥርዓት እንደ ሌሎቹ ብዙ ጊዜና ብዙ ጉዞ ሳይጠይቅ በቀላሉ የሚፈታ ነው፡፡

ሐ. ሔር ዴር (xeer dheer)፤ ይህ የሴቶችን ጉዳይ የሚመለከት ባህላዊ የሕግ ሥርዓት ሲሆን በተለይም ግጭት የሚነሳው የአንዱ ንዑስ ጎሳ የሌላኛውን ንዑስ ጎሳ ሴት ሲደፍር ነው፡፡ በብሔሩ ባህል መሠረት አንዲት ባል የሞተባት ሴት ሌላ ለማግባት አራት ወር ከአስር (4ወር ከ10) ቀን መጠበቅ ግድ ይላታል፡፡ ይህችን ሴት ማግባት የሚችለው የሟቹ ወንድም እሱ ከሌለ ከሟቹ ዘመድ ይህም ከሌለ ከጎሳው ይሆናል፡፡ ከሟቹ ወገን የሆኑ ወንዶች ይህችን ሴት ለማግባት የአራት ወር ከአስር ቀን ጊዜ በመጠባበቅ ላይ እያሉ በሌላኛው ንዑስ ጎሳ አባል የምትደፈር ከሆነ የፀቡ መንስዔ ይሆናል፡፡በብሔሩ ባህል መሠረት የሴት ልጅ ድምጽ ተሰሚነት አለው፡፡ ሴት ልጅ እገሌ በድሎኛል ብላ አልቅሳ ከከሰሰች ተቀባይነት ስላላት ምንም ጉዳዩዋን ለማየት ምስክር አያስፈልግም ምክንያቱም በማኅበረሰቡ ባህል ሴት ልጅ በፍጹም አትዋሽም ብሎ ስለሚያምኑ ነው፡፡ ሴት አካላዊ ጥቃት ከደረሰባት ማንም የማሳከም ሃላፊነት አለበት፡፡ በጎሳው ዘንድ ከዳኝነት ውሳኔ በስተቀር የቃል ምስክርነት የመስጠትና ሌሎች የሴቶች መብቶች የተጠበቁ ናቸው፡፡ ይህንን ግጭት ለማስወገድ የሚከፍለው የካሳ ግመል ቁጥር አስራ አምስት (15) ሲሆን ፍየል ስትጠብቅ ለተደፈረች ሴት የሚከፈል የካሳ ግመል ቁጥር አስራ ስድስት (16) ይሆናል፡፡ ሴቷ አራት ወር ከአስር ቀን ጨርሳ ማንንም አላገባም ካለች በሽማግሌዎች ውሳኔ መሠረት ከጎሳው እንድትገለል ትደረጋለች፡፡

መ. ሔር ዲብሌ (Xeer Dhiblee)፤ ይህ ህግ አራተኛው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሲሆን በዚህ መሠረት የሚፈታው ግጭት በማንኛውም ወቅት ከጎሳው ውጭ በድንበርና በሌሎች ምክንያት ከሌሎች ጎሳዎች ጋር የሚፈጠር ግጭትን ለመቀልበስ የተደነገገ የቆየ ባህላዊ ሕግ ነው፡፡ የብሔረሰቡ ሽማግሌዎች እንደሚናገሩት ሔር (xeer) ለእነሱ ከምንም በላይ ነው፡፡ የዚህ ባህላዊ ሕግ እያንዳንዱን አንቀጾች ያከብሩታል፤ ማኅበራዊ ችግሮቻቸውንም ይፈቱበታል፡፡ ሔር ዲሞክራሲን መሠረት ያደረገ ስለሆነ ፍትሐዊነቱ የጎላ ነው፡፡ በኢሳ ማሕበረሰብ መካከል የተነሳ ችግር (ግጭት) ከሔር (xeer) ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡ ሕጉ ሁሉን አቀፍ በመሆኑ ማንኛውም የማሕበረሰቡን ወግና ባህል የለቀቀ ነገር በሙሉ ይስተካከልበታል ሥርዓትም እንዲይዝ ይደረግበታል፡፡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ለዘመናዊው የፍርድ ሂደት የራሱ የሆነ የጎላ ሚና እያበረከተ ነው፡፡ «ከገንዴ» ባህላዊ ፖርላማ እስከ መንደር ሽማግሌዎች ያሉ እርቅ አስፈጻሚ አካላት ሰላምን ለማውረድ የተጣለባቸውን ኃላፊነት ይወጣሉ፡፡ የዳኝነት ሥርዓቱ የሚካሄደው በዛፍ ሥርና በወንዞች አካባቢ ሲሆን ይህም ችሎቱን ለመከታተል በርካታ ሰዎች እንዲገኙ ያስችላቸዋል፡፡

## ጌድፈዲሲ/ጌድሆስቲ

ጌድ ፈዲሲ በሽንሌ ዞን የሚኖሩ የኢሳ ማህበረሰቦች ባብዛኛው ለሰላም ግንባታ ሥራቸው የሚጠቀሙበት ሀገረ-ሰባዊ የእርቅና የሽምግልና (የፍፁም ይቅርታ) ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡ የሶማሌ ማህበረሰብ በአብዛኛው በተለያዩ መንስኤዎች (በግጦሽ፣ በውሃ ጉድጓድ፣ በሴት ጠለፋ፣ በከብት ዝርፊያና የመሳሰሉት) ግጭቶች በሚከሰቱበት ጊዜ እነዚህን ለመፍታት የሚጠቀሙት መንገድ ነው። ይህ ስነ-ስርዓት የሚከወነው ሽማግሌዎች በዛፍ ስር በመሰብሰብ ሲሆን የሁለቱንም ጎሳ ጉዳዮች በማዳመጥና ዉሳኔ በመስጠት ግጭቱ እንዲቆም በመጠየቅ ነው፡፡ ሀገር በቀል እሴቱ የሚከወነው የተፈጠሩ አለመግባባቶች ወደ ከፍተኛ ግጭት እንዳያመሩ ሽማግሌዎች ጣልቃ በመግባት የሚያስቆሙበትና የሚያስታርቁበት በመሆኑ ከሰላም ጋር ከፍተኛ ቁርኝት አለው፡፡ ወጣቶችም ሆኑ ማንኛውም የአካባቢው ነዋሪ የማህበረሰብ ክፍል ይህንን የሀገር በቀል እውቀቶቻችን ውጤት የሆነውን ሀገረ-ሰባዊ የግጭት መፍቻ መንገድ አምኖና ተቀብሎት በማክበር ይፈፅመዋል፡፡

## ሔራ

በሐረሪ ህዝብ በርካታ ማህበረ-ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትና ስርዓቶች ያሉ ሲሆን በአጠቃላይ ሔራ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ሐረሪዎች በቤተሰብ ደረጃ ያለውን አውዋ አይን (Aw wa ay) ጨምሮ አህሊን (Ahly/kinship)፣ቶያ ማለቁን (Toya malaqe/neighborhood committee)፣አፎቻን (Afocha/Association) እንዲሁም ባድ ረጋን (Bad Raga/Harari Elders Assembly) ለበርካታ መቶ ዓመታት በስፋት ሲጠቀሙባቸው ቆይተዋል፡፡ በሐረሪ ሕዝብ ቅድመ- እና ድህረ-ግጭት አፈታት ስርዓት መካከል "Aw wa Ay" የሚባለው ስርዓት በሁሉም ደረጃ የግጭቶችን ስርጭት ለመቀነስ ጠቃሚ ሚና ይጫወታል፡፡ በተለይም ሰላምና አብሮነት በቤተሰብ ደረጃ ስለሚጀምር ሕጻናትን ከመጀመሪያው ጀምሮ በዚህ መንገድ መቅረጽ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የሐረሪ ህዝብ የቆየ ራስን በራስ የማስተዳደር፣ የትብብር፣ እንዲሁም ሰላምና መረጋጋትን ሲያሰፍንባቸው የኖረባቸው አፎቻ፣ ሙሬኖ፣ ባሃ፣ ጀመሃ እና ጉዛ የሚባሉ አምስት ባህላዊ ተቋማት እንዳሉት ሙስጠፋን (1988) ጠቅሰው ብሩክና ጂራ (2008) ጽፈዋል፡፡ በአጠቃላይ የሐረሪ ህዝብ በአብዛኛው 'Karsamle gabata hidagulo!...Cinanamle uga Hida-

gulo!" በሚባለው መርህ የሚመራ ሲሆን ይህም ማለት "ምግብን ለበላተኛ እንዲሁም ለነገረኛ/አደገኛ ሰው መንገድህ ልቀቅለት" በመሆኑም ቤተሰቦች (mother and father) እነዚህንና ሌሎች የ"HERA" ግጭት አፈታት ስርዓቶችንና የ"HALA MAHAL" mindset በተለይም ለህግና ስርዓት የመገዛት አስፈላጊነትን ለልጆቻቸው በማስተማር ከሚያስከትሏቸው ችግሮች እንዲጠበቁ ያደርጋሉ፡፡ የሐረሪ ህዝቦች ለህግ የበላይነት ከፍተኛ ክብር እንዳላቸው አብዱልፈታህ አብዱላሂ (2008) ይገልጻል፡፡ ይህ የሔራ ሞዴል አሁንም ድረስ በስራ ላይ እየዋለ የሚገኝ ሲሆን ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሐረር ግጭቶችን መከላከልና መፍታት የተቻለው በዚሁ ስርዓት ነው፡፡

# ትምባ

በቤኒሻንጉል ክልል በመተከል ካማሺ ዞን የጉሙዝ ብሄረሰብ ሀገረ-ሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ ሲሆን ዘመናዊ የአስተዳደር ዘይቤ ከመጀመሩ በፊትና እንደዛሬው የተፃፈ ህግና ዘመናዊ ፍርድ ቤቶች ባልነበሩበት ዘመን ጀምሮ የጉሙዝ ማህበረሰቦች በመካከላቸውም ሆነ ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል ጋር ግጭቶች ሲከሰቱ በሰላማዊ መንገድ ግጭቶችን በመፍታት በአከባቢያቸውን ሰላምና መረጋጋትን በማስፈን ሲጠቀሙበት የነበረና አሁንም እየተጠቀሙበት ያለ አገረ-ሰባዊ የፍትህ ተቋም ነው፡፡ ?የትምባ? ሥርዓት የሚመሩ ከብሄረሰቡ አባላት መካከል የብሔረሰቡን ባህልና ወግ ጠንቅቀው በሚያውቁ፣ በመልካም ስነ-ምግባራቸው አንቱ የተባሉ፣ ስለስርዓቱ ዕውቀትና ችሎታ ያላቸው እንዲሁም በዕድሜ የገፉ ሽማግሌዎች ተመርጠው ነው፡፡

በ"ትምባ" ግጭት አፈታት ስርዓትና ደንብ መሰረት ግጭቶች በሁለት መንገድ ይፈታሉ፡፡ አንደኛ የቀላል ወንጀሎች የግጭት አፈታት ስርዓት፤ ሁለተኛ የከባድ ወንጀሎች የግጭት አፈታት ስርዓት ናቸው፡፡ የሰው ልጆች በየእለት የኑሮ እንቅስቃሴያቸው ውስጥ በብዙ መልኩ የእርስ በእርስ ግንኙነቶችን ይፈጥራሉ፡፡ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በመሆኑም በጉሙዝ ማህበረሰቦች በዚህ መልኩ በየእለቱ እርስ በእርስ እና ከለሎች ጋር በሚገናኙበት ወቅት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡ በቀላል ጉዳይ የተቀሰቀሰው ግጭት ቶሎ ካልቆመና በትኩሱ መፍትሄ ካልተገኘለት ሰዎች ወይም ግለሰቦች ይጎዳደላሉ፡፡ በጉሙዝ ብሄረሰብ ከባድ የሚባሉ ወንጀሎች ድብደባ፣ አካል ማጉደል፣ የሴት ልጅ ጠለፋና ግድያ ናቸው፡፡ በከማሺና ማንዱራ ወረዳዎች መረጃ አቀባዮች እንደገለፁት በሁለት ወገን ወይም ጎሳዎች መካከል ግጭት ሲፈጠርና ከአንደኛው ጎሳ ወይም ወገን የሰው ህይወት ቢጠፋ በመጀመሪያ ገዳዩ ወደሌላ አከባቢ እንዲሸሽ ይደረግና በቁጥር ከሶስት እስከ አራት የሚደርሱ በእድሜ በሰል ያሉ እናቶች ለምለም ሳር፣ ነጭ ማሽላና ጥጥ በመያዝ ወደ ሶስተኛ ወገን/ጎሳ/በመሄድ የሟች ወገኖችን ለእርቅ እንዲማፀኑ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ሦስት ነጭ ነገሮች በጉሙዝ ማህበረሰብ የሰላም ተምሳሌቶች ናቸው ተብሎ ይታመናል (ሎላሳ አሸካ፤ ምት ምህ፤እና ያዴሳ ዲቢ)፡፡ በመቀጠል የሟዋች ወገኖች ከያሉበት ተጠራርተው ተሰባስበው በጉዳዩ ዙሪያ በሰፊው ከተወያዩ በኋላ ለእርቅ ከተስማሙ ማሽላውን ቀምሰው ይመልሳሉ፡፡

ሦስተኛ ወይም /ገለልተኛ/ ወገኖች ሁለቱን ወገኖችን በማነጋገር "የትምባው" ስርዓት የሚከናወንበትን ጊዜና ቦታ ይወስናሉ፡፡ በተባለው እለት የሁለቱ ጎሳ ተወካዮች በተገኙበት ክርክር /ሙጉት/ ይጀመራል፡፡ ወደ ዋናው ቁም ነገር ከመገባቱ በፊት "የትምባው" መሪ ይመረጥና እሱ በበኩሉ ደግሞ ከሳሽና ተከሳሽን ዋስ ያስጠራል፡፡ በመቀጠል የሟችና የገዳዩ ወገኖች የደረሰባቸውን ችግር አንድ በአንድ ለሀገር ሽማግሌዎች እንዲናገሩ እድል ይሰጣቸዋል፡፡የሀገር ሽማግሌዎች ግራና ቀኝ ካዳመጡ በኋላ በጥልቀት ተወያይተውበት ውሳኔ ያስተላልፋሉ፡፡ ውሳኔው ከሁለቱ ወገኖች እኩል ህይወት ጠፍቶ ከሆነ ያለ ካሳ እንዲታረቁ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ከአንደኛው ወገን እላፊ ሕይወት ጠፍቶ ከሆነ በጥንት ጊዜ ለሞተበት ወገን ሴት ልጅ ካሳ ይከፈል ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ሴት ልጅ ካሳ መሰጠቱ ቀርቶ እርቁ በገንዘብና በዓይነት እየተደረገ ይገኛል፡፡ እንደመረጃ ሰጪዎች አገላለፅ ሴት ልጅ ካሳ የምትከፈለው በብሄረሰቡ ሟችን ወልዳ ትተካለች የሚል እምነት ስላለ ነው፡፡ ነገር ግን ግድያው ከጉሙዝ ማህበረሰብ ውጪ ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር ከሆነ ለሞተበት ወገን እንደ አከባቢው ሁኔታ ከሰላሳ እስከ አርባ ሺህ የደም ካሳ በመክፈል የትምባው ስርዓት ይፈፀማል፡፡

ከላይ በተገለፀው አካሄድ የትምባው ስርዓት ከተፈፀመ በኋላ የሟች ወገኖች፣ የገዳይ ወገኖችና የሀገር ሽማግሌዎች ውሃ ያለበት ወንዝ ለእርቁ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ዶሮ፣ ጥቁር በግና ለሎች ቁሳቁሶችን ይዞ ወንዝ ይወርዳሉ፡፡ ሁለቱ ባለጉዳዮች ወይም ጎሳዎች አንደኛው ጎሳ ከወንዝ ወዲህ ማዶ ሌላኛው ጎሳ ከወንዝ ወዲያ ማዶ ሁኖ ወንዙ ላይ መጋረጃ ይጋረዳል፡፡በመቀጠል "የትምባው" መሪ ዶሮውን አርዶ የሁለቱ ጎሳ ተወካዮችን እጅ ለእጅ በማጨባበጥ የዶሮ ደም ያስነካል፡፡ በመቀጠል ለተሰበሰቡ ሁለቱ ወገኖች ደም በግንባራቸው ላይ ይቀባል፡፡ ከዚያም ከገዳይና ሟዋች ጎሳዎች ሁለት ተወካዮች ተመርጠው ዓይን ለዓይን ሳይተያዩ አንድ ቢላዋ ለሁለት ጨብጠው ጥቁር በግ እንዲያረዱ ይደረጋል፡፡ በመቀጠል ገዳዩ በልብስ ተከናንበው ወይም ተሸፋፍነው ከነበረበት ይወጣና በበጉ ደም ከሟች ወገኖች ጋር እንዲጨባበጥ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ለተሰበሰቡ ሁለቱ ወገኖች ደም በግንባራቸው ላይ ይቀባል፡፡በመጨረሻ ከታረደው በግ የጎድን አጥንት ከተወሰደ በኋላ በጉ ውሀ ውስጥ ይጣላል፡፡ ትርጉሙም እንደ መረጃ ሰጭዎች "ደምና ውሃ ቀዝቃዛ" ናቸው፡፡ ስለዚህ ጠባችን እንደ ውሃና ደም ይቀዝቅዝ ማለት ነው፡፡ የበጉ አጥንት ሽማግሌዎቹ ባሉበት የአንዱ ጎሳ ተወካይ በአንድ ጎን የሌላው ጎሳ ተወካይ በሌላኛው ጎን ሆኖ ለሁለት አጥንቱ ተሰብሮ ወደ ፀሐይ መግቢያ ይጣላል፡፡ በመቀጠል ከወንዝ ወዲህና ወዲያ ማዶ የነበሩ ሁለቱ ጎሳዎች አንድ ላይ ተገናኝተው ሰላምታ ይጠያየቃሉ፡፡

የአጥንት ሰበራ ተምሳሌቱ እርቁን የሚያፈርስ እንደዚህ "አጥንት ይሰበረው" ማለት ነው ይላሉ መረጃ ሰጭዎች፡፡ ይህ ድርጊት ከተፈፀመ በኋላ የገዳይ ጎሳዎች፣ የሟች ጎሳዎችና የሀገር ሽማግሌዎች በአንድ ሆነው ወደ ሟዋች ሰፈር ያቀናሉ፡፡ ወደ ሟዋች ቤት ከደረሱ በኋላ /የጅምፅዋ/ Jaamas`owa/ ስነ-ስርዓት ይከናወናል፡፡ ጅምፅዋ ማለት ከማሽላ፣ ብቅልና ጆካ ከሚባል የዛፍ ቅርፊት ተፈጭቶ የሚሰራ ዱቄት ሲሆን እንደ መድሐኒትመድኃኒት"/እምነት"/ ነው፡፡ /አቶ ምት ምህ/ (ቃለ መጠይቅ፡ 7 /9/ 2008) ይህ "ጅምፅዋ" ስነ-ስርዓት በሁለቱ ጎሳዎች ግንባርና አንገት አከባቢ ከተቀባ በኋላ በግ፣ ፍየል፣ አቅም ካላቸው በሬ ታርዶ ስጋው ከተበላና ቦርዲ ከተጠጣ በኋላ "የትምባው" መሪዎች /የሀገር

ሽማግሌዎች/ በዳዩንና ተበዳይን ገስፆና መክረው ዳግም ወደ ግጭት እንዳይገቡ ቃል ኪዳን ያስገባሉ፡፡ "የጅም ፅዋና" የግብጃው ስነ -ስርዓት በገዳዩ ቤት በተመሳሳይ ከተደገመ በኋላ የእርቁ ስርዓት ይጠናቀቃል፡፡ ምንም እንኳን ገዳዩ በፍርድ ቤት እስራት ተበይኖበት የእስራት ጊዜውን ጨርሰውጨርሶ ቢወጣ እንኳን ባህላዊ የእርቅ ስርዓት ሳይፈፅም ከህብረተሰቡ ጋር በሰላም መቀላቀል አይችልም፡፡ ከእርቅ በኋላ ሁለቱ ወገኖች /ጎሳዎች/ እንደ ልብ ወጥቶ ለመግባትና ስራቸውን ያለ ስጋት ለማከናወን "የትምባ" ስርዓት ዋስትና ይሰጣቸዋል፡፡

"የትምባ" ሥርዓት በአሁኑ ወቅት በጉሙዝ ህዝብና በሌሎች ብሄረሰቦች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን በመፍታት አዎንታዊ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ የጉሙዝ ብሄረሰብ እርስ በራሱ እና ከሌሎች የመልክዓ ምድር፣ ወሰን ተጋሪ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር የሚያደርገው ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት የሰመረ ይሆን ዘንድ "የትምባ" ስርዓት ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይጋገኛል፡፡ ባህላዊ ስርዓቱ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠረውን እና ሊፈጠር የሚችለውን በኢኮኖሚ ተጽዕኖ የሚመጣ ጭቅና፣ የማኅበራዊ ኑሮ ቀውስ፣ የተዛባና አድሎአዊ አስተዳደር ወዘተ እንዳይሜንና ፍትህን እንዳያዛባ ለመከላከል ይረዳል፡፡ "የትምባ" የግጭት አፈታት ፈጣን፣ ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ ነው፡፡ "ትምባ" የተሰኘው የጉሙዝ ብሄረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓት ዓላማ ቅጣት መጣልና የአጥፊውን ጥፋት ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን በተፈጠረው ግጭት የተዛባውን ማኅበራዊ ግንኙነት ወደ ነበረበት ሰላማዊ ሁኔታ መመለስ ነው፡፡ በእርቅ ወቅት የአገር ሽማግሌዎች ቁልፍ ጉዳዮችን አንጥሮ በማውጣት የወጡትን ቁልፍ ጉዳዮችን በአግባቡ አይቶ መፍተሄ በመስጠትና ተግባራዊነቱንም በመገምገም ለዘለቂ ሰላም እርቁ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ እንዲሁም "የትምባ" ሥርዓት ከመደበኛው የፍትሕ ሥርዓት በተለየ ሁኔታ አሳታፊ እና ማኅበራዊ ፍትሕ እንዲኖር የሚያስችል ነው፡፡

# ጣሂኒዓያ

በቤንሻንጉል ክልል በማኦና ኮሞ ልዩ ወረዳ የሚገኘው ይህ የግጭት አፈታት ስርዓት በኮሞኛ ቋንቋ «ጣሂያዓያ» እና አስታራቂ ሽማግሌዎች ደግሞ«ማስት ጋታ» እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ ማስት ጋታዎች /የአገር ሽማግሌዎች/ ባለጉዳዮችን በዳይና ተበዳይን አገናኝቶ ጉዳዮችን ዓይተው እና ተነጋግረው መፍትሔ የሚያሰጡ፣ የሚያስታርቁ ካሳ የሚገባውን የሚያስክሱ ሲሆን «ጣሂያዓያ» ደግሞ እነዚህ ሽማግሌዎች ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሚያከናውኑት የፍትህ ስራ የሚገልጽ ሂደት ነው፡፡ በአጭሩ«ማስት ጋታ» አስታራቂነትን «ጣሂያዓያ» ደግሞ ከሙጉት እስከ እርቅ ስራውን የሚጠቅሱ ናቸው፡፡ በኮሞ ባህል ሽማግሌዎች በስርቆት፣ በድብደባ፣ በአካል ማጉደል፣ በባልና ሚስት አለመግባባት፣ ግድያና፣ የድንበር ግጭት፣ ይሸመግላሉ ወይም የእርቅ ስራ ይሰራሉ፡፡ "ሚስት ጋታ" /የአገር ሽማግሌዎች/ ወደ ግጭት የገቡ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች፣ ጎጦች፣ መንደሮች ወዘተ የተውጣጡ ቡድኖችን ለመሸምገልና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን የባህል ህጉን ይጠቀሙበታል፡፡ ፋይዳውም ማስታረቅ ብቻ ሳይሆን ሰላምን በዘላቂነት ማስፈን ነው፡፡ ራስን ከራስ ጋር (በአንድ ጎሳ ከሚወሰኑ ግለሰቦችና ቡድኖች መካከል) እና ራስን ከሌሎች ጋር (በኩታ ገጠም መልክዓም ድራዊ ወሰን አልያም ድንበር ዘለል በሆኑ ማኅበረ-ባህላዊ ግንኙነቶች ለምሳሌ በገበያ፣ ቦታ በትም/ቤት፣ በመንገድ ወዘተ) የተፈጠሩ ግጭቶችን ለመዳኘት ፋይዳ ሲኖረው "በጣሂያዓያ" ሥርዓት የሚፈጠረው ሰላምም ዘላቂ እንደ ሚሆን ይታመናል፡፡

በኮሞ ማህበረሰብ በግጭት ውስጥ የነፍስ መጥፋት ወንጀል ሲከሰት ነፍሰ ገዳዩ ወይም ወንጀለኛው ከአከባቢው እንዲሸሽ ይደረጋል፡፡ አለበለዚያ በፖሊስ ተይዘው ወደ እስርቤት ከተላከ በኋላ በአከባቢ አገር ሽማግሌዎች አስተባባሪነት ሟች በገዳይ ጎዋሮ በገለልተኛ ወገኖች /ጎሳዎች/ ይቀበራል፡፡ ለመቃብር ቆፋሪዎች የላብ መተኪያ ፍየል እና ሸዊ የሚባል ባህላዊ መጠጥ ይሰጣቸዋል፡፡ በመቀጠል በአከባቢው ያሉት የአገር ሽማግሌዎች የመጀመሪያ ስራቸው የሚሆነው በሁለቱ ወገኖች መካከል የሚካሄደውን ግጭት/ ማስቆም ነው፡፡በዚህ መሰረት እንዚህ የአገር ሽማግሌዎች የወንጀል ድርጊት የተፈጸመባቸው ጎሳዎች ደም ለመመለስ ካልተሳካ ደግሞ የገዳይ ወገኖችን ሀብትና ንብረት ለማውደም ወደ ገዳዮች ሰፈር ተሰባስበው ለጦርነት በሚሄዱበት ጊዜ በሚመጡበት አቅጣጫ ላይ አስቀድሞ በመጠበቅ "ቀይ ጨርቅ" በመያዝ ጦርነቱ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሥነ - ልቦናዊ ቀውሶችን በማስረዳት፣ የሟች ወገኖችን ለእርቅ ይለምናሉ በዚህን ጊዜ ጠበኞቹ ይረጋጋሉ፡፡ ይህም "ጦርነት አቁም ስምምነት" ይባላል፡፡የአገር ሽማግሌዎች /ሦስተኛ ወገኖች/ ለተበዳይ ወገኖች መልዕክተኞችን ይልካሉ መልዕክተኞችም የሽምግልናው ስርዓት የሚከናወንበትን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት በመወሰን ቀጠሮ ይይዛሉ ይህንንም ለሚመለከታቸው የበዳይና የተበዳይ ወገኖች በማሳወቅ በዕለቱ እንዲገኙ ጥሪ ያስተላልፋሉ፡፡ የገዳይና የተገዳይ ቤተሰቦችና ቤተ-ዘመዶች በተቆረጠላቸው ዕለት የአካባቢያቸውን ሽማግሎች ይዘው ይቀርባሉ፡፡

ከባድ ግጭት የሚያስከትለው አደጋ የከፋ ስለሚሆን በልማዱ መሰረት የተለያዩ እና ውስብስብ የሆኑ ስርዓተ -ክዋኔዎች ይደረጋሉ፡፡እንደ መረጃ ምንጮች የሽምግልናው ስርዓት የሚካሄደው በትልቅ ዋርካ ዛፍ ስር በዕለት አርብ አስታራቂ ሽማግሌዎች /"ሲትጋታ"/ በተገኙበት ነው፡፡ አስታራቂ ሽማግሌዎች በግድያ እርቅ ጊዜ ዘውትር ከሚለብሱት ልብስ የተለየ ረጅም አቡጀዲ ልብስ ለብሰው የእርቁን ስራ ያከናውናሉ፡፡ በእርቁ ዕለት አገር ሽማግሌዎችና ሁለቱ ወገኖች ባሉበት በመጀመሪያ የተጎጂ ወገን የደረሰበትን ግፍና በደል በዝርዝር ለአገር ሽማግሌዎች ያቀርባል፤ በመቀጠል በዳይ በተራው ተጠይቆ ወንጀሉን በምን ምክንያት ተነሳስቶ እንደ ፈጸመ ሀሳቡን ካቀረበ በኋላ የአገር ሽማግሌዎች ግራና ቀኙን በሚገባ በጥልቀት መርምረው በዳዩ ለተጎጂው ካሳ እንዲከፍል ውሳኔ ያስተላልፋሉ፡፡ በመቀጠል ለእረቁ ማሰሪያ ፍየል፣ ጦር፣ እና ለምለም ሳር መሬት ላይ ካስቀመጡ በኋላ ፍየሉ ታርዶ ደሙን በእርጥብ ሳሩና ጦሩ ላይ እንዲጠባጠብ ያደርጋሉ በማስከተል ሁለቱ ደመኞች ወንዶቹም ሴቶችም በጦር፣ በሳሩ እና በፍየሉ ደም ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየሄዱ ይረማመዳሉ ከዚያም በፍየሉ ደም እንዲጨባበጡ ይደረጋል፤ ይህም ከጠላትነት ወደ መልካም ወዳጅነት የሚያሸጋግራቸውና በርካታ የሆኑ ማህበራዊ መስተጋብሮች ቅርጽ እንዲይዙ ያደረጋል፡፡ እርጥብ ሳር የሆነበት ምክንያት የጥሩ ነገረ ገድ፣ ልምላሜና ተስፋ መገለጫ እንድሆነ የመረጃ ምንጮች ገልጸዋል፡፡ በደሙ ሁለቱ ባላንጣ አካላት መጨባበጣቸው ጉዳቱ እንዲደርስ ያደረገ ወይም መጥፎ ተግባርን ከነፍሰ ገዳዩና ከቤተሰቦቹ የማራቅ ትርጉም አለው፡፡ የዚህ ስርዓት-ክዋኔ ትርጉም በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተከሰተ የሚከሰት ጠላትነትደም ለደም መፈላለግንና ይህን እርቅ ያፈረሰ በሕወቱ፣ በንብረቱ እና አጠቃላይ በቤተሰቦቹ ላይ

አስከፊ አደጋ ይደርሳል ተብሎ ስለሚታመን እርቁን ደፍሮ የሚያፈርስ አይኖርም፡፡ ከዚያም ባላንጣ ወገኖች በአንድ ማዕድ ቀርበው እንዲመገቡ ይደረጋል፡፡ ይኸውም ቤተሰባዊነትን መተሳሰብን፣ መፈቃቀድን አንዱ ለሌላው ማሰብን እንዲጀምሩ ሰላምና ፍቅር እንደሰፈን በማሰብ ነው፡፡ የመጨረሻው ሥራዓት- ክዋኔ ሰላም በዘላቂነት እንዲሰፍን የሚያስችል ምርቃት በኮማኛ "ፀጉ" በመስጠት ወደጸብ የሚመራውን የጥላቻ መንፈስ ከግለሰቦቹ ላይ በእርግማን በኮማኛ "ጌፍ" መልክ ይገስጻሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት የሰው ሕይወት ያኋ ወይም የገደለ ሰው ወዲያው በፖሊስ ተይዞ በዘመናዊ የፍትህ ተቋም ውሳኔ ካገኘ በሓላ ዘመዶቹ/ ወገኖቹ / ከሟወች ቤተሰብ /ጎሳዎች /በባህለዊ የእርቅ ሥርዓት ይታረቃሉ፡፡ በስርዓቱ የገንዘብ ካሳ ክፍያ አይኖርም ይልቁንም ነፍስ ገዳዩ ለሞተው ሰው ምትክ ለሟች ወገን ሴት ልጅ እንዲከፍል የአገር ሽማግለዎች ይበይኑበታል ሴት ልጅ ከቤት ከሌላቸው ከጎሳ /ከዘመድ / በብድር መልክ አፈላልጎ ለመክፈል ዋስ ይጠራል፡፡ ልጅቷ ካሳ ከተከፈለች ከአንድ ወር በኋላ የእርቁ ስነ-ስርዓት ይከናወናል በአሁኑ ጊዜ መንግስት ግንዛቤ በመፍጠሩ እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት መሆኑን ማህበረሰቡ ተገንዝቦ ሴት ልጅ ካሳ መክፈሉ ሙሉ በሙሉ ቀርቷል፡፡በእርቁ ወቅት ለሚዘጋጀው ዝግጅት የእህል ዘር እና ለስጋ የሚሆን ፍየል በገዳይ ወገን በአገር ሽማግሌዎች በኩል ከተላከ በኋላ «ሹዊ» የሚባል ባህላዊ መጠጥ፣ ፍየልና የሚበላ ምግብ ተዘጋጅቶ ሁለቱ ወገኖችና የአገር ሽማግሌዎች በተገኙበት ለሁለት ቀናት በገዳይ ቤት ድግሱና ጭፈራው ከተደረገ በኋላ በሟች ቤት ለስድሰት ቀናቶች ይህ ድርግት ተደግሞ አጠቃላይ ስርዓት ይፈጸማል፡፡

የኮሞ ብሄረሰብ ባህላዊ የፍትህ ሥራዓት የሚታወቀው ከትውልድ ወደ ተውልድ ሲተላለፍ በመጣው "ጣሂያዓያ" ህግ ነው፡፡የፍትህ ሥርዓቱ የተጓዳኝ /horizontal/ እንጂ የተዋረድ /vertical/ ደረጃዎች ወይም እርከኖች የሉትም በብሄረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ አብዛኞቹ ግጭቶች በባህላዊ መንገድ እስከ ተፈቱ ድረስ ባለጉዳዮች ይግባኝ የሚጠይቅባቸው ተከታታይ ባህላዊ የፍትህ ደረጃዎች የሉትም፡፡ ሆኖም ችግሮች በመጀመሪያ ሽምግልና ካልተፈቱ እንደገና የሚፈቱት "በጣሂያዓያ" ህግ ነው፡፡ ባለጉዳዮች የሽማግሌዎችን ውሳኔ ያልተቀበሉ እንደሆነ እንደገና ጉዳያቸው ይታያል እንጂ እንደ መደበኛው ፍርድ/ቤት ወደ ላይ የመሄድ አዝማሚያ አይኖርም፡፡

- ባህላዊ የችሎት ክዋኔ በቃል መተላለፉ፣ የችሎቱ መግባቢያ ቋንቋም የአካባቢው ማህበረሰብ የሚግባባበት መሆኑ፣ ለስርዓተ ክዋኔውና ለአፈጻጸም የሚውለው ወጪ አነስተኛ መሆኑ የባህላዊ የፍትሕ ሥርዓቱን በቀላሉ ተግባራዊና ተደራሽ እንዲሆን አስችሎታል፡፡
- በአመዛኙ ውሳኔዎች የሚሰጡት በበዳይ እና በተበዳይ መካከል በሚደረጉ ድርድሮች፣ ስምምነቶች እና በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ ይህም የመቻቻልና የመደጋገፍ ባህል እንዲጎለብት ይረዳል በግጭቱ የሚፈጠረው ቀውስም ይቀንሳል፡፡
- ጣሂዓያ የጋራ ተጠያቂነት መርህ አንጻር ከግለሰብ ጥቅም ይልቅ ለጎሣው፣ ለቤተሰቡ እና ለመንደሩ ደኅንነት እና የጋራ ጥቅም ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱ ለዘላቂ ሰላም ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

# ኔሞ

በቤንሻንጉል ክልል መተከል ዞን የቦሮ-ሺናሻ ህዝብ እንደሌሎች ህዝቦች የራሱ የሆነ ባህላዊ የዳኝነት ተቋም "ኔም" ተብሎ ይጠራል፡፡ "የኔሞ" ተቋም ሦስት የዳኝነት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን እነዚህም፡- "ቡራ" "ኔማ" እና"ቴራ/ጼራ/"ተብሎ ይጠራሉ፡፡ ለእነዚህ የዳኝነት ደረጃዎች የሚበቁና የዳኝነት ስራዎች የሚሰሩ ከህብረተሰቡ ውስጥ በእድሜ የበሰሉ፤ ብልህና የአከባቢውን ወግና ልማድ ጠንቅቀው የሚያውቁ፤ በአስተዳድር ጥበብ የተሻሉ የሆኑ ከብሄረሰቡ "ከዶ-ዋ"፣ "ኢኖሮ"፣ እና "ኢንዲ" ከሚባሉ ታላላቅ የዘር ግንዶች ተመርጠው፤ ተመርቀውና ፍትህዊ አገልግሎት እንዲሰጡ አደራ ተሰጥቷቸው ይሾማሉ፡፡ "ቡ-ራ"፡- እንደ ብሄረሰቡ የዳኝነት ሥርዓት ወንጀለኛን ከመቅጣት በፊት በዳኝነት ደረጃዎች የማጣራት ስራ ይሰራል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የዳኝነት ስርዓት ሂደት ውስጥ እያንዳአንዱ የዳኝነት ሂደትና ይዘት ስንመለከት "ቡ-ራ" የሚባለው በአንድ ታዋቂ ሽማግሌ የሚመራና ጉዳዩ የሚታይበት፤ የሚመረመርበት የመጀመሪያ የዳኝነት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ እንደ ጉዳዩ ክብደትና ቅለት ውሳኔ ሊያገኝ ወይም ወደ ሚቀጥለው የዳኝነት ደረጃ ሊሻገር የሚችል ሲሆን ውሳኔውም በብሄረሰቡ ቋንቋ "ቡ-ሪ ናይር ቆራ" ይባላል፡፡ ትርጉሙም የመጀመሪያ ደረጃ ዳኛ ውሳኔ ማለት ነው፡፡ "ኔማ"፡- ሁለተኛው የዳኝነት ስርዓት ሲሆን በዚህ የዳኝነት ሥርዓት ውስጥ በቡ-ራ የዳኝት እርከን የተሰጠውን በመመርመርና ባለ ጉዳዮችን በማነጋገር ባገኙት ጭብጥ በመነሳት "የቡ-ራን" ውሳኔ በማጽደቅ፣ ወይም በማሻሻል ወይም በመሻር ውሳኔ የሚሰጥበት ሁለተኛ የዳኝነት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ "በኔሞ" የሽምግልና አካል በተሰጠው ውሳኔ ያልረካ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ወደ ሚቀጥለው የዳኘነት እርከን ይግባኝ ጥያቄውን ያቀርባል፡፡ "ቴራ/ዜራ" የመጨረሻውና ይግባኝ የማይጠየቅበት የዳኝነት እርከን "ቴራ/ጼራ" ይባላል፡፡ ይህ የዳኝነት ሂደት በአንድ ሰው የሚፈጸም ሲሆን ከላይ የተመለከትናቸው ሁለቱ የዳኝነት እርከኖች ምርመራ ሂደትና ውሳኔ ከፈተሸ በኋላ በህብረተሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥበት የዳኝነት እርከን ነው፡፡

የቦሮ-ሺናሻ ባህላዊ የሽምግልና አስተዳዳር ውስጥ ከሚታወቁ የቅጣት ዓይነቶች ከግድያ፣ ዘመድ ጋር መጋባትና መሰል ወንጀሎች በስተቀር እንደ ጥፋቱ ክብደትና ቅለት ደረጃ አጥፊ ሆኖ የተገኘው በምክር የሚታለፍ ካልሆነ ጋቢ/ኩታ ወይም የበግ/ፍየል ሙኩት ዋነኛ የካሳ/ የቅጣት ዓይነቶች ናቸው፡፡ በየእርከኑ በሚሰጡ ውሳኔዎች አቀባበልን በተመለከተ ሁሉም የዳኝነት ደረጃዎች የሚሰጠው ውሳኔ በአንድ ዓይነት ወይም የተለያየ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሚሰጡ ውሳኔዎች በባለጉዳዮች ተቀባይነት ባገኙት ደረጃ ላይ ሊገታ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን አንድ በተከሳሽ ዘንድ ተቀባይነት በማጣት እስከ ❑ቴራ/ዜራ/❑ በሚባል የመጨረሻ የዳኝነት ደረጃ ሥርዓት ድረስ ሊሄድ ይችላል፡፡ በዚህ የዳኝነት ደረጃ የተሰጠውን የመጨረሻ ደረጃ ውሳኔ አንድ ተከሳሽ ባይቀበልና አሻፈረኝ ብሎ በእምቢተኝነት ቢገኝ ይህ አሻፈረኝ ባይ በህብረተሰቡ ይቀጣል፡፡

❑ፋላ❑ ማለት ጥፋት የፈፀመው ሰው ቅጣቱን ለመቀበል ንስሃንስሓ የሚገባበት ሂደት እንደሆነ ተደረጎ ይወሰዳል፡፡ እንደ ብሄረሰቡ እምነት ከፍተኛ ወንጀል የሚባለውና በጥንቃቄ ፍርድ የሚሰጠው የሕይወት ግድያ ወንጀል ነው፡፡ ውሳኔውም የሰውን ሕይወት ሆን ብሎ ያጠፋ ከሆነ

ከ7-8 ዓመት ድንገተኛ አደጋ ከሆነ ደግሞ 2-3 ዓመት ከህብረተሰቡ ተለይቶ በጫካ ውስጥ ብቻቸውን እንዲኖሩ፤ ምግብ ከሚያቀርበው ሰው በስተቀር ከማንም ሰው ጋር እንዳይገናኝ ተደርጎ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ ሲሄድም ተረግሞ ሲሆን የእርግማኑ ይዘትም "አውሬ ይብላህ""እሾህና ጋሬጣ ይውጋህ""አትመለስ ሙት" ወዘተ...የሚል ነው፡፡ ሥርዓቱ ተፈፅሞና ተረግሞ ጫካ በሚቆይበት ሰው ካየ ወደ ጫካ ይሮጣል እንጂ ሰው አያገኝም፡፡ ፀጉሩን አይላጭም፤ ገላውን አይታጠብም ጥፍሩን አይቆረጥም፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚገለፀው ስውነቱ ከመቆሸሹ የተነሳ እንዲያሳክከውና ሲፎክትም ሰውነቱ እንዲደማና እንዲቆስል ነው፡፡ ይኸውም በብሄረሰቡ ቋንቋ "ሼር-አማ" ሲሆን ስርዓቱን የሚያስፈፅመው ባህላዊ የንሳሐንሥሓ አባት ደግሞ በብሄረሰቡ ቋንቋ "ጻስ-ነሃ" ሲባል የሥርዓቱ ሂደት "ፉላ" ይባላል፡፡ "የፉላ" ሥርዓት የሚያስፈጽሙ አባቶች "ከጎንጋ ጎሳ"፣ "ኒሂ-ናኦ" ሲሆን "ከዱ-ዎ" ጎሳ ደግሞ "ቆላ" የሚባሉ ዘሮች ናቸው፡፡ ይህን ቅጣት ጨርሶ ለተመለሰ ሰው ከሰርግ ያልተናነሰ የድግስ ዝግጂት በማድረግ በቀኑ ሰውዬው ከጫካ እንዲመጣ ተደርገው ሁለቱ /በዳይና ተበዳይ/ ቤተሰቦች ቀርበው የእርቅና "ደም ማድረቅ" ሥርዓት ተፈጽሞ በምርቃት ህብረተሰቡን ይቀላቀላል፡፡ በዚህ መሰረት ወደ ህብረተሰቡ የተቀላቀለው በቀደም ደመኞች ምንም ዓይነት በደል አይፈፀምም፡፡

በአሁኑ ወቅት ከላይ የተገለፁ ሦስት ደረጃዎችን ባይጠብቅም በአካባቢው ተቀባይነት ባላቸው ሀገር ሽማግሌዎች በሽምግልና ሥርዓቱ አከባቢያዊና ብሄረሰቦች መካከል የሚነሱ ግጭቶችንና ችግሮችን እየፈታ ይገኛል፡፡ የቦሮ-ሺናሻ ህዝብ በቀደምት ታሪኩና በአሁኑ ወቅት "በኔሞ" ሥርዓት ግጭት የሚያስወግድበትና በህዝቡ ውስጥ ወንድማማችነትን፣ መልካም ግንኙነትን ሰላምና መረጋጋትን እንዲኖር እንዲሁም ወንጀለኞችንበማረም የባህል ህጉ ከፍተኛ ሚና እተጫወተ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት ባህላዊ ሥርዓቱ ለልማት፣ ለሰላም እና ደኅንነት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

# አሾራ/አልቡራ

በቤኒሻንጉ ክለል የበርታ ብሔረሰብ አባላት በመካከላቸው የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍፍታት የሚጠቀሙበት የራሳቸው የሆነ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥነ-ሥርዓት አላቸው፡፡ ይህ ሥርዓታቸውም በብሔረሰቡ ዘንድ በአንድ ቀበሌ ውስጥ የሀገር ሽማግሌ ወይም አሽህ /አልቃርያ/ በመባል ህ/ሰቡ መርጧቸው የሚቀመጡ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ የተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎች በቀበሌው እና በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎችን ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ማንኛውም ሰው ሲጣላ የተበደለው ሰው ለቀበሌው ሊቀመንበር ይከሳል፡፡ የቀበሌው ሊቀመንበር ደግሞ ወደ ሀገር ሽማግሌዎች ወይም አሽህ/አልቃሪያ/ ተብለው ለሚጠሩ አስታራቂዎች በመንገር ተሰብስበው ችግሩን እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡ ክሱ ከቀረበ በኋላ የሀገር ሽማግሌዎቹ የሚሰበሰቡት ከለዋ ቤት ውስጥ ወይም ከትልቅ ዛፍ ስር በመቀመጥ ነው፡፡ ከዚያም ከሽማግሌዎቹ ፊት ሁለቱም የተጣሉት ሰዎች ተጠርተው አብረው ይቀመጣሉ፡፡ ሽማግሌዎቹም ታራቂዎቹን እንዲድህ በማለት ይጠይቋቸዋል፡፡ እናንተ ተጣልታችሁ ከርማችሁ ለመታረቅ ከኛ ጋር የመጣችሁት አሁን መታረቅ ነው የምትፈልጉት ወይስ ወደ ዳኛ ነው የምትሄዱት ብለው ይጠይቋቸዋል፡፡ ታራቂዎቹም እኛ በሀገራችን ሽማግሌዎች ስር ነን ወደ ዳኛ አንሄድም እናንተ የምትሉንን በሙሉ እንቀበላለን ብለው ከተስማሙ በኋላ ታራቂዎቹ አንድ በአንድ ይጠየቃሉ።

በዚህም መሠረት ሽማግሌዎቹ ጥላቻውን ማን እንደጀመረው የተናገሩትን ሁሉም ሽማግሌዎች በስርዓቱ ካዳመጧቸው በኋላ ታራቂዎቹን የብቻለየብቻ ተለያይተው እንዲቀመጡ ያደርጋሉ፡፡ ሽማግሌዎቹም የሁለቱን ሰዎች ሀሳብ በማንሳት ይወያያሉ፡፡ ከተወያዩ በኋላ ሁለቱንም ሰዎች ጠርተው አጥፊው አበሉ ነው ተብሎ ይወሰናል፡፡ /አበሉ ማለት እገሌ ነው ማለት ነው/ ከዚያም ያጠፋው ወይም የበደለው አበሉ ስለሆነ እኛ የወሰነውን ይቀጣል ብለው ሲወስኑ በዳዩ /አጥፊው/ ደግሞ እኔ ያላችሁኝን በሙሉ እቀጣለሁ እስማማለሁ ይላል፡፡ ከዚያ በኋላ ሽማግሌዎች ቅጣቱ ከባድ ከሆነ ለወንድሙ አልአደባ /አልአደባ ማለት ወንድሙ ልቡን ነፃ እንዲሆን በፍቃደኝነት መቀጣት ማለት ነው/ 10 /አስር/ ብር እንዲቀጣ ይወስናሉ፡፡ አስር ብር በዱሮ ጊዜ ሁለት ፍየል ይገዛ ነበር፡፡ አጥፊው አስር ብር ከተቀጣ በኋላ የተጋጩት ሁለቱ ሰዎች ሰላም ይባባላሉ፡፡ ከዚያም ተበዳዩ ሰው ብሩን ተቀብሎ ላስታረቁት ሀገር ሽማግሌዎች ሦስት ብር ወይም አንድ ፍየል በአካባቢው ያሉት ዘመዶቹን ጠርቶ ስጋውን በእሳት ይጠብስና ሁሉንም ያስታረቁትን ሰዎች እንዲመገቡና እንድዲጠጡ ያደርጋል፡፡ ከተበላና ከተጠጣ በኋላ ሽማግሌዎቹ ዱዓ ወይም ጸሎት ያደርጋሉ የተጣሉት ሰዎች ለወደፊቱ ተስማምተው በሰላም እንዲኖሩላቸው፡፡ ጥላቻዉ ትንሽ ከሆነ ደግሞ አጥፊው ሰው አንድ ዶሮ ብቻ ነው የሚቀጣው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ግን የተጣሉ ሰዎች ወደ ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመሄድ የጠቡን መነሻ ቃላቸውን ሰጥተው ከተስማሙ ከላይ እንደተዘረዘረው በሀገር ሽማግሌ ይታረቃሉ፡፡ እንቢ ካሉ ደግሞ ወደ ህግ ቀርበው ወንጀለኛው ተቀጥቶ እንዲታረቁ ይደረጋል፡፡ "አሾራ/አልቡራ" ይህ ስርዓት በአሁኑ ወቅት የተጋጩትን በማስረቅና ወደ ነበሩበት ሰላማዊ ግንኙነት በመመለስ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ "አሾራ /አልቡራ"ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ህብረተሰቡ ዘመናዊ ፍትህ አገልግሎት ፍለጋ በፍርድ ቤትና በፖሊስ ጣቢያ በመመላለስ የሚያጠፋዉን ጊዜና ገንዘብ በመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የበርታ ህዝብ ቅራኔንና ግጭት የሚፈቱት ባህላዊ የፍትህ ስርዓት "አሾራ/አልቡራ" ይባላል፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች በቤተሰብ፣ በጎረቤትና በህዝብ መካከል ያሉ ቅራኔዎች እንዳይባባሱ መፍትሔ በማፈላለግ የአካባቢያቸውን ሰላምይጠብቃሉ፡፡

# ሹምቡ

በማኦና ኮሞ ልዩ ወረዳ በማኦ ብሄረሰብ አካባቢ በተለያዩ ጊዜያት የሚከሰቱ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የግጭት ዓይነቶች ይታያሉ፡፡ የብሄረሰቡ አባላት ለእነዚህ ስርዓቶች ተገዢ በመሆኑ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ግጭቶች ቢከሰቱ በጊዜዉና በሰዓቱ ለአካባቢዉ

ሽማግሌዎች በማሳወቅ መፍትሄ ለማፈላለግና ለማግኘት ህዝቡ አስቀድሞ ይንቀሳቀሳል፡፡ በሀገር ሽማግሌዎች ጣልቃ ገብነት የሚፈቱ ቅራኔዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ስላላቸዉ ለእርቁ ተግባራዊነት ህዝቡ በዋናነት የተፈጠሩትን ችግሮች ለመፍታትም ሆነ እርቅ አዉርዶ በየትኛዉም አቅጣጫ በሰላም አብሮ ለመኖር ያለዉ ተነሳሽነትና በእርቅ ዙሪያ ከእምነት አባቶች ጋር ተያይዞ ለመስራት ያለዉ እንቅስቃሴና ሞራል የእርቅ ስርአቱን ምሳሌ እንዲሆን አድርጎታል (ስለ ማኦ ብሄረሰብ ከተጻፈ ብሮሸር ላይ የተገኘ)፡፡ በማኦ ብሄረሰብ ዘንድ ማንኛዉም ግጭት በመኖሪያ አካባቢ፣ በገበያ ቦታ፣ በስራ ቦታ አካባቢ በየትኛዉም የየእለት ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ይከሰታል፡፡ እነዚህ ግጭቶች ሲከሰቱ የብሄረሰቡ ሀገር በቀል ሽማግሌዎች ግጭቱ እንዳይስፋፋ በአፋጣኝ ጣልቃ በመግባት የማስቆምና የማረጋጋት ጠንካራ ባህሉ ዛሬም በማኦዎች ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰራበት ይገኛል፡፡ የሚከሰቱ ግጭቶችና ያስከተሉት ጉዳቶች በሀገር ሽማግሌዎች በጥልቀት ከተመረመሩ በኋላ እንደጥፋቱ ዓይነትና ክብደት የጥፋተኝነት ዉሳኔዎች በማከናወን የሚታለፍበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

በዚህ አይነት በማንኛዉም አቅጣጫ የተፈጠረዉን ግጭት ለሁሉም አማካኝ የሆነ ቦታ ትልቅ ዛፍ ጥላ ስር ሆነዉ እርጥብ ሳር /ቅጠል/ ላይ በመቀመጥ የግጭቱን ዓይነትና መነሻ ምክንያቶችን በዝርዝር መረዳት የበዳይና ተበዳይ ጉዳዮችን በጥልቀት ማዳመጥና መመርመር በግጭቱ ወቅት በቦታ የተገኙትን ግለሰቦች ቃል በጥልቀት መስማት፣ ግጭቱን ለመፍታት በባህሉ  በኩል  ዘዴዎችን ሁሉ በመጠቀም ለማንም ሳያደሉ እዉነትንና ሀሰትን በጥልቀት በመመርመር በባህሉ መሰረት ለተጎጂ ወገን  ትክክለኛዉን ፍርድ በመስጠት በጥፋተኛዉ ላይ እንደጥፋቱ አይነትና ክብደት የጥፋተኝነት ዉሳኔዎች ይተላለፋሉ (Ibid, 2008)፡፡

ከላይ በዝርዝር ማየት እንደተቻለዉ የማኦ ብሄረሰብ ግጭት በግለሰቦች፣ በጎሳና በቡድን መካከል በሚከሰትበት ጊዜ ግጭቱን የሚፈቱበት የራሳቸዉ የሆነ አገር በቀል ባህላዊ ዳጭኝትና የእርቅ ስራዓት አላቸዉ፡፡ ባህላዊ ዳኝነትና የእርቅ ስርዓታቸዉ በዳይና ተበዳይን ፍታህዊ በሆነ መልኩ ፍርድ የመስጠትና እርቅ የመፍጠር ስርዓት አላቸዉ፡፡ በዳዩ /ተከሳሹ ለተበዳዩ/ ለከሳሹ ካሳ እንዲከፍል በማድረግና ሁለተኛ በጠላትነት እንዳይተያዩ በማስጠንቀቅ ማህላ በማድረግ እርቅ እንዲይፈጠር ያደርጋሉ፡፡ የባህላዊ ዳኝነት ትልቁ ፋይዳ በዳዩና ተበዳዩ መካከል ያለዉ ችግር በአከባቢ ሽማግሌዎች በባህላቸዉ መሰረት እርቅ ከተፈጠረ በኋላ ይቅር በመባባል በሰላም አብረዉ ይኖራሉ፡፡ በዘመናዊ ዳኝነት ስርዓት ግን ወንጀለኛዉ በህግ ቁጥጥር ስር ቢዉል እንኳ ከሁለቱ ተቃራኒ ቤተሰቦች መካከል ከመፈላለግና ከመጋጨት አያድንም፡፡ ስለ ማኦ ብሄረሰብ ግጭት አፈታት ይህን ካልኩ በኋላ የግጭት መንስኤዎች፣ የባህላዊ ዳኝነት፣  የእርቅና ፍትህ ስርዓት አንድ በአንድ እንደሚከተለዉ እናያለን በማኦ ብሄረሰብ በአብዛኛዉ የግጭት መንስኤ ተብሎ የሚታወቀዉ የሴት ልጅ ጠለፋ፣ ስርቆት እና የወንድ ሚስት መድፈር ነዉ፡፡ የመረጃ አቀባዮች እንደገለጹልን የሴት ልጅ ጠለፋ በማኦ ብሄረሰብ ዋነኛዉ የግጭት መንስኤ ነዉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የሴት ልጅ ጠለፋ እየቀረ ቢሆንም ድሮ ዋነኛ የግጭት  ምክንያት ሁኖ ቆይቷል፡፡ በተለይ ሴት ልጅ እየተጠለፈች ባለችበት ሰዓት የልጅቷ ዘመዶች ወይም የጎሳ አባለት ዱርጊቱን ካዩ እስከ መገዳደልና የደም መፋሰስ ደረጃ ላይ ይደረሳል፡፡ የሴት ልጅ ጠለፋ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት መሆኑ ታዉቆ መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት የሴት ልጅ ጠለፋ እንዲቀንስ ማድረግ ተችሏል፡፡ ሌላዉ ደግሞ አንድ ሰዉ የወንድ ሚስት ጋር የግብረ ስግ ግንኙነት ሲፈጽም ከተያዘ ወይም ከተጠረጠረ በግለሰቦቹ መካከል ግጭት ይፈጠራል፡፡ ስርቆትም ሌላዉ የግጭት መንስኤ ነዉ፡፡

በማኦ ብሄረሰብ አንድ ሰዉ ህይወቱ በሰዉ እጅ  ቢያልፍ በአካባቢ ሽማግሌ ዕርቅ እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ ሁሉም ነገር በሀገር ሽማግሌ ነዉ የሚጠናቀቀዉ፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች የእርቅ ስነ-ስርዓት የሚያከናዉኑት ከመኖሪያ ስፍራቸዉ ራቅ ብለው ነዉ፡፡ በማኦ ብሄረሰብ ብቀላ ወይም ደም መመለስ በሚል ሰበብ የሌላዉን ሰዉ ዉድ ህይወት ማጥፋት በባህላቸዉ የተወገዘ ነዉ፡፡ የዕርቁ ጥያቄና የዕርቅ ሂደቱ የሚጀመረዉ ከገዳዩ ቤተሰብ ወይም ጎሳ ነዉ፡፡ የሰዉ ህይወት በእጁ ያለፈ ግለሰብ ወይም ቡድንግዲያ በተፈጸመ ማግስት ዘጠኝ ሽማግሌዎችን ይልካል፡፡ ሽማግሌዎች የሚመረጡት ከሦስት የተለያየ ሰፈር /መንደር/  እና ከተለያዩ  ጎሳዎች ነዉ ፡፡ ሽማግሌዎቹ ሄደዉ ለሟቹ ቤተሰብ የተፈጠረዉን ጉዳይ ያስረዱና ግዲያዉ የተፈጸመው በስህተት  በመሆኑ በአካባቢዉ ባህልና ደንብ መሰረት እንድናስታርቃችሁ ሽምግልና ልከዉናል ብለው ሁኔታዉን ያስረዳሉ፡፡ በማኦ ብሄረሰብ አንድ ሰዉ አዉቆም ሆነ በስህተት የሰዉ ህይወት በእጁ ቢያልፍ በሟቹ ምትክ አንድ ሰዉ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ በሞተዉ ሰዉ ምትክ የደም ካሳ የሚሰጠዉ ሴት ሊሆን ይችላል፡፡ የገዳዩ ቤተሰቦች በሞተዉ ምትክ ሰዉ ለመስጠት ከተስማሙ የገዳዩ ቤተሰቦች ለእርቅ የሚሆን ጥቁር ፍየል ይሰጣል፡፡ የሀገር ሽማግሌዎቹ ፍየሉን ያርዳሉ፡፡ የፍየሉን ደም በመራራ የቅል ፋጋ ዉስጥ ይደረጋል፡፡ አስታራቂ ሽማግሌዎች የገዳዩ ቤተሰቦችና የሟቹ ቤተሰቦች በደሙ ያጨባብጣሉ፡፡ ሁለተኛ ግዲያዉ እንዳይፈጸም መህላ ይደረጋል፡፡ መህላ ተፈጽሞ እርቅ ከወረደ በኋላ የፍየሉ ስጋ ይበላል፡፡ ስጋዉ ከተበላ በኋላ አጥንቱ እንዲቃጠል ይደረጋል፡፡ በመራራ ፋጋ የተደረገዉ ደም ከነቅሉ ወደ ፀሐይ መግቢያ አቅጣጫ ይወረወራል፡፡ በመራራ ፋጋ የተደረገዉ ደም ከነቅሉ ወደ ፀሐይ መግቢያ አቅጣጫ የሚጣልበት ምክንያት የዚህ አይነቱ መራራና አሰቃቂ ግዲያ ድጋሚ እንዳይከሰት ለመማጸን የሚደረግ ስርዓት ነዉ፡፡  ይህን ባህላዊ የዕርቅ ወይንም መህላ ህግ ጥሶ በደል የፈጸመ ሰዉ ካለ ማህላዉና የተደረገዉ እርግማን የድርጊቱ ፈጻሚና ቤተሰቦቹን ያጠፋል ተብሎ ሲለሚታመን አብዛኛዉ የብሄረሰቡ አባላት ህጉን አይጥሱትም፡፡

ግጭቶች ሲከሰቱ የብሄረሰቡ ሽማግሌዎች ግጭቱ እንዳይስፋፋ በአፋጣኝ ጣልቃ በመግባት የማስቆምና የማረጋጋት ጠንካራ ባህሉ ዛሬም በማኦዎች ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰራበት ይገኛል፡፡ባህላዊ ዳኝነትና የእርቅ ስርዓታቸዉ በዳይና ተበዳይን ፍታህዊ በሆነ መልኩ ፍርድ የመስጠትና እርቅ የመፍጠር ስርዓት አላቸዉ፡፡ በዳዩ /ተከሳሹ ለተበዳዩ/ ለከሳሹ ካሳ እንዲከፍል በማድረግና ሁለተኛ በጠላትነት እንዳይተያዩ በማስጠንቀቅ መህላ በማድረግ ይርቅ እንዲፈጠር ያደርጋል እያደረገ ይገኛል፡፡ “የሹምቡ” ባህላዊ ዳኝነት ትልቁ ፋይዳ በዳዩና ተበዳዩ መካከል ያለዉ ችግር በአከባቢ ሽማግሌዎች በባህላቸዉ መሰረት መህላና እርቅ ከተፈጠረ በኋላ ይቅር በመባባል በሰላም አብረዉ ይኖራሉ፡፡

# ሳንጋኔና

በትግራይ ክልል የኲናማ ብሄረሰብ የዕርቅ ስነ-ስርዓት  በአከባቢው ቋንቋ መጠርያ 'ሳንጋኔና'ተብሎ የሚታወቀው የማሕበረሰቡ ባህላዊ ሃብት ነው። 'ሳንጋኔና' የሚለው ቃል 'ሳንጋ' እና 'ኔና' ከሚሉ ሁለት ቃላት የተፈጠረ ጥንድ ቃል ሲሆን፤ሳንጋ ማለት 'ኣጥንት' 'ኔና' ደግሞ ዕርቅ የሚል ቀጥተኛ ትርጉም ያለው ሲሆን፤ ብሄረሰቡ የኣንድ ኣጥንት፣የኣንድ ዘር-ሃረግ ሰዎች እና ወንድማማቾች በመሆናችን በመካከላችን ግጭት መፈጠር የለበትም የሚል ኣጠቃላይ መልእክት ያለው ቃል ነው። ይህ የግጭት አፈታት ስርዓት በማሕበረሰቡ ታማኝ በሆኑ፣ተቀባይነት ባላቸው፣ወገንተኝነት በሌላቸውና ትልቅ ቦታ በተሰጣቸው በኣካባቢው ቋንቋ ስኻንዴ ተብለው የሚታወቁ ሽማግሌዎች የሚከናወን ሲሆን፤በዋናነት ከግድያና ኣካል ማጉደል ተያያዠነት ባላቸው ግጭቶችን መሰረት ያደረገ ነው። ወንጀል ፈፃሚው በራሱና በቤተሰቦቹ ሊደርስበት የሚችለው ግብረ መልስ ወይም ብቀላ ለማስቀረትና በፈፀመው ወንጀል መፀፀቱን ለመግለፅ ወንጀሉን ከፈፀመበት ሰዓት ጀምሮ በፍጥነት ወደ ስኳንዴዎቹ ወይም የአከባቢው ሽማግልዎች በመሄድ ከለላ ይጠይቃል። የፈፀመው ነገር ሳይደብቅ በዝርዝር ይነግራቸዋል። ከዚህ በኋላ በስኳንዴዎቹ ግቢ እንዲቆይ ይደረጋል። ማለትም ከለላ ይደረግለታል። በሱም ሆነ በቤተሰቦቹ ዘንድ አንዳች ጉዳት አይደርስም። የወንጀል ፈፃሚ ቤተሰቦችና ወንጀል የተፈፀመባቸው ቤተሰቦች ተጠርተው ከመጡ በኋላ በተሰየመው መድረክ መተማመንና ይቅር መባባል መንፈስ የሚፈጥሩ ንግግሮች ከተደረጉ በኋላ  በዳዩ እንደየ ጉዳቱ ክብደትና የኑሮ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ካሳ ለተጎጂው ቤተሰብ እንዲከፈል ይደረጋል። ከዚህ ባሻገር ቂም በቀል እንዳይኖር ድግስ ተደግሶ በሃገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች የምረቃ ስነ ስርዓት ይደረጋል። በመጨረሻ በዚህ ስርዓት የማይገዛ የማሕበረሰቡ አካል ቢገኝ ከማህበረሰቡ እንዲገለል ይደረጋል። ወጪ ከመቆጠብ፣የወንድማሟችነት ስሜት ከማሳደግ እነዲሁም ብቀላ ከመቀነስ ረገድ ባጠቃላይ ሰላም ከማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና ያለው ባህላዊ ሃብት ነው።ባህላዊ ሃብቱ በማሕበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ቢኖረውም ከትውልድ ወደ ትውልድ በአግባቡ ስላልተሸጋገረ በመሞት ደረጃ ላይ ይገኛል።

# ደመርግራ-ገረቦ

በደቡብ ምስራቅ ትግራይ አከባቢ የሚገኘው ይህ ደመር ግራ-ገረቦ (ደመር ወጀራት ዕስራ ዓዲ) ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ነው። የአከባቢው ማሕበረሰብ በማሕበረሰቡ ውስጥ ይሁን ከማሕበረሰቡ ውጭ ወይም ከአጎራባች አከባቢዎችና ክልሎች ጋር በሚያደርጓቸው ዕለታዊ እንቅስቀቃሴዎች ላይ የሚያጋጥማቸውን ግጭቶች 'ቃንጭን ሓቅን' ማለትም ሓቅ እና እኩልነት የሚለውን መርህ ተከትለው በሚመርጧቸው የአከባቢው ሽማግሌዎች የሚዳኙበት የግጭት አፈታት ስርኣት ነው። ሽማግሌዎቹ በተሰጣቸው ኃላፊነት መሰረት በአከባቢውና በአጎራባች ህዝቦች መካከል ችግር እንዳይፈጠር በእለትተእለት እንቅስቃስያቸው መረጃዎች በመለዋወጥአስቀድመውለመከላከል ከተከሰተም በፍጥነት መፍትሄ እንዲበጅላቸው በማድረግ የአከባቢውን ሰላም አስጠብቆ በትጋት በመስራት ያለምንም አድልዎ በታማኝነት ማሕበረሰቡን ያገለግላል። በኣከባቢው ችግር ሲፈጠር የጎጡ ወይም የጣብያው ማሕበረሰብ ሰው ግራ-ገረቦ በሚባለው ቦታ እንዲሰባሰብ ይደረጋል። ችግር መፈጠሩ የሚታወቀውም በጥቆማ አመካኝነት ለአፈርጭቃ በሚደርሰው መረጃ፣ተጎጂው በሚያመለክተው አቤቱታ ወይም ጉዳት ባደረሰው ኣካል የሚሰጠው መረጃ ሊሆን ይችላል። ህዝቡ በተሰበሰበበት መድረክ ወንጀለኛው ካልቀረበ የወንጀል ፈፃሚው ጎጥ ወይም ጣቢያ ነዋሪዎች ኣጋልጠው እንዲያቀርቡት ይጠየቃሉ። ወንጀል ፈፃሚ ባለበት ጎጥ ያለው ኣፈር ጭቃም ወንጀለኛው እንዲያቀርብ ይደረጋል። ወንጀለኛው መቅረብ ካልቻለ ወንጀል የተፈፀመበት ጎጥ ነዋሪ በሙሉ ለቅጣት ይዳረጋል። በመሆኑም ነዋሪዎቹ የቅጣቱ ሰለባ ላለመሆን፤የጎጡ መልካም ስም እንዳይጠፋ ወንጀለኛውን ለማቅረብ ከፍተኛ ርብርብ ያደርጋሉ። በዚህ ሂደት ወንጀለኛው ሳይጋለጥ ቢቀር ሁሉም ኣፍርጭቃዎች በየጣቢያው በሚገኙ ነዋሪዎች ጋር በመሆን ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የሚታሰበውን ግለሰብ ቤተሰቦች፣ዘመድ ወዳጆች በማውጣጣት ለፍርድ እንዲቀረብ የማድረግ ስራ ይካሄዳል። በዚህ ሁኔታ ወንጀለኛው ተጠርቶ የሚቀርብ ሲሆን ህዝቡን ያደከመበትን ከግምት በማስገባት ከመደበኛው ከፍ ያለ ቅጣት ይሰጠዋል። ቀለል ያለ ጥፋት ከሆነ ምህረት ይደረግለታል ካልሆነም እንደየ ጥፋቱ ክብደት ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል። በመጨረሻም በሽማግሌዎቹና በሃይማኖት መሪዎች የምርቃት ስነ-ስርአት በማድረግ የፍትሕ ሂደቱ ይጠናቀቃል። ባህላዊ ሃብቱ በማሕበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ እስከ ኣሁን ኣገልግሎት ላይ እየዋለ ነው። ወጪ ከመቆጠብ፣የወንድማማችነት ስሜት ከማሳደግ እንዲሁም ብቀላ ከመቀነስ ረገድ ባጠቃላይ ሰላም ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና ያለው ባህላዊ ሃብት ነው።

# ገረብ

በአፋርና በዋጅራት ሕዝቦች መካከል ግጭትና አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችል የጋራ ተቋም ሲኾን ከሁለቱም ሕዝቦች የተውጣጡና «አቦ ገረብ» (በቀጥታ ትርጉሙ የወንዝ አባት) የተሰኙ አባቶች የሚመሩት ባህላዊ ተቋም ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ወንድማማች ሕዝቦች በአስተዳደራዊ ወሰን የተለያዩ ይኹኑ እንጂ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት የሚገናኙ ናቸው፡፡ የአፋርና የዋጅራት ሕዝቦች በገበያ እና በጋራ የግጦሽና የውሃ ሥፍራዎች የሚጠቀሙ፣ እንዲሁም በጋብቻ ጭምር የተሳሰሩ ሕዝቦች እንደመኾናቸው (Abraha 2012) በባህል፣ በቋንቋ እና ማኅበራዊ ሕይወት የሚጋሩ ብሎም በዚህ «ገረብ»  በተሰኘው የጋራ ባህላዊ ተቋም ግጭቶችን የሚፈቱ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ይኸው ሥርዓት በዋጅራትና በራያ አዘቦ፣ በዋጅራት እና በተቀረው ትግራይ መካከልም ግጭቶች፣ ግድያ፣ የከብት ስርቆት፣ ዝርፊያ፣ ደፈራ፣ ጠለፋ፣ የግጦሽ መሬት መጣስ፣ ወዘተ ሲከሰቱ ግጭቶች የሚፈቱበት ተቋም ነው (Assefa 2016፣ ገጽ 154)፡፡ የዚህ ተቋም ዓይነተኛ መገለጫና ትልቁ ፋይዳው ችግሮችን፣ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን ድንበር-ዘለል በኾነ ባህላዊ ሥርዓት መፍታት መቻሉ ነው፡፡ በዚህ ሥርዓት ከሦስት እስከ 12 የሚደርሱ አቦ ገረቦች ማኅበረ-ህላዊ ጥበቦቻቸውን ተጠቅመው ችግሩን በሚገባ ከመረመሩ በኋላ ለተበዳይ ፍትሕን፣ በዳይን ደግሞ ተገቢውን ቅጣት የሚሰጡ ብቻ ሳይኾን በሁለቱ ወገኖች መካከል የጋብቻ ትስስርን (Assefa 2016፣ ገጽ 156) የመሰሉ መፍትሄዎችን በመጠቀም ከግጭቱ በኋላ ቂም እና በቀል

እንዳይቀጥል ዘላቂ እርቅ እንዲሰፍን ያደርጋሉ፡፡

# ባይቶ

ባይቶ በትግራይ ክልል ካሉ ማኅበረ-ፖለቲካዊ አደረጃጀቶች መካከል ተጠቃሽ ሲኾን በመንደር ደረጃ ነዋሪዎችን በተወካይ ወይም በእንደራሴነት ኃላፊነት የሚሰጥ ለዘመናት የዘለቀ ተቋም ነው፡፡ የቃሉ ትርጉም በአንድ በኩል ከፍትኅሕ ወይም ፍርድ ቤት ጋር ሲገናኝ በሌላ በኩል ሥርዓቱ የሕዝብ እንደራሴዎችን ወይም ተወካዮችን የሚያቅፍ በመኾኑ በጥቅሉ በመንደር ደረጃ ያለ ምክር ቤት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ሥርዓት ግጭትና አለመግባባትን ከመፍታት ባሻገር ማኅበረሰብን በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ እንቅሳቃሴዎች የሚያሳትፍ ነው፡፡ በዚህ ተቋም ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የእረሻ መሬት ክፍፍል እና የአፈርጥበቃ ሥራዎችን ማስተባበር የሚመለከቱ የልማት ሥራዎች ተጠቃሽ ናቸው (ብሩስ 1993 በ ሽመልስ እና ታደሰ 2008 እንደተጠቀሰው)፡፡ ይህ ማኅበራዊ ሀብት በክልሉ የማዕከላዊ መንግስቱ መደበኛ የፍትሕ ሥርዓት እንቅፋት ሲገጥመው አለያም በተለያዩ ምክንያቶች ሲቋረጥ ማኅበረሰቡ ለባይቶ አስተዳደርና የፍትሕ ሥርዓት ተገዢ መኾኑ የተቋሙን ሁለገባዊ አገልግሎትና በሕዝቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ያሳያል (ሽመልስ እና ታደሰ 2008)፡፡

# መድኣ

በአፋር ክልል የአፋር ብሔረሰብ የፍትህ ስርአት መጠሪያ ስም /መድኣ/ ተብሎ ይታወቃል። መድአ በአፋር የባህል ስርአት ውስጥ የህግና የዳኝነት ስርአት ለይቶ ይመለከታል፡፡ የህዝቡ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች የሚወሰነውና የሚቀርበው በህዝብ የባህል ህግ ሰርአት ነው። ይህ ማለት ማህበራዊ፤መንፈሳዊ፤ኢኮኖሚያዊ፤ፖለቲካዊ እና ፍትሀዊ የዳኝነት ጉዳዮች እንዲሁም የህዝቡ እሴቶች የሚቀርቡበት እና ስርአት የሚይዙበት የባህል ህግ መድአ ነው። የመድኣ ስራዓት በውስጡ የህግ አውጪ፤ የህግ ተርጓሚና የህግ አስፈጻሚ አካላትንና ሚናቸውን ጭምር የሚዘረዝር ስለሆነ ልክ እንደ ገዳ ስርአት ሀገር-በቀል የዴሞክራሲ ተቋም ነው ማለት ይቻላል። አፋሮች በመድኣ ስርአት አምካኝነትና በጎሳ ትስስር ወንጀል ይከላከላሉ፤ ማህበራዊ መስተጋብር ያጠናክራሉ፤ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋም ሲያጋጥም በቶሎ ኃይልና ሀብት በማሰባሰብ ያገግማሉ አንደዚሁም የውጭ ወረራና ጠላትን ይመክታሉ። ይህ ማህበራዊ ሃብት በአሁኑ ሰዓት በገጠር የአፋር ህዝብ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የሚጠቀመውና ያልተሸረሸረ ማህበረ-ባህላዊ ዕሴት ነው።

# ማሮ

ማሮ ማለት በአፋር ክልል የአፋር ብሔረሰብ ግጭት ለምፍታት በዛፍ ጥላ ስር የተሰየመ የሽማግሌዎች ጉባኤ ወይም ሸንጎ ማለት ነው። በአፋር ባህል ግጭት የሚፈቱና እርቅ የሚያወርዱ ዳኞች ማካባንይባላሉ። እነዝህ ማካባኖቹ እጅግ ከተከበሩት ከጎሳ ምሪዎች (ከዶ) ተብሎ ከሚጠሩት ጋር አብሮ በመስራት የህዝቡን ሰላም ያስጠብቃሉ። በመድኣ ህግ መሰረት ማካባኖች (ዳኞች) ማንኛዉንም ግጭት (የቤተሰብ ፣ነፍስ ግድያና የጎሳ) ግጭቶችን የፈታሉ አንደዝዚሁም እርቅ ያወርዳሉ። በአንድ ጎሳ ውስጥ ግጭት ቢቀሰቀስ ገለልተኛ ማካባኖች ከሌላኛው ጎሳ ተመርጠው ነው የሚያስታርቁት። የማሮ ተቋምና መድኣ የፍትህ ስርአት የድንበር ግጭቶችን ከትግራይ፤ ከኢሳና ከኦሮሞ በሄረሰብ ጋር ከተፈጠረም ጭምር ይፈታሉ፣ እርቀ ሰላም ያወርዳሉ። እነዚህ የፍትህ ስርአቶችና ተቋሞች በሁሉም ዓይነት የህብረተሰብ ችግሮች ላይ መፍትሄ የሚሰጡ ዳኞች፤ስልጣኖች፤የጎሳ መሪዎች በሚሰጡት ውሳኔ መሰረት ፀጥታ ማስከበርና ወንጀል መከላከል ያስችላል፡፡ እነዚህ የባህል ህጎች ከማንኛውም አካባቢ በበለጠ መልኩ ያልተሸረሸሩና አሁን በስራ ላይ ያሉ ህዝቡ የማያምንበት የሚያምንባቸው የሚገለገልበት ተቋማት ናቸዉ።

# አፊኒ

አፊኒ በሲዳማ ክልል ለሲዳማ ህዝብ እንደ ማኅበረሰብና እንደ ትውልድ ለዘመናት ጠብቆና ተንከባክቦ ያቆየው የራሱ የሆነ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ነው። በሲዳማ ባህል በግጭት አፈታት ስነስርዓት ውስጥ ሀሳብን የማንሸራሸር ስልት ዋነኛው ነው የህም አፊኒ ይባላል። ይህም ቀጥተኛ የአማርኛ ትርጉሙ “ስማችሁ ወይ” እንደ ማለት ነው። ሙሉነህ ካሳ የፎክሎር (በባህል ጥናት) ባለሙያ በአዲስ ዘይቤ ዲጅታል መጽሔት፣ ሐምሌ 30፣ 2013 ባወጣው እትም ላይ ስለ አፊኒ የሚከተለውን ዘገባ አስቀምጧል። በአፊኒ ስርአት መሰረት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ግለሰቦች ወይም አካሎች በሸንጎ ውስጥ በውይይት ወይም በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንዲሳተፉ ዕድል የሚሰጥ መንገድ ነው። ሀሳብን ለማንሸራሸርና ለማሰባሰብ ጊዜ ለማግኘት ጭምር የሚረዳ የንግግር መሳሪያም ነው። በሲዳማ ባህል ሰዎች ሲናገሩ “አፊኒ” ሳይባል ጣልቃ አይገባም። በሌላ መልኩ አንድ የተበደለ ሰው ማንኛውም ዓይነት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት በአጠገቡ ላሉት ወይም ለታላላቆቹ “አፊኒ” በማለት ማሳወቅ ባህላዊ ግዴታው ነው። ይህንን ሳያደርግ በግብታዊነት እርምጃ የወሰደ እንደሆነ ቅጣት ይጣልበታል። አጥፊው ቅጣቱ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት እንዲያጣ ስለሚያደርገው ከባድ ይሆንበታል፡፡ ከቅጣቶቹ ውስጥ እድር፣ እቁብ ወይም ሌሎች ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያለውን ሥልጣንና ተሳትፎ እንዲያጣ፣ እንዳይሸጥ እና እንዳይገበይ፣ ልጆቹን እንዳይድር የሚከለክሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

አፊኒ እውነትን ከማፈላለግና ከፍትሕ አሰጣጥ ጋር በእጅጉ ይተሳሰራል። እውነትን በማጣራትና በማረጋገጥ ወደሚቀጥለው እርምጃ ለመራመድ አፊኒ ወሳኝ መንገድ ነው። በአፊኒ ስርዓት መሠረት ሽማግሌዎች ቁጭ ብለው “halaale” (እውነትን የማውጣት) ስራ ይሰራሉ። ይህም

የሚሆነው አፊኒ በጉዳዩ ላይ እውቀት ያለው ማንኛውም ሰው መረጃ እንዲሰጥ ሰፊ እድል ስለሚሰጥ ነው። በመሬት፣በድንበር፣በትዳር፣ነፍስ በማጥፋት፣በጠለፋ፣የሰው ሀቅ በመብላት፣... ስሞታ የቀረበባቸው ጉዳዮች ወደ ሕግ ከማምራታቸው በፊት በሲዳማ ባህል በአፊኒ ስርዓት ይዳኛሉ። በማኅበረሰቡ ዘንድ ግጭቶች በአፊኒ የመፈታት እድላቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል ግጭት ቢፈጠር፤ ተጎጂው አካል አጠገቡ ላሉ ሰዎች አፊኒ (ሰማችሁ ወይ) መበደሌን ብሎ ስሞታውን ያሰማል። አፊኒ ከተባለ በኋላ ግጭት ይረግባል። ወቃሽ እና ተወቃሽን የመለየት እንዲሁም ችግሮችን የመፍታት ስራ ነው የሚሰራው። ይህ ሀብት በአብዛኛው በገጠሩ የስዳማ አከባቢ ግልግላት እየሰጠ ይገኛል።

# ጉዱማሌ

የጉዱማሌ ተቋም በሲዳማ ክልል በሲዳማ ብሔረሰብ ግጭት የሚፈቱበትና እርቅ የሚያወርዱበት ስርአት ነው። ይህ ተቋም በሲዳማ ክልል በሀዋሳ ወረዳ አካባቢ የሚዘወተር ነው። ጉዱማሌ የሚለው ቃል ቀጥተኛ ፍቺው የፍትህ ቦታ ማለት ነው። ጉዱማሌ ከፍተኛ የግጭት ጉዳዮች እና የይግባኝ አቤቱታዎች የሚሰሙበት ከፍተኛው የፍትህ አካል ነው። ጉዱማሌ አሊቃ የጎሳ መሪው ሲሆን ሞቲ ተብሎ ይጠራል። ጉዱማሌውን የሚመራው ጎሳ መሪ ጉዱማሌ ሞቲቻ ይባላል። የጉዱማሌ ካውንስል ከሞላ ጎደል ሁሉንም ከአካባቢው ማህበረሰቦች ውስጥ እና አንዳንዴም ከውጪ የሚነሱ አለመግባባቶችን ይመለከታል፤ ግጭቶችንም ይፈታል። የክርክር ጉዳዮች እንደየ ክብደታቸው ይመደባሉ፡፡ ጥቃቅን ጉዳዮች ለምሳሌ ስርቆት፣ የግለሰብ ጸብ፤ የቤተሰብ አባላት መካከል አለመግባባት (ለምሳሌ ባልና ሚስት፣ በወንድማማቾች መካከል)፣ ከብቶች ወይም ሰብል በማውደም እና በእርሻ መሬት ወሰን ላይ የሚነሱ አለመግባባቶች ይገኙበታል። ከባድ ጉዳዮች የግድያ ወንጀል እና በጎሳ መካከል የሚነሱ ግጭቶችን ያካትታሉ። እነዚህን ሁሉ የጉዱማሌ ካውንስል ይዳኛል።

ረቡዕ እና ቅዳሜ የጉዱማሌ ምክር ቤት ወደ ጉዱማሌ (የፍትህ ቦታ) ይወጣሉ። ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ ሞቲቻ እና የምክር ቤቱ አባላት በአንድ ዛፍ ስር መሬት ላይ ይቀመጣሉ። እነሱን ተከትለው ችሎቱን ለመከታተል ከተለያዩ መንደሮች የሚመጡ የሀገር ሽማግሌዎች የምክር ቤቱን አባላት ዙርያዉን ከበው ይቀመጣሉ። ማንኛውም ወንድ አላፊ አግዳሚ እነሱን መቀላቀል፣ መመልከት እና ሂደቱን መከታተል ይችላል። ሴቶች ወደ ጉዱማሌ እንዲመጡ አይፈቀድላቸውም። አንዲት ሴት ችሎት በሌለበት ቀናት እንኳን የጉዱማሌ ቦታ ማቋረጥ ኃጢአት እንደሆነ ይታመናል። የስርአቱ መሰረታዊ ዓላማ በተከራካሪ/በተጋጩ ወገኖች መካከል ሰላምና እርቅ መፍጠር ነው። ሆኖም፣ ቅጣትና የዉሳኔ ተፈጻሚነትን በተመለከተ፣ በተለይ ለከፍተኛ ወንጀሎች የተወሰኑ የተለመዱ ህጎች አሉ። ከዚህ አንፃር በግድያ እና በአካል ጉዳት ጉዳይ ላይ የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎችን የሚደነግግ ፊታ የሚባል ህግ አለ። እንደማንኛዉም የሽምግልና ስርአት ጉዱማሌ ተቋም በዳይ ለተበዳይ ካሳ በዓይነት/በገንዘብ ወይም በከብት እንዲከፍል ያደረጋል። የጉዱማሌ ሞቲቻ ውሳኔ አልቀበልም ላለ ግለሰብ የተለያዩ ቅጣት ይጣልበታል። እነዚህም በሴራው (የጉዱማሌው ህግ) መሰረት ከማህበራዊ ህይወት ተሳትፎና ከህዝብ ሀብት ተጠቃሚነት ከማግለል፤ ከአካባቢው እስከ ማባረር ሊደርስ ይችላል። ይህ ሀብት በአብዛኛው በገጠሩ የሲዳማ አካባቢ ግልጋሎት እየሰጠ ይገኛል።

# ሀላሌ

ሀላሌ (Halaale) በሲዳማ ክልል ለሲዳማ ህዝብ በእውነት የመኖር መርህ ነው፡፡ ሀላሌ ማለት “እውነት” ማለት ነው፡፡ የሰዎችን ሀቅ ያለ ውሸት፣ ያለማዳላት፣ ለራስ ብቻ ከማለት ይልቅ እኔ የምፈልገውን ነገር ባልንጀራዬም ይፈልጋል በማለት በእውነት ህሊና መመላለስ ማለት ነው፡፡ የሀላሌ መርህ የሰዎችን፣ የእንስሳቶችንየእንስሳትን በአጠቃላይ የተፈጥሮ መብት ከማክበርና ከማስከበር ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ በሁሉም ማህበራዊ ፖለትካዊና እኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ በስፋት በ ሀላለ በመመላለስ ማህበረሰቡ እርስ በርስ ያለዉን ትስስር እንዲያጠናክርና በህዝቦች መካከል መተማመን እንዲኖር በማድረግ ሚናዉ የጎላ ነዉ። ስለሆነም ግጭት ለምፍታትና ለእርቅ ብቻ ሳይሆን ለአብሮነት፤ ለሰላምና ለደሞክራሲ ስርአት ግንባታ እጅግ ወሳኝ ማህበራዊ ሃብት ነው። ሀላሌ በማህበረሰቡ ዘንድ እስከአሁን ድረስ ተቀባይነት ያለው እሴት ነው።

# ያካ

ያካ (Yakka) በሲዳማ ክልል ስሲዳማ ህዝብ ወንዶች በሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ገደብ የጣሰና አስነዋሪ ድርጊት ሴቶች በጋራ በመሆን ለማውገዝና ለመቅጣት የሚገለገሉበት የተቃውሞ ሥርዓት ነው፡፡ የሚመራውም “ቃሪቾ” (Qaricho) በተባለች የሴቶች መሪ አማካኝነት ሲሆን በትዳር ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ሴቶች የሚያቅፍ ነው፡፡ ሥርዓቱ ማህበራዊ ፋይዳው ከፍተኛ እንደሆነ ይነገራል፤ ዓለም እንደ ዛሬው ባልሰለጠነበት ጊዜ የሲዳማ ሴቶች መብታቸውን የሚያስከብሩበትና የቋያቸውንየቀዬአቸውን ሰላምና ደህንነት የሚጠብቁበት ሥርዓት በመሆኑ ሴቶች ሰላማቸውና ደህንነታቸው ከቤት ጀምሮ ሲከበር እንደ ሀገር ሰላም መሆን ስለሚቻል ሚናው በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ምንም እንኳ ስርአቱ የሴቶችን መብት በማስጠበቅ ለሰላምና ዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሚናው የጎላ ቢሆንም የያካ ሥርዓት በአሁኑ ጊዜ ተዳክሟል ማለት ይቻላል፡፡

# ሉዋ

ሉዋ (Luwa) የሲዳማ ብሔር አባላት የሆኑ ወንዶች ከየጐሳቸው ተወጣጥተውና በትውልድ ዑደት ተደራጅተው በማህበረሰቡ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ የላቀ ተሳትፎ ለማድረግ የሚሰበሰቡበት ባህላዊ ተቋም ነው፡፡ የሉዋ ሥርዓት በአባልነት የሚያቅፏቸው ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ጥንካሬን፣ አርአያነትን፣ አስታራቂነትን፣ ለሰላም መቆምን ወዘተ ያሉ በጐ ምግባሮችን እንዲቀስሙ ያደርጋል፡፡ ሕዝቡን ከውጪ ጠላት ወረራ የመከላከል ተግባር በሉዋ አባላት ይመራል፡፡ በአንድ የሉዋ ስልጣን ዘመን በማህበረሰቡ መካከል ሰላም፣ ደህንነትና አንድነት እንዲሰፍን የሉዋ ሥርዓት መሪዎች በተለይም ጋዳና "Gadaana" ከፍተኛ ሃላፊነትን ይጣልበታል፡፡ ሉዋ በተለያዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ማህበረሰቡን የሚወክሉ አዋቂ ሰዎች የሚወጡበት ተቋም በመሆኑ ግጭት ለመከላከል፤ ለሰላም ግንባታና፤ ለአብሮነት ያለዉ ሚና ከፍተኛ ነዉ። ሆኖም ግን የሉዋ ሥርዓት በአሁኑ ሰዓት እየተዳከመና እየቀዘቀዘ የመጣ ስርዓት ነዉ።

# ደረ-ዱለታ/ደረ-ዎጋ

ደረ-ዎጋ ወይም ደረ-ዱለታ በድቡብ ክልል በጋሞ፤ በጎፋ፤ በወላይታና በዳውሮ ብሔረሰቦች ዘንድ የሚዘወተር የግጭት መፍቻ ስርአት ነው። ደረ-ዎጋ የአከባቢው ባህላዊ ህግ ሲሆን አስታራቂ ሽማግሌዎች ደግሞ ደረ-ጭማ ይባላሉ። ደረጭማዎች ማንኛዉንም ግጭት( የግለሰብ፤ የቤተሰብ፤ የጎሳ፤ የድንበር፤ የመሬትና ሊሎች) ግጭቶችን የፈታሉ። እርቅም ያወርዳሉ። በወላይታ አካባቢ ጫቆ፤ ከመሐላ ጋር የሚመሳሰል፤ እንዲሁም ጭማተታ (ሽምግልና)ስርአቶች አሉ። እነሱም በዋናነት የጎሳ አለመግባባቶችን ለመፍታት እንዲሁም ከግጦሽ መሬት፣ ድንበር፤ የከብት ስርቆት እና የመሳሰሉት ወንጀሎች ጋር በተያያዘ የሚፈጠር ግጭት የሚፈቱበት ስርአት ነው። እነዚህ ተቋማት የራሳቸው አደረጃጀት፤ መዋቅርና የአተገባበር ሂደቶች አሏቸው። በጋሞ ብሔረሰብ ዘንድ ከዋኔው ሽማግሌዎች እርጥብ ሳር በመያዝ ተንበርክከው ግጭቱ እንዲቆም በመጠየቅ ሲከወን ወጣቶችም ሆኑ ማንኛውም የአካባቢው ነዋሪ የማህበረሰብ ክፍል ይህንን የሀገር በቀል እውቀቶቻችን ውጤት የሆነውን ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ መንገድ አምኖና ተቀብሎት በማክበር ይፈፅመዋል፡፡ ይህ ሥርዓት በአዲስ አበባ በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች የብሔረሰቡ አባላት ሰላም ለማውረድ በየክፍለ ከተማው የሀገር ሽማግሌዎች ቡድን ተመስርቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

# ውርሳ

በደቡብ ክልል በባስኬቶ ብሔረሰብ ዘንድ "ውርሳ" የሚባል የባህላዊ አስተዳደር ሥርአት አለ፡፡ በዚህ ሥርአት ዉስጥ በስልጣን ተዋረድ መሰረት በየደረጃው ግጭቶችን የባህል መሪዎች ይመለከታሉ። የሁሉም ባህላዊ ስልጣኖች የበላይ ዳኛ "ካቲ" ሲሆን የነፍስ ግድያ፤ የአካል መጉደል እና ከአንድ ጎሳ ውስጥ ጋብቻን ይዳኛሉ። በካቲው የመጨረሻው እርቅ እና የሰላም የመጨረሻው ውሳኔ ይካሄዳል። ውርሳ ወይም ጎሜውርሳ በግጭት ምክንያት የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት የሚረዳ ነው፡፡ በባስኬቶ ብሄረሰብ ዘንድ በርካታ (45) በላይ ጎሳዎች ቢኖሩም ዓበይት 4 ካቲቾች አሉ። ሁሉም በየጎሳው ስልጣን ተዋረድ ግጭቶችን ይዳኛሉ። ይህም ጎሜ እንዳይኖር ውርሳ ይካሄዳል። ዲና፡ የቤት ማቃጠልን፤ የመሬት ግጭትን፤ የተለያዩ ሰብሎችን ከብቶች መብላት፤ እንዲሁም ጉዳ፤ ቢታና በየደረጃው ግጭቶችን ይዳኛሉ በዚህም ያልረካ ጉዳዩን እስከ ካቲው ድረስ ይዞ መቅረብ ይችላል። እርቅ ሥነ-ሥርዓቱ ሲያልቅ ሁሉም በየጎሳው ስለሚያካሂድ ስጋ በእሳት በመጥበስ ሁለቱ የተጋጩ ግለሰቦች በጥርሳቸው በመያዝ የባህል መሪው በስለት ይቆርጡታል። የጥርስ እና የአካል መጉደል የበግ ወይም የፍየል መንጋጋ በእሳት ውስጥ በመጥበስ ለእርቅ ስርዓቱ ይጠቀሙበታል። የካሳ ስርዓቱም የሚወሰነው በባህል መሪዎች እና በእርቅ ሸንጎው ነው። ይህ ስርአት አሁንም እየተተገበረ ይገኛል ሆኖም በዘመናዊ ዳኝነት ስርዓት እየተዳከመ ነው። ጥበቃ እና የእሴቱ ልማት ማጠናከር ይጠበቃል። ይህ ስርአት በባህላዊ መንገድ ስለሚከናወን በቀል እና ቁርሾን በሙሉ ያደርቃል። የቅጣቱ ክብደት ሳይሆን የባህል ስርዓቱን በማክበር ሕዝቡ ሰላሙን ጠብቆ በስምምነት እንዲኖር ያደርገዋል።

# ኺታኺላቴ

ይህ ባህላዊ ዳኝነት ስርአት በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት በኧሌ ልዩ ወረዳ በኧሌ ብሔረሰብ የጎሳ መሪ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ የጎሳ መሪ የዳኝነት ሥርዓት ዉስጥ ብዙ የግጭት/ችግር አፈታት ሥርዓቶች ይፈፀማሉ፡፡እነዚህ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓቱ ኺታ ኺላቴ (የኧሌ ባህል) በመባል ይታወቃሉ፡፡ በነኚህ የባህል ሥርዓት ስር ከእርሻ ድንበር መሬት መተላለፍ እስከ የሰዉ ህይወት ማጥፋት ሁሉ በመዋቅሩ የተለያየ የእርቅና ድርድር ሥርዓት ያለምንም ጥቃትና ደም መፍሰስ በባህሉ ከትንሹ እስከ ተወሰነለት የሞራልና ደም ካሳ ክፍያ በመፈፀም እርቅ በመፈፀም ያለ ቅም በቀል ለመኖር የፈውስ እጥበት በምፈፅሙ የጎሳ መሪዉ ስርዓት ፈፃሚ በሆነው ኻሃዶ ወይም ስርዓት ፈፃሚ ተብሎ በሚታወቀዉ ሁሉም ስርዓት ተደርጎ በሰላም የመኖር ስርዓት ያደርጋል፡፡ በዚህ ስርዓት አንድ ወንጀል የፈጸመ /ድንበር የገፋ የሰዉን ሚስት የደፈረ የሰዉ አካል ያጎደለ እና ሰዉን የገደለ/ መሰል ወንጀሎችን ሲፈጽሙ ሁሉም ወንጀል በተመሳሳይ ሥርዓት አይፈቱም። ለምሳሌ የሰዉን ደም ያፈሰሰ የሰዉን ሚስት የደፈረ እና ሰዉን የገደለ ያለምንም አውጫጭኝ እጁን ለጎሳ መሪዉ ይሰጥ እና የወንጀሉን ዝርዝር ለሳርኮ ወይም ለጎሳ መርው መልዕክተኛ ነግሮ የችግሩ አፈታት ስርዓት ከወንጀል ፈፃሚው የጎሳ መሪ ሳርኮ ወደ ወንጀል የተፈጸመበት ጎሳ መሪ ሳርኮ በማድረስ ሁለቱ የጎሳ መሪ ሳርኮዎች ወይም መልዕክተኞች በጋራ በመሆን ለጎሳ መሪዎቻቸዉ በማድረስ ስርዓት ወደሚያመራዉ የችግር ወይም ግጭት አፈታት ሂደት ይገባል፡፡ በስርዓቱ መሰረት ሰዉ የገደለ እርቅ ለማድረግ መጀመሪያ በባህላዊ ሽምግልና ኩማቼ (ኩማ) ወይም የደም ካሳ መጀመርያ ይከፍላል፡፡ ይህ ካሳ የሚወሰነዉ

የሟች ግለሰብ ሁኔታን ያገናዘበ ይሆናል፡፡ ልጅ ነዉ? ወጣት ነዉ? ሽማግሌ ነዉ? አሮጊት ናት? ወንድ ነዉ? ሴትናት? በማለት ከተለየ በኋላ የስርዓት አደራረጉ ስለሚለያይ ይህን መሰረት በማድረግ ካሳዉ በገንዘብ የሚከፈል ሲሆን ገንዘቡ ከተከፈለ በኋላ የእርቅ ስርዓት ሲካሄድ ሰዉ የገደለ ከሆነ በተለመደዉ ነጩ በግ (ኤንተካርካተ) እራሱን በግ ገዝቶ ወንጀል የፈጸመዉ ያቀርባል፡፡ ከዚያም ይታረድና ደሙ እና ፈርሱ በአንድ ላይ በማቀላቀል ሟቹ የሞተበት ቦታ (ደሙ የፈሰሰበት) በኦሃዶ እና ሳርኮ አማካኝነት ይረጫል፡፡ ዉሃ በሾርቃ (ሻደ) ይደረግና የሚደረግ ሥርዓት ተደርጎ ዉሃን በመርጨት እርቅ ይፈጸማል፡፡

የሰዉን ሚስት የደፈረም በኧሌ ብሔረሰብ በጣም ከባድ ወንጀልና ሰዉ ከመግደል አይተናነስም። ደም አፍሳሽ የነበረዉን ወንጀል ግን በባህላዊ የጎሳ ዳኝነት የራሱ የሆነ የግጭት አፈታት ሂደት አለዉ፡፡ በዚህ መሰረት የጎሳ መሪዉ የዳኝነት ስርዓት ወንጀለኛዉ የሞራል ካሳ እስከ 40,000 (አርባሺህ) ከከፈለ በኋላ ወንጀል ለተፈጸመበት የጎሳ አባላት የእርቅ ግብዣ ተብሎ አንድ በሬ ለእርድ ያቀርባል፡፡ ከዚያ በኋላ ለስርዓት እጥበት ነጩ በግ (ኤንቴከርካተ) ያመጣና በጊቷ ታርዳ ደሟና ፈርሱ ፈርሷን በማቀላቀል በኦሃዶ አማካኝነት ይረጫል ዉሃ በሾርቃ ተደርጎ የባህል የልመና ጸሎት ተደርጎ ስርዓተ እርቅ ተፈጽሞ ያለምንም ቂም በቀል በሰላም መኖር ይቀጥላል፡፡ ነገርግን እርቅ ከተፈጸመ በኋላ በቀል የሚያስብ ወይም የፈጸመ በባህሉ የተረገመ (አዋራጅ) ተብሎ ስለሚፈረጅ ቂም በቀል ማሰብም ሆነ መፈጸምአይታሰብም፡፡ በአሁኑ ሰዓት ሥርአቱ ያለበትን ሁኔታ ስናይ የባህል ሥርዓቱ ቀድሞ ብር ካለመኖሩ የተነሳ ወንድ የገደለ የደም ካሳን ጠንካራ ብረት ገዝቶ ያቀርብም ነበር ግን አሁን ላይ ብረት ገዝቶ ማቅረብ ቢቀርም ሥርዓቱ የደም ካሳው በገንዘብ እና ሌሎች ባህላዊ አስፈላግጊ የሆኑትን ባመከለ መልኩ በአግባቡ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ የጎሳ መሪውና ባህላዊ ዳኝነቱ እንደ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ተቋም ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡

# ኼልታ

በደ/ብ/ብ/ ሕዝቦች በኮንሶ ብሔረሰብ “ኼልታ” የሚባል ባህላዊ አስተዳደር ስርዓት አለ፡፡ ስርዓቱ በውስጡ ባህላዊ ዳኝነትና እርቅን የሚመራ “ኤራአታኾንሶ” የሚባል ባህላዊ የዳኝነት አስተዳደር ስርዓት አለው፡፡ “ኤራአታኾንሶ” በውስጡ “አራራ” እና “ዴኻ” የሚባሉ የዳኝነት ስርዓትን የያዘ ነው፡፡ በነኚህ በሁለቱ የእርቅም ሆነ የዳኝነት ስርዓት የሚፈጸምበት ሲሆን ስርዓቱ በሁለቱም ከቀላል እስከ ከባድ ግጭት /ግድያ/ ድረስ ያሉትን ጉዳዮች የሚዳኝ /የሚመለከት/ ይሆናል፡፡ እንደ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ተቋም ሆኖ አገልግሎት የሚሰጥ ኢመደበኛ ተቋም ነው፡፡ በእውነትና በህቅ ላይ መሠረት አድርጎ ቶሎ ፍትህ የሚሰጥና ቅጣቱ ሰላማዊ ኑሮን ባገናዘበ መልኩ የሚጣል ቅጣት ስለሆነ ፍርዱ የፀና ተቀባይነት ያለውና በሁለቱ መካከል ቀጣይነት ያለው ሰላማዊ ኑሮ እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡ “አራራ” በሽምግልና /ቅሙማ/ ስነ-ስርዓት እርቅ ተካሂዶ የተጎዳ አካልም ካለ የሚካስበት ሂደት ነው፡፡ “ዴኻ” በአብዛኛው በ”አፓቲምፓ” የሚመራ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ሲሆን ከሳሽና ተከሳሽን በማከራከር በውሳኔ ላይ ከደረሰ በኋላ እንደ የጥፋቱ ክብደትና ቅለት ቅጣት የሚጣልበት ነው፡፡ ደም ፈሶ ወይም ግድያ ተፈጽሞ ከሆነ ጥቁር በግ ወይም ላም በማረድ የማንጻት ስርዓት ይካሄዳል፡፡ ይህ ማህበራዊ ሃብት አገልግሎት እየሰጠ ቢሆንም ከኃይማኖትና ከዘመናዊነት እንዲሁም ከመደበኛ ህግ አንጻር እውቅና ማጣትጋር ተያይዞ የመዳከም አዝማሚያ ይታይበታል፡፡

# ሆቀተ

ሆቀተ በደ/ብ/ብ/ ሕዝቦች ክልል ከምባታ ጠምባሮ ዞን የዶንጋ ብሔረሰብ ባህላዊ ሀብት ነው። የዶንጋ ብሔረሰብ በመካከላቸው የሚከሰቱ አለመግባባቶችና ልዩ ልዩ ግጭቶችን በማጣራት ዳኝነት የሚያከናወኑበት እርቅ የሚፈጥሩበት ባህላዊ የሽምግልና መዋቅር አላቸው፡፡ አነስተኛ አለመግባባቶችና ግጭቶች ቢከሰቱ በየአከባቢው ያሉ የጎሳ መሪዎች የወማው ሹመኞች ወይም “መጋባዎች” ግጭቶችን ያስወግዳሉ፡፡ ከፍተኛ ግጭቶች ለምሳሌ፡- የነፍስ ግድያ ከሆነ ጉዳዩ በወማው በሚመራው ከፍተኛ የሽምግልና መዋቅር ተይዞ የዳኝነትሥርዓትይፈፅማል፡፡ በባህላዊ አስተዳደሩ “ወማው” በየአከባቢው በሚደረጉ እርቆች ላይ ይግባኝ የሚዳኝ ሲሆን የመጣውን ጉዳይ ገምግሞ ይወስናል፤ ያሻሽላል ወይም ያፀናል፡ ፡ በድንገተኛ ፀብ የአንድ ሰው ሕይወት ቢያልፍ በወማው በሚመራው ከፍተኛ የሽምግልና መዋቅር የሚታይ ሲሆን መዋቅሩ “መጋባዎችንና የሀገር ሽማግሌዎችንም” ያጠቃልላል፡፡ እነርሱም ጉዳዩን በእነርሱ ቁጥጥር ሥር ይዘነዋል የናንተን ልጅ ወይም ዘመድ እንደ ገደለ አውቀናል ግደሉት” ይላሉ፤ይሁን እንጂ ሽማግሌዎች በባህሉ ስለሚከበሩና ስለሚፈሩ የሟች ዘመዶች እናንተ ግደሉት ወይም የሚታደርጉትን አድርጉ ይላሉ፡፡ በኃላ ሽማግሌዎች ሁሉቱንም ወገን የማስታረቅ ሥራ ያከናወናሉ ጉዳዩን ወይም ጠቡን ይመረምራሉ፤ጥፋተኛውን ለይተው ያወጣሉ፡፡

በወገን መካከል ተጨማሪ ግጭትና መበቃቀል እንዳይከሰት ሁለቱ ባላንጣዎች እንዲታረቁ ይለምናሉ፡፡ ከብዙ ልመናና ማግባባት በኃላ የሟች ቤተሰቦችን አሳምነው በማስታረቅ በመጨረሻም ባህላዊ ሥርዓት ያከናውናሉ፡፡ ባህላዊ እርቁ የፀና እንዲሆን አንድ ጥቁር አንድ ዳለቻ በጎች ይገዛሉ፡፡ ሥርዓቱ የሚከናወነው ማታ ሲሆን በጨለማ ቤት ውስጥ ጥቁሩ በግ በራፍ ላይ ይታረድና የሟችና ገዳይ ወገኖች ደሙን በመርገጥ ፊታቸውን ወደ ውጭ በማድረግ ወደ ኋላ እየሄዱ ቤት ውስጥ የሚታረዳውን ዳለቻ በግ ደም በመሻገር ባንድ ላይ በተዘጋጀላቸው ሥፍራ ተቀላቅለው ይቀመጣሉ፡፡ ከዚያም የተበጠበጠ ማር በላያቸው ላይ ይርከፈከፋል፤ በመቀጠል አብረው መብላትና መጠጣት ይጀምራሉ፡፡ ከዚህ በኋላ እርቁ የፀና ይሆናል። ሰዎችም እንደ ዘመድ የሚተያዩ እንጂ እንደ ባላንጣ የሚጣሉ አይሆኑም የእርቅ ሥርዓቱም በዚህ ይፈፀማል፡፡

ይህ ባህላዊ እሴት በዶንጋ ብሄረሰብ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነት ያለው እና እስከዛሬ ድረስ ህብረተሰቡ በመኪና አደጋ፣ በድንገተኛ ጠብ የሚከሰቱ የነፍስ ግድያ ወንጀሎችን እያስታረቁ ይገኛሉ። ሆኖም ግን ከእርቅ በኃላ የሚከናወን ባህላዊ ሥርዓቶች ከሃይማኖት ተጽዕኖ የተነሳ ሲተገበሩ አይስተዋልም። በሁለት ወገኖች መካከል በተፈጠረው ግጭት የተከሰተው ሞት ወደ ሰፋ ግጭትና መበቃቀል ብሎም ወደ ጎሳ ግጭትና ወደ ብሄር ግጭት ከዚያ እያደገ ወደ ሀገር የማፍረስ ብጥብጥ እንዳያመራ ከማድረግ አኳያ እንዲሁም በህብረተሰቡ መካከል አንድነትንና እናአ

አብሮነትን ያዳብራል። እርቅና ሰላም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ስለሆኑ እሴቱ ከሰላምጋር ያለው ቁርኝት ከፍተኛ ነው።

# ሴራ

ሤራ በደ/ብ/ብ/ ሕዝቦች፤ ሀላባ ዞን የሀላባ ብሔረሰብ ማህበራዊ ሃብት ነው። በሀላባ "ሤራ" የሚባል የባህላዊ አስተዳደር ሥርዓት አለ፡፡ በዚህ ሥርአት ዉስጥ ሁለት የግጭት አፈታት ክፍሎች አሉት። እነሱም ጉዳ እና ጉማ በመባል ይታወቃሉ፡፡ በነ፝ህ በሁለቱ የዕርቅ፣ የሰላምና የዳኝነት ሥርአቶች የሚፈፀሙ ሲሆን ከቀላል እስከ ነፍስ ግድያ ወንጀልና ግጭት ሲፈፀም ይዳኝበታል፡፡ እንደ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ተቋም ሆኖ ያገለግላል። በአባቶች የሚጣለዉ የቅጣቱ ክብደት ሕዝቡ ሰላሙን ጠብቆ በስምምነት እንዲኖር ያደርገዋል፤

ጉማ፡-በተለይ በግድያ የተፈፀሙትን ግጭቶች የሚፈታ ሲሆን እንደየደረጃቸዉ ተከፋፍሎ የሚፈፀም ነዉ፡፡ እነሱም፡-(1) ሙሉ በሙሉ በጉማ ሥርአት መፍታት (2) በግማሽ ደረጃ በጉማ ሥርአት መፍታትና (3) በሩብ ደረጃ መፍታት ናቸዉ፡፡

ጉዳ፡-በሀላባ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርአት ሲሆን አፈፃጸሙም ጥቁር የመስዋእት ላም፣ ጥቁር በግ፣ ጥቁር ባህላዊ ሻማ፣ጥቁር ባህላዊ ብርድ ልብስ ወዘተ ከቀረበ በኋላ የሚካሄድ ሥርአት ነዉ፡፡የተፈፀመዉ የግድያ ወንጀል ከሆነ እስከ 100 ከብት ድረስ ካሳ የሚሰጥበት ሥርአት ሂደቶች አሉት፡፡ ይህ ማኅበራዊ ሀብት አሁንም በአግባቡ እየተተገበረ ይገኛል፡፡

# ገትሴራ

ገት ሴራ በደ/ብ/ብ/ሕ በሀዲያ ዞን በሀዲያ ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር ስርአት ነው። ገትሴራ በሀዲያ ግጭትን ለመከላከል ጥቅም ላይ ከሚውሉ ዋነኛና በጣም ውጤታማ ከሆኑ ዘዴዎች የሚጠቀሰው መህላ (ህድሮ/Hidiro) ነው፡፡ በአጠቃላ ይህ ድሮ በግጭት ወቅት የነፍስ ማጥፋት ወይም የንብረት ውድመት ቢከሰት በቂም በቀል ስሜት ግጭቶች እየተስፋፉ እንዳይሄድና ተጨማሪ የህይወት መጥፋትና የንብረት ውድመት እንዳይከሰት በተጋጩ ቡድኖች እውነተኛ መከባበርና መተባበር እንዲሰፍን ተመሳሳይ ግጭት እንደገና እንዳይከሰት በማድረግ በጣም ውጤታማ የሆነ የሀዲያ ሴራ አካል ነው፡፡ በሀዲያ ጎሣዎች መካከል ህድሮ (ማሃላውን) በፈጸሙ ጎሳዎች መካከል ጋብቻ የሚከለክል ዝምድናን በመፍጠር የሚጠናቀቅ ነው፡፡ በመሀላ (ህድሮ) ወቅት ተቆጥሮ የተገባውን ቃል የማክበር ግዴታ ሴራው ተቆጥሮ ያስቀምጣል፡፡ የተደበቁና የሰፉ የግጭት ሚስጥሮችን በማውጣት የሚተነትኑ የወቅቱን ግጭት ድብቅ መነሻ የሚያሣዩ ትልቅ የአዕምሮና የአስተሳሰብ ብቃት ያላቸው ግለሰቦች "ሀራጋኖ" ይባላሉ፡፡ እነዚህ ግለሰቦች እስካሁን በሕብረተሰቡ ዘንድ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ሴራው በግጭት የሚከሰት ሞት አይነቶችን በመዳኘትና በማስታረቅ በህብረተሰቡ መካከል የተፈጠረን አለመግባባቶች ቀድሞ ወደነበረበት ሠላማዊ ግንኙነት ይመልሳል፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች (ዳኞች) የሚያስቀምጡት ግዴታ ተፈፃሚነቱ ሠላምን ለማስቀጠል ሁነኛ መፍትሔ በመሆኑ ለዘላቂ ሰላም ግንባታ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

# ቢታንቴ

ቢታንቴ በደ/ብ/ብ/ሕ በጎፋ ዞን በጎፋ ብሄረሰብ ዘንድ ያለ እሴት ነው። በጎፋ ባህል የግጭት አፈታት ወይም የዳኝነት ሥራውን የሚመራሰው "ቢታንቴ" ተብሎ ይጠራል፡፡ "ቢታንቴ" ማለት በእያንዳንዱ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ የመሬት ሥሪት /አስተዳደር/ የሚመራ ሰው ነው፡፡ የሽማግሌዎች ህብረት ደረዱላታ (Dere duulata) ይባላል። በአከባቢዉ ነዋሪ ወይም ህዝብ ዉስጥ ማጭበርበርና በዉል ያልታወቁ ጉዳዮችን ለመመርመርና ለማዉጣት የሚደረግነዉ፡፡ ጋደጭማ (Gade cima)-ትላልቅ የሆኑትን ማለትም መሪን ከመሪ፡ መሪን ከህዝብ ጋር ለማስታረቅና ለማግባባት ሰባት ጭማ (Laapun cima)-ቤተሰባዊና ዘመድ ከዘመድ ጋር ያለን ችግር ለመፍታትና ለማግባባት የሚሰባሰቡበት ነዉ፡፡ ዱቡሻ (Dubusha)-ተራና ቀላል የሆኑ ግጭቶችን ለመፍታት የሚደረግ ስብሰባ ነዉ፡፡ ኩረሲ (Kuurethi)-ከተከራካሪዎች መካከል ለባህላዊ ዳኝነቱ እምቢተኝነቱን ለሚያሳዩ ግለሰቦች ላይ የሚጣል በማህበራዊ ተሳትፎ እና እንቅስቃሴዎች ላይ የሚያገል የተለያዩ ዓይነት ማዕቀቦች ናቸዉ፡፡ ጉፐሲ (Guupeth-i)-በግጭት አፈታት ጊዜ የሚደረግ ብይን ወይም ፍርድ ነዉ፡፡ ባራንቾ (Baarancho)- በማናቸዉም ግጭት ወቅት ይቅርታና ዕርቅ ማዉረድ ስርዓት ነዉ፡፡ ሕዝቡ ሌላ አማራጭ መንገድ ከመፈለግ ይልቅ በአሁኑ ጊዜም እንደዚህ ያለዉ ሥርዓት በየቀበሌው ሁሉ በትኩረት ቀጥሎ እየተተገበረ ይገኛል፡፡

# ጎሜ

ጎሜ በጎፋ ባህል በአካባቢዉ ሕዝቡ በጋራ የሚያምኑበትና አንድ የሚያደርጋቸዉ አስተሳሰቦች፣ ስርአትንጠብቆና ተከባብረዉ እንዲኖሩም ጭምር የሚታመንበት መቅሰፍት ማለት ነው። ከባህል የወጣ፤ ሽማግሌን የማይሰማ፤ ወንጀል የሚሰራ ሰው ጎሜ ይደርሰዋል ተብሎ ይታመናል። በአሁኑ ሰአትም ሰዎች ወንጀልን እንዳይፈጽሙ፤ በሰላም እንዲኖሩና ለቀጣይ ትውልድም እያስተማሩ ባህሉን በጋራ በመጠበቅ ተጠናክሮ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በጎፋ ባህል ሶስት የጎሜ አይነቶች አሉ፤ (1) ካዉሻጎሜ (Kawsha gomme)፡ ስድብና የቃል መተላለፎች (2) ፓላጎሜ (Pala gomme) ዘመድ ከዘመድ መጋባት/መዳራት፣ ዝሙት፣ ራስን ማጥፋት፣ ግፍ መፈጸም ሰዉ ከእንስሳ ጋር ያለዉ አግባባዊ ያልሆኑ ግንኙነቶች ቢሆን (3)- ግታጎሜ (Gita gomme) ዉልማፍረስ/ቃልመለወጥ፣ ማጭበርበር፣ ክህደት የውሸት ክስና ምስክርነትወዘተ ተብለዉ ይታወቃሉ፡፡

የጎሜ እምነት በጎፋ ብቻ ሳይሆን በዙሪያው ያሉ ብሔሮች ለምሳሌ በጋሞ፣ በወላይታና በዳውሮ ህዝቦች ዘንድም የተለመደ ባህል ነው። ይህም ከዘመናዊዉ መንግስት የዳኝነት እና መቀጮ ስርአት ይልቅ ሕብረተሰቡን በማስተሳሰር ትልቅ ሚና ያለዉ እሴት ነዉ፡፡

ኅብረተሰቡን ከማስተሳሰር አንፃር የጎፋ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት ሁኔታን ከዘመናዊው ዳኝነት ሥራ ጋር በንፅፅር ሲታይ ባህላዊ ዳኝነቱ የተሻለና ጠንካራ ጐን ያለው ነው ለማለት ያስችላል፡፡ ምክንያቱም በቦታው ካለው ሰው ሁሉ ጋር ሲሆን በዳይ አቅም ያለውና ከፍያ ለበደል ያደረሰ ከሆነ የቦርዴ መጠጥ ብዛት እስከ /7/ ሰባት እንሥራ ወይም በአከባቢው አጠራር (Xugga) ድረስ እንደ ሽማግሌዉ ብዛት ሊቀጣ ይቻላል፡፡ በዚህ ጊዜ አብሮ መብላት፣ መጠጣት እንዲሁም መጫወት የተለመደ ስለሆነ፤ የሰውልጅ አብሮ በማህበራዊ ሕይወት መኖር የግድ ስለሆነ፤ ለአብሮነትና ለሠላማዊ ኑሮ እጅግ በጣም ታላቅ አስተዋጽኦ አለዉ፡፡

# ጪማታነሊግነሶዎጋ

ይህ ሃብት በደ/ብ/ብ/ሕ በጋሞ ዞን ጋሞ ህዝብ ዘንደ የታወቀ የግጭት መፍቻ ዘዴ ነው። በግለሰቦችም ይሁን በቡድኖች መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶች በዉይይት መፍታትና በሰላም አብሮ ተቻችሎ መኖር ጋሞዎች ካሏቸዉ እሴቶች መካከል አንዱና ዋነኛዉ ነዉ፡፡ ባህላዊ የግጭቶች መፍቻ ዘዴዎች በአንድ ሀገር ዉስጥ የመንግስት መዋቅር ተዳክሞ የሀገሪቱን አሊያም የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ በማይችልበት ወቅት ክፍተቱን በመሙላት በየአካባቢዉ ሰላምና ደህንነት እንዲፈጠር የጎላ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ይገልፃሉ። ከዚህ አንጻር ባህልና ሠላም የአንድ ሳንቲም ሁለት  ገጽታዎች በመሆናቸው ከሰላም ጋር ያላቸው ትስስር የጠነከረ ነው፡፡

በጋሞ ማህብረሰብ ዘንድ የባህላዊ ግጭት መፍቻ ዘዴ ብዙ ጥቅም እየሰጠ ይገኛል። እነሱም ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች መደበኛ ፍርድ ቤት ከሚደረገዉ በዳኝነት ግጭትን መፍታት ዘዴዎች ተመራጭ እንዲሆኑ ከሚያደርጋቸዉ ነገሮች አንዱና ዋነኛዉ የሁለቱንም ወገኖች ፍላጎት ለሟሟላት ወይም ሁለቱንም ወገን አሸናፊ ለማድረግ ጥረት ስለሚያደርግ፤ (2) በአካባቢዉ ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር የበኩላቸዉን ሚና ስላላቸው /ስለሚጨወቱ፤ (3) በፍርድ ቤት ደረጃ የሚሰጥ ዉሳኔ አንዱን ወገን አሸናፊ ሌላዉን ወገን ደግሞ ተሸናፊ ስለሚያደርግ በተጋጩ ወገኖች መካከል የተፈጠረዉን ቅሬታ በዘላቂነት ስለሚፈታ በተጋጩ ወገኖች መካከል የሻከረዉን ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጠናከርና ዘላቂ ሰላም በመካከላቸዉ በመፍጠር ባህላዊ የግጭት አፈታት ስልት ተመራጭ እንደሆነ የጋሞ አባቶች መረጃ ያስረዳሉ። እንዲሁም ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በመፍታት የመደበኛዉን ፍርድ ቤት ሥራ ሚና እና የመንግስት ወጪ በመቀነስ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል። ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በቅርበት ሆነዉ የማህበረሰቡን ልማዶችንና ሞራልን ጠብቀዉ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን የሚፈቱ በመሆናቸዉ በተጋጩ ወገኖችም ሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ አድርጓቸዋል፡፡

# ጪማና አሊሶ ዎጋ

በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል በዘይሴ ብሄረሰብ ቋንቋ ግጭት አሼ (Oeshe) ተብሎ ይጠራል። በብሄረሰቡ ዘንድ ለግጭት የሚሰጠዉ ትርጉም በሁለት ወገኖች አለመስማማት ነዉ፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ ግጭቶችን ለመፍታት የሚነገሩ የተለመደ አባባል ዶስ ሜቶ ይፈንጋቶፌሽ (Dost Metsy Fengate Feeshe) ሲሆን ትርጉሙም የጎረቤበት ችግር ባላሰብኩበት ቦታ ያዉላል የሚል ነዉ፡፡ ይህ የሚያሳየዉ የዘይሴ ማህበረሰብ አባላት የራሳቸዉን ሥራ ትተዉ ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት በአካባቢያቸዉ ያሉትን አለመግባባቶችና ግጭቶችን መፍታት የተለመደ ነዉ፡፡ በዘይሴ ማህበረሰብ ዘንድ ባህል የማንነታቸዉ መገለጫ እንደመሆኑ መጠን ሰላም በግለሰቦችና በቡድኖች ዕለትተዕለት እንቅስቃሴ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ማህበረሰቡ ለሰላም የሚሰጠዉ ቦታ እጅግ የጎላ ነዉ፡፡ በዘይሴ ብሄረሰብ የባህላዊ ዳኝነት ስርአትና ግጭት መፍቻ ዘዴ ጪማና አሊሶ ዎጋ ይባላል።

# ግዲቾ ዎጋርሲ ጎንዶሮ

ግዲቾ ዎጋርሲ በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል  በጋሞ ዞን የግድቾ ብሔረሰብ ግጭት መፍቻ ሥርራአት ነው። ግዲቾ ማህበረሰብ ከሌላ ብሄረሰብ ጋር ግጭት ሲፈጠር ጎንዶሮ በሚባል ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት መሠረት በባህላዊ መሪዎች አማካኝነት ይፈታል፡፡ ስርዓቱም የተጋጩ ወገኖች ዳግም እንዳይፈላለጉ የሚያደርግ ነዉ፡፡ የእርቅ አፈፃጸም ሂደቱም ከብት ከታረደ በኋላ በፈርሱ በመታጠብ የሚፈጸም ነዉ፡፡ በጊዲቾ ቋንቋ ኤንጌ (Enge) ተብሎ ይጠራል፡፡ ትርጉሙም በሁለት ወገኖች መካከል አለመስማማት መከሰት ማለት ሲሆን፤ በዳይ ተጸጽቶ ነገሩን ለሽማግሌዎች ካመለከተ በኋላ፤ሽ ማግሌዎች ጉዳዩን በሚገባ በማጤን በሁለቱ ቤተሰቦችና ጎሳዎች መካከል ብሎም፤ ግጭቱ እየሰፋ ወደ ህዝብ እንዳይገባ ጭምር የሚታመንበት ስለሆነ፤ በፍጥነት በመመርመር በየደረጃዉ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ይፈታሉ፡፡ አሁን ላይ እሴቱ እንደ አዲስ በማንሰራራት ላይይገኛል፡፡ ለዚህ በዋነኝነት የሚነገረዉ ለባህል ዘርፍ ትኩረት በመሰጠቱ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ባህላዊ ግጭት አፈታት በአብዛኛዉ በመደበኛዉ ፍርድ ቤት የሚያሳልፉትን ጊዜ በማስቀረት ከጊዜና ከወጪ አንጻር እንዲሁም ወደ ልማት ሥራዎች እንዲሰማሩ የጊዜ ብክነት ከማስቀረት አንጻር ፋይዳዉ እጅግ የጎላ ነዉ፡፡ የእርስበርስ ግንኙነትን ከማጠናከር ባለፈ መተሳሰብንና ይቅርባይነትን ስለሚያስተምር ከሰላም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡

# ዴሃእናቅማዩማ (ቅሙማ)

ይህ እሴት በደ/ብ/ብ/ሕ ደራሼ ልዩ ወረዳ በደራሼ፣ ሞስዬ፣ ማሾሌና ኩሱሜ (የአራቱም ብሔረሰቦች ተመሳሳይ ነዉ) ባህላዊ ሀብት ነው። ሞራ የሚባል በአራቱም ብሔረሰቦች (ዴራሼ፣ ሞስዬ፣ ኩሱሜ እና ማሾሌ) ዘንድ ለወንዶችና ለሽማግሌዎች መዝናኛና ለቅማዩማ (ቅሙማ)/ ለሽምግልና እንዲሁም ለባህላዊ የዳኝነት ሥርአት የሚጠቀሙበት ባህላዊ ተቋም ነዉ፡፡ በዚህ በሞራላ ይቅሙማ/ሽምግልና ሥርአት ይካሄድበታል፡፡ ግጭት ሲከሰትም ሆነ አዲስ ዝምድናን ለመፍጠር ቅሙማ እጅግ በጣም ሰፊ ሚና አለዉ፡፡ ቅሙማ በአራቱም ብሔረሰቦች ተመሳሳይነት ያለዉ የግጭት አፈታት እና የሰላም ግንባታ ተቋም ሲሆን በማህበረሰቡ መካከል ግጭት ሲፈጠር ግጭቱ ተባብሶ እንዳይሰፋ በዳዩ ገና በማለዳ ቅማያ/ሽማግሌ ወደ ተበዳዩ ቤት ይልክና በዴሃ ድርድር ተስማምተዉ አብረዉ ቤት ያፈራዉን መብልና መጠጥ በመቃመስ ይለያያሉ፡፡ አሠራሩ እና የጊዜዉ ጉዳይ ልክ እንደተፈጠረዉ ግጭት መጠን የሚለያይ ቢሆንም ሂደቱና ሥርአቱ ግን ቅማዩማ (ቅሙማ) በመባል ይታወቃል። ቅማዩማ አዲስ ዝምድናን ለመፍጠር፣ የቀድሞዉን ሰላም እና አንድነትን ወደነበረበት ለመመለስ፣ ከሌላ ብሔር ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት እና ሌሎች ያለመግባባቶችን በዘላቂነት የሚፈታ መሆኑ ለሰላምና አብሮነት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። በተለይ በሥርዓቱ ተሣታፊዎች የንጉስ ዘርያ ያላቸዉ፣ የአባቶች መንፈስ ያደረባቸዉ ታዋቂ ሽማግሌዎች፣ የጎሣ መሪዎችና በሕብረተሰቡ ዘንድ እጅግ የተከበሩ ሰዎች መሆናቸዉ ግጭት ለመፍታትና እርቅ ለማውረድ ያላቸው ሚና  ከፍተኛ ነው። በመጨረሻዉ የዕርቅ ቀን የጋራ ግብዣና የእርድ/የደም ማፍሰስ ሥርአቶች መኖራቸዉ የስርዓቱን ተቀባይነት የጎላ ያደርገዋል።

ይህ ባህላዊ ሀብት ለዘላቂ ሠላም ግንባታ ጉልህ ሚና አለዉ፡፡ ቅማዩማ እስከዛሬ ድረስ በሕዝቡ ዘንድ ወደር የሌሌዉ የግጭት አፈታት ስርአት ሲሆን፤ ለዚህ ሥርአት የማይገዛ ማንኛውም ሰዉ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ለቁም ነገር የማይበቃ እምነት እንደማይጣልበትና እንደማይረባ ሰዉ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ሀብቱ በማኅበረሰቡ ዘንድ ሰላምንና መረጋጋትን የሚፈጥር ሲሆን ይህንንም የሚያከናውነው በባህላዊ ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም የህብረተሰቡን ማህበራዊ ግንኙነት የሚያጠናክር ከመሆኑም በላይ ለባህላዊ ዕድገቱም ጉልህ ሚናን ይጫወታል፡፡ በቅሙማ የተፈታ ግጭት ወይንም አለመግባባት አብሮ በመብላትና በመጠጣት የሚጠናቀቅበት ዋና አላማ የቀድሞዉን አብሮነትና ወዳጅነት 100% የሚመልስ ስለሆነ ነዉ፡፡ እንደ ሥርአቱ አብረዉ የሚቃመሱት እህል እንኳ ቢጠፋ፤ ጨዉ ተወስዶ ሁሉም በአንድነት ቀምሰዉ ይለያያሉ፡፡ ከዚያን ሰዓት ጀምሮ ጥለኞች የነበሩት የቀድሞ ወዳጅነታቸዉ ይቀጥላል፡፡

# ጭሙንታንታ ሴራ

ጭሙንታንታ ሴራ በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል በቡርጂ ልዩ ወረዳ የቡርጂ ብሔረሰብ የግጭት መፍቻ ባህላዊ ሀብት ነው። ልክ እንደሌሎች አካባቢዎች የቡርጂ ሕዝብ የሽምግልና ሥርአት ያለው ሲሆን፤ በተለያዩ ምክንያቶች የተጣሉትን፣ የተጋደሉትን፣ ብሎም ከአጎራባች ነዋሪዎች ጋር ግጭት ሲፈጠር በዚሁ ስርአት ይታረቃሉ፤ ያስታርቃሉም፡፡ በመሆኑም የአካባቢዉን ሰላም ለማስፈን፣ ለአብሮነትና ለመተሳሰብ ይገለገሉበታል፡፡ ስለዚህ በማናቸዉም ምክንያት ግጭትና አለመግባባቶች ሲፈጠሩ የሚፈቱበት ዋነኛዉ መንገድ ጭሙንታንታ ሴራ ነዉ፡፡

ጭሙንታ በቡርጂ ከሁሉም የዳኝነት ሥርአቶች ይልቅ ቅድሚያ የሚሰጠዉና በሕዝቡ ዘንድ ሰላምና መረጋጋትን ፈጥሮ እስከዛሬ ድረስ የሕዝብ አንድነትን ያስጠበቀ ብቸኛ መንገድ እንደሆነ የብሔረሰቡ አካላት ይገልፃሉ፡፡ ስለ ጭሙንታንታ ተሣታፊዎች እና ሕዝቡን ስለሚገዛዉ የጋራ እምነት፤ በተለይም ከአባቶች ስለሚተላለፈዉ መልዕክትና በህዝቡ ዘንድ እጅግ በጣም ተቀባይነት ማግኘት የቻለ ተቋም ነው። በርግጥ ዘመናዊነት እየተስፋፋ ሲመጣ ክሶችን ወዲያዉኑ ወደ ፍርድ ቤት ይዘዉ የሚሮጡ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ከመምጣቱ በስተቀር አሠራሩም ሆነ ሥርአቱ እስካሁን ድረስ በአግባቡ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ጭሙንታንታ ማስታረቅ ወይንም ግጭትን መፍታት ብቻ ሳይሆን መንደርን ከመንደር እንዲረዳዳ የሚደረግበት፤ በተለይም የመንገድ እና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎችን በጋራ ለመከላከል የሚጠያየቁበት እና የልማት ሥራዎች ጥያቄ ሲኖር ከመንግስት ጠይቆ ለማስፈቀድ እንደ ሕዝብ ኃይልም ይቆጠራል፡፡ የሚፈጠሩትን ግጭቶችን ከማብረድ ጀምሮ በማያዳግም መልኩ በማስማማት ወደ አንድነት የሚያመጡ በመሆናቸዉ ዘላቂ ሰላምን በመፍጠር የሕዝቡን አንድነት ጠብቆ የቆየ ነው።

# ቦኮ

ቦኮ በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል በአማሮ ልዩ ወረዳ የኮሬ ብሔረሰብ እሴት ነው። ይህ ባህላዊ ስርዓት የራሱ መሪዎች ያሉት የአንድ ባህላዊ አስተዳደር ወሰን ክልሉ ቀደምት ሰፋሪ ጎሳ ወኪሎች ተቋም ነዉ፡፡ እነኚህ የጎሳ መሪዎች የሚያቋቋሙት ከእያንዳንዱ ነባር ጎሳ መሪዎች ተዉጣጥተዉ የሚመሰርቱት በመሆኑ የሁሉንም ጎሳ አባላት ማሕበረሰብ በአንድነት በመያዝ አምባ (amba) የሚመሰረት ነው፡፡ ቦኩ ከሁሉም የጎሣ መሪ ሽማግሌዎች የተዉጣጣ ሕብረት በመሆኑ፤ በአማሮም ሆነ ኮሬ ሰፍሮ በሚገኝባቸው አዋሳኝ አካባቢዎች የኮሬ ብሔረሰብ አባላት ታላቅ ፍርሀትና አክብሮት ይሰጠዋል፡፡ ሕዝቡ ሁሉ ለአባቶች የሚሰጡት ክብር እጅግ ከፍ ያለ ስለሆነ የቦኮ ዳኝነትም ሆነ የእርቅ ሥነ-ስርአት በአካባቢዉ ከፍተኛ ተጽእኖ አለዉ፡፡ የግጭት አፈታት ሂደቱ ከቀላል እጅግ ዉስብስብ እስከሆነዉ ደረጃ ድረስ መፍትሔን ሊያመጣ የሚችል ከመሆኑም ባሻገር በሕብረተሰቡ ዘንድ ለጎሳ መሪ አባቶች የሚሰጠዉ ከበሬታ ለነገሮች መቃለል ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ በቤተሰብ ችሎት (ዛዋኦሄ) የንዑስ ጎሳ ችሎት (ካራኦሄ)፣ የአባባይየአደባባይ/የማህበረሰብ ችሎት (ለዶኦሄ) እና ቤተ-መንግሥት ችሎት (ካሦኦሄ) በአራት አገር በቀል ችሎት ደረጃዎች ላይ በየችሎቱ ዕዝ ላይ ለማስቻል የባህል ሕጉ ሥልጣን ለሚሰጣቸው ወኪል የጎሳ መሪዎች ከተቀመጡ ኃላፊነቶች አኳያ በ24ቱም የግዛተ-ንጉሡ ግዛቶች በ-ሶስት ክልሎችና 24 ቦኮዎች ዳኝነት፣ እርቅና ሰላም ሲወርድ ክፉን መርገም እና መልካሙን የመመረቅ ሥልጣን የቦኳደ ሥራ ነው!
ቦኮ እስካሁን ድረስ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትና ተአማኒነት ያለዉ የግጭት አፈታት ሥርአት ነዉ፡፡ እንዲያውም ብዙ ባህላዊ ሥርዓቶች

በተለያዩ ሐይማኖታዊና ፓለቲካዊ አካሄዶች ሳቢያ ሲዳከሙና የቀድሞ ኃላፊነታቸውን ለመስጠት አቅም ሲያጡ አማችነትና ቦኳደነት ከዚያ ቤተሰብ በሥጋ አንጋፋ ሆኖም ድሪቱን በማየቱ እጅግ በጣም የሚፈራና የሚከበር ባህላዊ እሴት ነው። ሕዝብን ከሕዝብ፣ ግለሰቦችንም እርስበርሳቸዉ እንዲቀባበሉ ስለሚያደርጋቸዉ ከቅድመ-አያቶች ወደ አባቶች የተላለፈዉ ይህ ዘመናዊ ያልሆነዉ ባህላዊ ሥርአት ዉጤታማነቱን ተከትሎ ሌሎች ጠቃሚ ባህሎች በሕዝቡ መቀባበልና አንድነት እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ ይህም ቀጣዩ ትዉልድ ከአባቶች እንዲማሩ ይረዳቸዋል፡፡ አሁን በአካባቢው ያሉግጭቶችንና አለመግባባቶችን ያለቂምና በቀል መፍትሔ የመስጠት ብቃቱ ተወዳዳሪነት ባለማግኘቱ ተመልሰው እያንሰራሩ የሚገኙ ተቋማት ናቸው።

በአካባቢዉ ቀጣይነት ያላቸዉ ስምምነቶች እና የሚመለከቱ ህጎችን፤ ሰብአዊ መብቶችን ጨምሮ የሁሉም ሰው መብቶች ተጠብቀዉ ሕዝቡ በሠላም እንዲኖር ዋስትና ይሰጣል፡፡ 109ኙም የኮሬ ጎሳዎች በአራት ነገዶች (ኮረሴ፣ካናኤ፣ማና እና ዎጋጨ ነገዶች) የሚታቀፈበትን ሁሉን አካታች ተቋም በመሆኑ ለሠላም ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። ሁሉ አቃፊ ብቻ ሳይሆን አንዱ ነገድ በጉባኤው ካልተሳተፈ የኮሬ ፍርድ የማይፀና ወይም ዋጋ የማይኖረው ስለሚሆን የአንደኛው ወገን ባለመኖሩ ምልዓቱ እንዳልተሟላ ስለሚወሰድ እንከን የሌለውን ፍርድ በመስጠት ለሁሉም ሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን ለተፈጥሮ፣ ለእንስሳት፣ ደን፣ለሚታየውና ለማይታየው ሁሉ በፈጣሪ ፊት ቅን ፍርድ ይሰጣል፤ለፍትህና ለእውነት ይቆማል።

# ሻቲኒሳዛባ

ይህ ማህበራዊ ሃብት በደ/ም/ኢ/ህ//ክ/መ የኮንታ ብሔረሰብ ነው። የኮንታ ህዝቦች ባሳለፏቸው ረዥም ዘመናት ውስጥ ካዳበሩት ፖለቲካዊ፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስርዓቶች ጋር ትልቅ ቁርኝት ያለውን ባህላዊ ዳኝነት (Shatintha zabba) ይባላል፡፡ በኮንታ ብሔር በየመንደሩ የሚነሱ ጥቃቅን ችግሮች ከቡና ጎረቤታማማቾች ጀምሮ እስከ አካባቢ ባሉ ሽማግሌዎች የሚፈቱ ሲሆን ከባድ ወንጀሎች ማለትም፡-ነፍስ ግድያ፣ ስርቆት፣ ዝሙት፣ ለማህበረሰቡ ወግና ባህል አለመገዛት፣ የቤት ቃጠሎ፣ የድንበር ግጭት፣ በጎሳ የማይመጣጠን ጋብቻ፣ በስካር የሚነሳ ከፍተኛ ፀብና ግጭት ወዘተ ናቸው፡፡ እነዚህ ከላይ የተገለፁት ችግሮች በባህላዊ ዳኝነት የሚፈቱ ሲሆን በባህላዊ ዳኝነት የማይፈቱ ተመጣጣኝ ባልሆኑ ጎሳዎች መካከል የሚፈፀም የጋብቻ ስነ-ሥርዓት በብሔሩ የማይነፃና የማይፈታ ችግር ነው፡፡

የባህላዊ ዳኝነት የተለያዩ ስርዓቶችንና መሃላ በመፈጸም የሚከናወን ነው። በሰብሳቢው ዳኛ አማካኝነት ለመሃላ ማስፈፀሚያ የሚሆን ጭድ፣ እሳት፣ ድንጋይ፣ ከሰል፤ ጦር (Baaliya Toraa) ወናፍ ይቀርቡና ከመሃል ዳኛው በግራ በኩል የሚቀመጡ የዶጎላ ቆሞዎች (ጎሳ) መሃላ እንዲያስፈፅሙ ትዕዛዝ ይሰጣቸዋል፡፡ ትዕዛዝ የተቀበሉ የዶጎላ ቆሞዎች እንዲህ እያሉ መኃላ ያስፈፅማሉ፡፡ ይኸውም ጭድ ዘር እንደማይተካ እኔንም ተተኪ ዘር ያሳጣኝ፣ እንደ ድንጋይ ዱዳ ያድርገኝ፣ እንደ ብረት ያቀዝቅዘኝ፣ እንደ ከሰል አመድ ያድርገኝ፤ እሳት ነዶ እንደሚጠፋ የእኔ ዘር ይጥፋ፤ በማለት ከዶጋላዎች ቀጥሎ ተቀብሎ እየማለ የተቀጣጠለውን እሳት በሽንቱ እንዲያጠፋ ይደረግና ሁሉም ሽማግሌዎች ተነስተው በመቆም ተበዳይን በዚህ ዳኝነት ችግር ካልተፈታ በሚቀጥለው የዳኝነት እርከን እግዚአብሔር የአንተን እውነት ያውጣ በማለት መርቀው ያሰናብታሉ፡፡ ሆኖምግን አሁን ዓለም የደረሰበት የእድገት ደረጃና እያሳየ ያለው ተለዋዋጭ ባህሪ የተነሣ የባህላዊ ዳኝነቱ ሥርዓት በጠበቀ መልኩ በማህበረሰቡ ዘንድ አጠናክሮ ለማስቀጠል ያለዉ ተጽዕኖ እጅግ በጣም ፈታኝ ነው፡፡

በኮንታ ብሔር የባህላዊ ዳኝነት የሚደራጀው በካቲ መዋቅራዊ አደረጃጀት ስር ሆኖ ከሦስት ጎሳዎች ማለትም ከማላ፣ ከዶጋላና ከአማራ ጎሣዎች (ቆሞዎች) የተውጣጡ ከሦስት እስከ ዘጠኝ የሚደርሱ ሽማግሌዎች ይሰየማሉ፡፡ የባህላዊ ዳኞች ቁጥር በጎዶሎ ቁጥር የሚሰየም ሆኖ የመህል ዳኛ የቀኝና የግራ ዳኞች ተብለው በሦስት ይከፈላሉ፡፡ የመህል ዳኛው ከማላ ጎሣ የዘር ግንድ ሲመረጥ ከቀኝ የሚቀመጡት ከአማራ ጎሳ የዘር ግንድ ነው፤ እንደዚሁም በግራ በኩል የሚቀመጡት ከዶላ ጎሣዎች የዘር ግንድ ሲሆን እያንዳንዱ ጎሣ አቀማመጥና ተግባር የራሱ ፍቺ አለው፡፡ ይኸውም የማላ ጎሣ የሚመርቅና የሚምር፣ አማራ ቆሞ የጉዳዩ ተሳታፊ ከመሆን ውጪ በመሃላ ወቅት አይረግምም አይመርቅም ነገርግን በውሳኔ ሃሳብ ተሳታፊ ሲሆን ዶጋላ ቆሞ እርግማን የሚያደርስ ነው፡፡ አቀማመጣቸውም በመህል የሚቀመጠው ማላ ጎሳ የነጋሲ የዘር ግንድ ሲሆን በስተቀኝ የሚቀመጠው ከአማራ የጎሣ ግንድ የሚቀመጥ አካል ሲሆን በግራ በኩል የሚቀመጡ ደግሞ የሚያደርሰውና የሚፈራው የዶጋላ ጎሣ ግንድ ነው፡፡ የዳኞች ቁጥር በጎዶሎ ቁጥር የተሰየመው ዋናው ምክንያት ሁለት ሲሆን፡- (1) ወንጀለኛው በመጀመርያው የማጣራት ሂደት ለሽማግሌዎቹ ወንጀሉን ስለ መፈጸሙ ሲጠየቅ እውነቱን ክዶ ያላመነ እንደሆነ በመህል ዳኛው አማካኝነት ቃለ መኃላ እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡ ይኸውም እነኝህን ሦስት የሽማግሌ ቆሞዎችን ግንባራችሁ ይጣላኝ ብለህ አቋርጠህ እለፍ የሚል ትዕዛዝ በመሃል ዳኛው የሚሰጥ ነው፡፡ (2) ወንጀለኛው የፈፀመውን ወንጀል አምኖ የተቀበለ እንደሆነ በመሀል ዳኛው ከግራ ከቀኝ ከተቀመጡ ሽማግሌዎች የሚነሱ ሃሳቦችን ሰብስበውና አደራጅተው ሚዛናዊ ውሳኔ የሚሰጥ አካል ነው፡፡

በአካባቢው ሁለቱ ግለሰቦች በተሰጠው ዳኝነት መስማማታቸው ሲረጋገጥ በዳይ ለተበዳይ በእግሩ ስር ወድቆ ይቅርታ ሲጠይቅ ተበዳዩም ይቅርታ ጠያቂውን ከመሬት በማንሳት ምህረትና ይቅርታ እንዲያደርግለት በማድረግ ተቃቅፈው እንዲሳሳሙ ከተደረገ በኋላ የማላ ጎሣ ወይም በሰብሳቢ ዳኛው አማካኝነት ባህላዊ የእርቅ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡ ይኸውም በገቡቴ መሃል ውሃ ተሞልቶ ሠርዶ፣ ማር፣ ወተትና እርጥብ የእንሰት ኮባ (አውዋ/Awuwa) አንድ ላይ በማድረግ ሁለቱም ግለሰቦች የሁለት እጆቻቸውን መዳፍ በገቡቴ ውስጥ በመንከር ከሰብሳቢው ዳኛ የሚከተለውን ምርቃት ይቀበላሉ፡፡ ይኸውም ከዛሬ ጀምሮ እግዚአብሔር እንዲህ አይነት ወንጀል ያርቅልን! በእናንተ መካከል የተፈጠረው መቃቃር ይህ ንፁህ ውሃ እድፍ እንደሚያነፃ በእናንተ ልቦና ያደረው መቃቃር እግዚአብሔር ያንፃው! ፍቅራችሁ የሰርዶስር መሬትን ዘልቆ እደሚይዝ ፍቅራችሁ ይዝለቅ! ከአንደበታችሁ የሚወጡ ቃላት እንደ ማር እንደ ወተት የጣፈጠ ይሁን! የሚያጋጩ የሚያጣሉ ጠላቶቻችሁ እንደ እንሰት ኮባ ይቀዝቅዙ! በዚህ ሽማግሌና ያስታረቃችሁ ሽማግሌዎች የእድሜ ባለፀጋ ያርጋችሁ በአካባቢያችን ሠላም ይስፈን ብሎ የመህል ዳኛው ሲመርቅ ሌሎች አሜን እያሉ ይቀበላሉ፡፡ እነዚህ የእርቅ ሥነ ሥርዓት በብሔረሰቡ ዘንድ ለሠላም የነበረው ፋይዳ በአሁኑ ሠዓት እጅግ

በጣም የጎላ ነው፡፡

# ዎራፎ

ዎራፎ በደ/ም/ኢ/ህ//ክ/መ በሸካ የሸካቾ ብሔረሰብ የባህላዊ ግጭት አፈታት ሥርአት ነዉ፡፡ ዎራፎ ማለት እሱ ወይንም እሷ መጥፎ ድርጊትን በመፈጸም ችግር እንዲገጥመኝ አልፈልግም ብለዉ የሚያምኑበት ወይንም መጥፎ ተግባር የማይፈጽም ሰዉ ምስጉን ነዉ ብለዉ የሚያምኑበት ሥርአት ነዉ፡፡ በሂደቱ ወቅት ለዎራፎ በተሰበሰበዉ ማህበር መካከል ከተጋጩት መካከል ይነሳና እኔ ችግር እፈጥራለሁ?፣ እኔ ረብሻለሁ?፣ እኔ እበጠብጣለሁ?ወዘተ እያለ በጥያቄ መልክ ይጮሃል፡፡ በዚህ ጊዜ ምንም ችግር የሌለበት እንደሆነ ሕዝቡ ሁሉ በአንድ ድምጽ ወራፎ ወራፎ ይላሉ፡፡ ይህም ማለት በማንኛዉም ሁኔታ ችግር የለበትም መጥፎ ተግባር የለበትም ምስጉን ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ሕዝቡ ዝም ካሉ ወራፎ ተከልክሏል ማለት ነዉ፡፡ ችግር አለበት፤ መጥፎ ተግባር ፈጽሟል ማለት ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ ወንጀለኛን በቀላሉ እየለዩ መቀጮ የሚያስቀምጡ ስለሆነ ማህበረሰቡ ፍርድ ቤት ከመሄድ ወራፎን እንደ አንድ ትልቅ ባህላዊ እሴት ይጠቀሙበታል፡፡

የወራፎ ስርአት የሚከበረዉ በባህላዊ መንደሮች አካባቢ ነዉ፡፡ ይህንን ተግባር በኃላፊነት የሚያስፈጽሙ የጎሣ መሪዎች ናቸዉ፡፡ በዋናነት የአከባበሩ ሥርአት የሚፈፀመዉም በትላልቅ ዛፎች ሥር ሲሆን አንዳንድ ጊዜ በሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሾች ዉስጥ ያካሂዳሉ፡፡ አብዛኛዉን ጊዜ የወራፎ ሥርዓት የሚፈፀመዉ ግጭት በተፈጠረበት አካባቢ ነዉ፡፡ በሥርአቱ ሂደት ወቅት ለአቅመ-አዳምና ሔዋን የደረሱ ወጣቶች በሙሉ መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ወራፎ ሲካሄድ የሁሉም የአካባቢዉ ነዋሪ ምስክርነት ላይ የተመሠረተ ዉሳኔ በመሆኑ፤ ሁሉም ሰዉ ጥልና ማንኛዉም ግጭት ዉስጥ ላለመግባትና በሰላም ነዋሪነቱን ለማረጋገጥ የሚያደርገዉ ጥረት ሰላምን ለመገንባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለዉ መሆኑ፤ ለዘመናት የህዝቡን ደህንነት ያስጠበቀ ባህል እንደመሆኑ ከሰላም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ በአሁን ወቅትም በአግባቡ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

# ኦቶ

ኦቶ በደ/ም/ኢ/ህ//ክ/መ በከፋ ባህላዊ የዳኝነት ሥርአት ሲሆን፤ አብዛኛዉን ጊዜ በባህላዊ የሀይማኖት መሪ ከሌሎች አማካሪዎቹ ጋር በመሆን የተጋጩ አካላትን በየተራቸዉ በግራና በቀኙ በማቆም ጉዳዩን አጣርተዉ ጥፋተኛዉ ሲገኝ ካሳ እንዲከፍሉ ወይንም አስፈላጊዉን ቅጣት እንዲቀበል ካደረጉት በኋላ ሁለቱን ግለሰቦች አስታርቀዉ ይሸኛሉ፡፡ እነሱም ለባህላዊ የኃይማኖት መሪዎች ካላቸዉ ከበሬታ አንፃር ተንበርክከዉ ይቅር ይባባሉና ሰላም ፈጥረዉ ይመለሳሉ፡፡ ከሃይማኖት መሪዉ ጀርባ ያለዉ የአባቶች መንፈስ እርግማን ፍራቻ ለእርቅና ለሰላም ያለዉ ሚና ከፍተኛ ነው። በአሁን ወቅት እጅጉን ይተገበራል፡፡ በመሆኑም በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ህዝቡም እንደ ፍርድ ቤት ተቋም ይገለገሉበታል የአባቶች እርግማን ስጋት ወንጀለኛዉ እንዲናዘዝ ስለሚያደርገዉ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ሰላም እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

# ቄሸ

ቄሸ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በደቡብ ኦሞ ዞን የአሪ ብሔረሰብ እሴት ነው። ቄሸ እርቀ ሰላም ማለት ሲሆን፤ ቀሽሞ ደግሞ እርቅ ማለት ነዉ፡፡ ባማከር (ሜል) የሚባል የአሪ ብሔረሰብ የባህላዊ አስተዳደሩ የንግስና ቦታ በዘጠኙም የአሪ ባላባቶች በሚኖሩበት የአስተዳደር ክልል ዉስጥ የታላላቅ ደንብ (ሥርአት) ማስፈፀሚያና የመናገሻ ቦታዎች አሉ፡፡ ከመናገሻ ወረድ ብሎ ባለዉ የባህላዊ አስተዳደር እርከን ጎዲሜ በመባል የሚታወቀዉ ደግሞ አካሜል የተለያዩ ባህላዊ ሥርአቶች ማስፈፀሚያ ሲሆን በሁለቱም ቦታዎች ከተራ ግጭት እስከ ሕይወት መጥፋት ድረስ ያሉት ጉዳዮች ቄሸ (ቀሽሞ) እና የዳኝነት ሥርአትም በነዚሁ ቦታዎች ይካሄዳል፡፡ በአሪ ብሔረሰብ እንደ ዛሬዉ የፖሊስ ተቋማት በአካባቢዉ ሳይኖር አንድ ሰዉ በስህተት ወይንም ሆን ብሎ ሰዉ ከገደለ በተለይ የራሱን ህይወት ለማዳን ወደ ባላባቱ (ባቢ) ቤት /ግቢ በሩጫ ሄዶ ከገባ የሟች ወገን ለበቀል እዚያ አካባቢ ድርሽ አይልም፡፡ ለአቤቱታ እንጂ ከዚያ በኋላ ባለዉ ጊዜ የቀሽ ሥርአት ይጀመራል። በዚህም ጉዳይ ባለባቱ (ባቢ) እና ጎድሚ ሌሎች ታላላቅ የአገር ሽማግሌዎች ቀደምት ታሪክ እየጠቀሱ ሃይሃይ በማለት ነጋን ካከተይ ንስዎን ችቡደርኪክኬዝጋ ይምሼ፡- ይቅር በሉ ወደ ፊት ልጆቻችን በደም (በቂም) እንዳይፈላለጉ፡፡ እንዲህ እያሉ እርቁ ይፈጸማል፡፡ ግጭቱ ከተለያዩ ባዕድ ጎሳ ጋር ከሆነ ደግሞ ፀቡ ከገዳይ ወገን ልጃገረድ ለሟች ወገን በጋብቻ ይሰጥ ነበር፡፡ ፀቡ በአንድ የዘር ግንድ መካከል የተፈጸመ ከሆነ ዳቢ ካሣ ለሟች ወገን እንዲከፍልና ሽማግሌዎችም በፈረዱት (በወሰኑት) ልክ ሙከት ፍየል/በግ ይቀጣና ጉዳዩ ይቋጫል፡፡

የነፍስ ግድያ ጉዳዮች በፍርድ ቤት የሚያስፈጽሙ ሲሆን ሌሎች ግጭቶች በአሁኑ ወቅትም ከላይ በተገለጹት የአስተዳደር ደረጃ ከላይ ያለዉ ጉዳይ በባላባቱ ሲፈጸም መካከለኛ ጉዳዮች በጎዲሚዎች (የቤተሰብ መሪዎች) በአግባቡ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ሰአት ይህ ስርዓት ከቀበሌ መደበኛው ፍርድ ቤት እኩል አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ሥርአት ነዉ፡፡ በዚህኛዉ ዉሳኔ ቂም በቀል የለም፡፡ የመደበኛው ፍ/ቤት ግን ቂም በቀል አይጠፋም፡፡ በማኅበረሰብ መካከል የሚነሱ ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉ ግጭቶች በመፍታትና በማግባባት ያላቸዉ ሚና ከፍተኛ ነዉ፡፡ በቀጠሮ መመላለስና የሥራ ጊዜን ማባከንም የለበትም፡፡ ይልቁንም አንዳንዴ ተበዳይ አንድ ሰዉ /ሽማግሌ ልብ በአንድ ወይንም በሁለት ሰዎች ጉዳዩ በማግስቱ ዕልባት የሚያገኝበት ሁኔታም አለ፡፡

# ማገኖ

የጌዴኦ ብሔረሰብ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ “ማገኖ” ብሎ በሚጠራው አንድ አምላክ እንደሚያምን፤ ይኸው የሰማይ አምላክ ርህሩህ ከሁሉ የበላይ በተለይም የሁሉ ነገር ፈጣሪ በመሆኑ ሕዝቡ ተገቢ የሆነ ክብርና መስዋዕትን ያቀርባል። በጌዴኦ ባህላዊ እምነት “ወዮ” የሚባሉና ስርዓተ-መስዋዕቱን የሚፈፅሙ ከሰባቱም የጌዴኦ ጎሣዎች የተወጣጡ የሀይማኖት መሪዎች አሉ። እያንዳንዳቸው የተለያዩ መንፈሣዊ ተግባራትን የመፈፀም፣ በእምነቱ መሠረት የመመረቅ እና የመርገም የሥራ ድርሻ ሲኖራቸው ከማገኖ ዘንድ ለዝናብ፣ ለሙብረቅ፣ ለውሃ ሙላት ወዘተ የተሰጣቸው የተለያየ “ቃሮ” ወይንም መንፈሣዊ ኃይል እንዳላቸው ይታመናል። ይህ ማጋኖ እምነት ወንጀል በመከላከል፤ ማህበራዊ መስተጋብር እንዳይናጋና፤ ግጭት እንዳይነሳ በማድረግ የህዝብ ሰላም የሚያረጋግጥ ተቋም ነው።

# ኳር ሙን (Kuaar Muon)

ኳርሙን በጋምቤላ ክልል የኑዌር ብሔረሰብ ግጭት መፍቻ ሥርአት ነው። ይህ ሥርዓት የነፍስ ግድያ፤ ስርቆት፤ የወስብ ቅሌት ጋር የተያያዙ ማንኛውንም ግጭት የሚፈታበት የራሱ የሆነ ሂደትና ቅደም ተከተል ያለው ማህበራዊ ሃብት ነው። የኑዌር ብሔረሰብ በጣም ጥልቅ የሆነ የማህብረሰብ አደረጃጀት ያለውና ግጭት የሚከላከልበት፤ የሚፈታበትና እርቀሰላም የሚያወርድበት ሀይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓት አለው። ኳር ሙን ማለት ልዩ፤ መንፈሳዊ ሃይልና ተሰጦ ያለው እጅግ የተከበረ የጎሳ መሪ ነው። ለምሳሌ ነፍስ ያጠፋ ሰው መጀመርያ ወደዚህ አባት ቤት ሮጦ በመሄድ ከበቀል ከለላ የሚያገኝበትና በኋላም ግጭቱ ተፈቶ እርቅ እስኪወርድ ድረስ ሽምግልናዉን በመምራት፤ በማንጻት፤ ካሳውን በማስከፈል ሰላምን እስከማረጋገጥ ድረስ ሂደቱን የመምራት ሃላፊነት የ ኳር ሙን ስራ ነው። ይህ እሴት አሁንም በአብዛኛው የኑዌር ወረዳዎችና ቀበሌዎች በስፋት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

# ክፍል ሦስት

# ድንበር ተሻጋሪ ማኅበረ-ባህላዊ ሀብቶች

# መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ባህለ-ብዙኅ የኾኑ ማኅበረሰቦች ያሏት ትሁን እንጂ በባህሎች መካከል ለዘመናት የዘለቀ ጥብቅ ግንኙነት የዳበረባት ሀገር ናት፡፡ እነዚህ ሕዝቦች በተለያዩ የፖለቲካ ሥርዓቶች አማካኝነት በሚፈጠሩ የአስተዳደር ወሰኖች የየራሳቸው መልክዓምድራዊ ወሰኖች ያሏቸው ቢኾኑም በዕለተለት ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶቻቸው የተነሳ ወሰን ተሻጋሪ እሴቶችን አዳብረዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በተለይ አዋሳኝ ሥፍራዎች ላይ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች የየራሳቸው ቋንቋ፣ ባህል፣ ወግ ቢኖራቸውም ወሰን ተሻግረው መግባባት፣ መሸጥና መለወጥ በጋብቻም መተሳሰር ብቻ ሳይኾን በነዚህ ግንኙነቶች ውስጥ አለመግባባት ወይም ግጭት ሲፈጠርም ከሁለቱም ባህል በተቀዱ ብልሃቶችና ተቋማት አማካኝነት ችግሮቻቸውን ይፈታሉ፡፡በአዋሳኝ አከባቢዎች ያሉ ማንነቶችም በአብዛኛው ውሕድ (hybrid) ማንነቶች ሲኾኑ የባህላዊ ማንነትም ኾነ የአስተዳደር ወሰን ተሻግረው ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን ማድረግ አይቸገሩም፡፡ ይህ የኾነው ውሕድ ማንነቶች ሥሪታቸው በልዩነት እና በተመሳስሎ (vector of similarity and of difference) የተዋቀረ በመኾኑ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ‹ሀ› እና ‹ለ› በአንድ በኩል የየራሳቸው ‹ልዩ› ማንነቶች፣ በሌላ በኩል ‹ተመሳስሎዎች› ያሏቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን ‹ሀ›ን ከ ‹ለ› ልዩ የሚደርገው ጉዳይ የት ጀምሮ የት እንደሚያበቃ ወይም ተመሳስሏቸውም የቱጋ ጀምሮ የቱጋ እንደሚቋረጥ ለመናገር አስቸጋሪ በኾነ (fludity) ሁኔታ ውስጥ እየዳበረ የሚሄድ ማንነት ነው፡፡ እንግዲህ በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች ወሰን በሚጋሩ ማኅበረሰቦች ማንነቶች፣ ወጎች፣ ሥርዓቶች፣ ተቋማት መካከልም ይህንኑ ውሕደት እናስተውላለን፡፡ ከዚህ አንጻር በተለይ በነዚህ ዓይነት አከባቢዎች ያሉ ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማት ወይም ሥርዓቶች የዚህ ውሕድ ማንነት ነጸብራቆች በመኾናቸው የእከሌ ሳይኾኑ የእከሌ ናቸው ብሎ መናገር አስቸጋሪ መኾኑን ልብ ይሏል፡፡ ይልቁንም ተቋማቱና ሥርዓቶቹ የሚሰጡት ፋይዳ ላይ ማተኮሩ የተሻለ ይኾናል፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡት ማኅበረ-ባህላዊ ተቋማትና ሥርዓቶችምአንድም ማኅበረሰብን ከማኅበረሰብ፣ ጎሳን ከጎሳ በማዛመድ ወይምበማገናኘት የአብሮነት ሚና የሚጫወቱ፤ አንድም ድንበር የሚዋሰኑ ሕዝቦች በጋራ የመሠረቷቸው የግጭት መፍቻና የእርቀሰላም ማውረጃ ተቋማት፣ ልማዶችና ሥርዓቶች ናቸው፡፡

# ሚቹ

ሚቹ ቀጥተኛ ትርጉሙ ጓደኝነት ወይም ባልንጀርነት ማለት ሲኾን በመተከል አካባቢ የሚኖሩ የተለያዩ ብሔሮች ግጭቶችን የሚፈቱበትና እርቀ ሰላም የሚያወርዱበት ተቋም ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በዚህ የወንድማማችነት ወይም የወዳጅነት ተቋም አማካኝነት የጉሙዝ ማኅበረሰብ ከተቀሩት የክልሉ ሕዝቦች ጋር ግጭቶች የሚፈቱበትና የመቻቻል ባህል እንዲዳብር ያስቻለ ተቋም ነው (Tsega 2002)፡፡ በክልሉ በሚኖሩ ብሔሮች መካከል ግጭቶችና ከበድ ያሉ አለመግባባቶች ሲከሰቱ ለችግሩ መፍትሄ ፍለጋ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ከመሄድ ይልቅ በሚቹ እልባት መፈለግ የተለመደ ነው (Fekadu 1998, 4 በTsega 2002 እንደተጠቀሰው)። እንደ ባይሳ በሴ እና ለሜሳ ደሜ (2008) አገላለጽ «በአከባቢው ግድያ የተበራከተ እና ገዳዮችም በማኅበረሰቡ ዘንድ አድናቆት ይቸራቸው ነበር፡፡ ነገር ግን የኦሮሞዎችን መስፈር ተከትሎ በጉሙዝ እና በደገኞቹ (ሺናሻ፣ ኦሮሞ፣ አገውና አማራ) መካከል ባህላዊና ማኅበራዊ መቻቻልንና እርቅን ማስፈን የቻለ ሚቹ የተሰኘ ወዳጅነት ሊፈጠር ችሏል፡፡» በማለት በአከባቢው ሚቹ በብሔሮች መካከል የድልድይነት ሚና መጫወት የቻለ የማኅበራዊ ሀብት ተቋም መኾኑን ያስረዳሉ፡፡ሚቹ በተለያዩ ብሔሮች መካከል የሚፈጠሩ ግጭችንና አለመግባባቶችን የመፍቻ ተቋም እንደመኾኑ «ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ግጭቶችን፣ ሥነልቡናዊ ብሎም ከቆዳ ቀለም ጋር በተያያዙ ፍረጃዎች ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶች ጭምር የሚፈቱበት ተቋም» (Tsega 2002) መኾኑ የተቋሙን ሁለገባዊ ግልጋሎት የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ተቋም የባህልና የብሔር ‹ድንበር› በመሻገር ግጭትን መፍታቱ በይነ-ባህላዊ ተግባቦትን በማሳለጥ የብዝኃ ባህል ባለቤት ለኾኑ አከባቢዎች ሰላምና አብሮነትን በማጠናከር በኩል እንደ ሞዴል ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡

# ሆርማ ሆዳ

ሆርማ ሆዳ በመተከል አከባቢ የኦሮሞ ማኅበረሰብ ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር ከሚተሳሰርባቸው ባህላዊ ሥርዓቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ በሆርማ ሆዳ ባህላዊ ሥርዓት ሊጣመሩ ከወደዱት ቤተሰቦች መካከል የአንደኛው ቤተሰብ ልጅ በማርና ወተት የተቀባ የሌላኛውን ቤተሰብ ሴት ጡት አለያም የወንድ አውራ ጣት በመጥባት የሚከወን ሲኾን በሁለቱ ሰዎች (በልጁና በሴቷ ወይም በልጁና በወንዱ መካከል) የወላጅ እና ልጅ ዓይነት ግንኙነት መመሥረት የሚያስችል በመኾኑ በሁለቱ ቤተሰቦች ብሎም በብሔሮች መካከል ጠንካራ ማኅበረ-ባህላዊ ትስስር መፍጠር የሚያስችል እሴት ነው (Tsega 2002)፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የዚህ ሥርዓት ማኅበረ-ባህላዊ ፋይዳ በሁለት ቤተሰቦች ብሎም ብሔሮች መካከል ትስስርን መፍጠር ማስቻሉ ለሰላማዊ ሕይወትና አብሮነት ፋይዳው ግልጽ ነው፡፡ ከማኅበራዊ ፋይዳው ባሻገር ደግሞ እንደ ብላከርስት (1996 በTsega 2002 እንደተጠቀሰው) አገላለጽ ይህ ሥርዓት በአንድ በኩል በሚፈጠረው ግንኙነት ሳቢያ በልጁና በአዲሱ ‹ወላጅ› መካከል የመንከባከብን መንፈስ የሚጠራ ቢኾንም ግንኙነቱን በቅርበት ስንመለከተው የተፈጠረው ግንኙነት ወይም ትስስር በልጁና በአዲሱ ቤተሰቡ መካከል ኢኮኖሚያዊ ትስስር ጭምር ያመጣል ምክንያቱም ልጁ ለነርሱ በሚሰጠው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ልክ ከነርሱም የሚጠብቀው ቁሳዊ ድጋፍ መኖሩ ስለማይቀር፡፡

# ገረብ

በአፋርና በዋጅራት ሕዝቦች መካከል ግጭትና አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችል የጋራ ተቋም ሲኾን ከሁለቱም ሕዝቦች የተውጣጡና «አቦ

ገረብ» (በቀጥታ ትርጉሙ የወንዝ አባት) የተሰኙ አባቶች የሚመሩት ባህላዊ ተቋም ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ወንድማማች ሕዝቦች በአስተዳደራዊ ወሰን የተለያዩ ይኹኑ እንጂ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት የሚገናኙ ናቸው፡፡ የአፋርና የዋጅራት ሕዝቦች በገበያ እና በጋራ የግጦሽና የውሃ ሥፍራዎች የሚጠቀሙ፣ እንዲሁም በጋብቻ ጭምር የተሳሰሩ ሕዝቦች እንደመኾናቸው (Abraha 2012) በባህል፣ በቋንቋ እና ማኅበራዊ ሕይወት የሚጋሩ ብሎም በዚህ «ገረብ» በተሰኘው የጋራ ባህላዊ ተቋም ግጭቶችን የሚፈቱ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ይኸው ሥርዓት በዋጅራትና በራያ አዘቦ፣ በዋጅራት እና በተቀረው ትግራይ መካከልም ግጭቶች፣ ግድያ፣ የከብት ስርቆት፣ ዝርፊያ፣ ደፈራ፣ ጠለፋ፣ የግጦሽ መሬት መጣስ፣ ወዘተ ሲከሰቱ ግጭቶች የሚፈቱበት ተቋም ነው (Assefa 2016፣ ገጽ 154)፡፡የዚህ ተቋም ዓይነተኛ መገለጫና ትልቁ ፋይዳው ችግሮችን፣ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን ድንበር-ዘለል በኾነ ባህላዊ ሥርዓት መፍታት መቻሉ ነው፡፡ በዚህ ሥርዓት ከሦስት እስከ 12 የሚደርሱ አቦ ገረቦች ማኅበረ-ህላዊ ጥበቦቻቸውን ተጠቅመው ችግሩን በሚገባ ከመረመሩ በኋላ ለተበዳይ ፍትህን፣ በዳይን ደግሞ ተገቢውን ቅጣት የሚሰጡ ብቻ ሳይኾን በሁለቱ ወገኖች መካከል የጋብቻ ትስስርን (Assefa 2016፣ ገጽ 156) የመሰሉ መፍትሄዎችን በመጠቆም ከግጭቱ በኋላ ቂም እና በቀል እንዳይቀጥል ዘላቂ እርቅ እንዲሰፍን ያደርጋሉ፡፡

## ጉርቲ

ጉርቲ በሶማሌ ማኅበረሰብ ዘንድ የተለያዩ ጎሳዎች መካከል ያለን ግንኙነት የሚያሳልጥ፣ ግጭቶችን በመፍታት በኩል ብቻ ሳይኾን በአከባቢው ያለን እንደ ግጦሽ ሳርና ውሃ የመሳሰሉ ሀብቶችን በማስተዳደር በኩል ሁነኛ ሚና የሚጫወት የሽማግሌዎች ተቋም ነው፡፡ የጉርቲ ሽማግሌዎች በጎሳዎች መካከል ያለን ግንኙነት የሚያስተዳድሩበት ሔር (Xeer) የተሰኘ ተቋማዊ ማዕቀፍ አላቸው፡፡

## ጉዲፈቻ

ጉዲፈቻ በኦሮሞ ህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ አስደናቂ ከሆኑት የገዳ ስርዓትና ሌሎች አስፈላጊ ተቋማት መካከል የሚመደብ ማህበራዊ የውህደት ተቋም ነዉ፡፡ ይህ ስርዓት ሞጋሳ ከሚባለው ሌላው የኦሮሞ ማኅበረ-ባህላዊ ኃብት ጋርም አንፃራዊ ቅርርብ አለዉ፡፡ በጉዲፈቻ ስርዓት ልጆች የሌሏቸው መሃን የሆኑ ባልና ሚስቶች ወይም ቤተሰቦች ከሌላ ቤተሰብ የመጡ ልጆቻቸውን ጉዲፈቻ (ማደጎ) የሚያድርጉበት ነው፡፡ በዚህ ስርዓት መሠረት የጉዲፈቻ ልጆች (ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች) በህጋዊ ጋብቻ ከሚገኙ ወንዶች ወይም ሴቶች ልጆች ጋር እኩል መብቶችና ግዴታዎች ይኖራቸዋል፡፡ጉዲፈቻ ልጅ ለሌላቸው ጥንዶች ማህበራዊ ዘርን በመስጠት ልጅ እንዲኖራቸውና ወራሾች እንዲያገኙ በማስቻልከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዋናነት የጉዲፈቻ ባህል በእርጅና ወይም በጤንነት ጊዜ የንብረት ወራሽ እና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ እንዲያገኝ የቤተሰብ መስመርን ማረጋገጥ ነው፡፡ የጉዲፈቻ አሠራር የሕፃናት ችግርን ለማስወገድ በሰፊው ልንጠቀምበት የምንችለው ሃገር-በቀል የጣልቃገብነት ስትራቴጂ ነው፡፡ እንደ አገርበቀል የሕፃናት እንክብካቤ በአጠቃላይ ሕፃናትን እና ወላጅ አልባ ሕፃናትን እንዲሁም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናትን በማዋሃድ እና በማስተዋወቅ የማስተሳሰር ስራ ይሰራል፡፡ ዘላቂ ሰላም ግንባታን መሰረት ያደረገ የተገፉ ህብረተሰብ ክፍሎችን መሰረት ያደረገ ስርዓት በመሆኑ ሰላምን ሲያፀና ቆይቷል፡፡

## ሞጋሳ

የኦሮሞ ህዝብ ከኅብረተሰቡ ጋር እንዲዋሃዱ ለግለሰቦች እና ለጎሳዎች አዲስ ስም የሚሰጥ ልዩ የማኅበራዊ ጉድኝት ዓይነት ነዉ፡፡ በኦሮሞ ማኅበረሰብ ውስጥ ሞጋሳ ልዩ እና ጉልህ የሆነ ባህላዊ ባህሪ ያለዉ ስርዓት ሲሆን የሌላው (ኦሮሞ ያልሆነ) ማኅበረሰብ ተወላጅ ወደ ኦሮሞ የሚቀላቀልበት ማህበራዊ ዘዴ ነው፡፡ ሞጋሳ በኦሮሞ ጎሳዎች መካከልም ሊከናወን ይችላል፡፡ ይህ ከአንድ ጎሳ ወደ ሌላው ጎሳ ለመሰየም የግለሰቦችን ጥያቄ በራሱ ብስለት ውስጥ የገባበት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት አሠራሩ በተለይ ሞጋሳ በማኅበረሰብ ደረጃ መጠኑ የቀነሰ ቢሆንም በግለሰቦች ደረጃ አሠራሩ እየቀጠለ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የገዳ ውህደት ገጽታ ከሰው ልጆች ግንኙነት ሥነምግባራዊ ልኬቶች ባሻገር ለተፈጥሮ እና ለፈጣሪ የመግባባት እና የአብሮነት ስልቶች ይዘልቃል፡፡ ሞጋሳ ለሰላም ግንባታ አስፈላጊ ሁኔታ ለሆኑ ማህበራዊ ትስስር እና ምንጮች ማፈላለግ አስፈላጊ ባህላዊ ስትራቴጂ ነው፡፡

## ጎንዶሮ

የጉጂ ኦሮሞና የጌዴኦ ህዝቦችተጎራባቾች ሲሆኑ በባህል፣ በቋንቋ፣ በኢኮኖሚ፣ በመልክዓ-ምድር፣ በማህበራዊና በታሪክ እጅግ የጠበቀ ትስስር አላቸዉ። ሁለቱ ህዝቦች ታላቅና ታናሽ ወንድማማቾች እንደሆኑ በአፈ ታሪካቸዉ ይነገራል። የየራሳቸው የገዳ ሥርዓት ያላቸዉ ሲሆን የጌዴኦ የገዳ መሪዎች ምርቃት የሚወስዱት ከጉጂ መንፈሳዊመሪ (አባ ቃሉ) ነው። ይህ የቅርብ ትስስር ሰላማዊ ግንኙነት እንዲኖራቸዉና በግጭት አፈታትና በሰላም ግንባታ ረገድ የጋራ ባህላዊ እሴት እንዲኖራቸዉ አድርጓል። ጎንዶሮ በጉጂ ኦሮሞና በጌዴኦ ብሄረሰብ ዘንድ የሚታወቅ የግጭት አፈታትና የእርቅ ባህላዊ ስርዓት ሲሆን በማህበረሰቡ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት አለዉ። ይህ ስርዓት በሁለቱም ማህበረሰቦች ቋንቋ በተመሳሳይ ጎንዶሮ ተብሎ ይታወቃል። ጥሬ ትርጉሙም “ዳግም ሊፈጠር የማይገባ ድርጊት ወይም ሁኔታ” እንደማለት ነዉ። ጎንዶሮ በግለሰብም በማኅበረሰብ መካከል የተፈጠረ ግጭት ወይም ጥፋት እንደጸጸት ተወስዶ በእርቅ መፍትሄ የሚሰጥበት ባህላዊ ስርዓት ነዉ። ይህ የግጭት መፍቻ ስርዓተ-እርቅ በዋናነት ከዘር (ከትዉልድ) እርግማን የማንጻት የጋራ እምነት ላይ የተመሰረተ ነዉ።የማህበረሰቡ መሪዎች እንደሚገልጹት በድሮ ጊዜ በጉጂ

ኦሮሞና በጌዴኦ ህዝቦች መካከል በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ግድያና ግጭት እንዳይኖር ቃለመሀላ (Oath) ተግባብተዉ ነበር። በአጋጣሚም ከተፈጠረ እርቀ-ሰላም የሚያደርጉበት ጎንዶሮ ተብሎ የሚጠራ ስነስርዓት እንደመሰረቱ የሁለቱ ህዝቦች አዛዉንቶች ይናገራሉ። ይህ ቃልኪዳን ከትዉልድ ወደትዉልድ ሲተላለፍ የመጣ ሲሆን ቃልኪዳኑን የሰበረ ሰዉ ወይም አካል ይረገማል። ጎንዶሮ ከትዉልድ እርግማን (ancestral curse) የሚነጻበትና ዳግም ጥፋት እንዳይፈጸም ቃልኪዳን የሚታደስበት ባህላዊ የእርቅ ስርዓት ነዉ። ይህን ባህላዊ የእርቅ ስርዓት በዋናነት የሚመራዉ የጉጂ አባቃሉ ሲሆኑ ከሁለቱ ማህበረሰብ የገዳ አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች በስርዓቱ ክንዉኖች ዉስጥ ሰፊ ተሳትፎ አላቸዉ።

ጎንዶሮ ዛሬም በጉጂ ኦሮሞና በጌዴኦ ህዝቦች መካከል በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ ግጭት ለመፍታት የሚጠቀሙበት ስርዓት ነዉ። እአአ በ1998 ዓም በጉጂ ኦሮሞና በጌዴኦ ህዝቦች መካከል ደምአፋሳሽ ግጭት ተፈጥሮ ነበር። የፌዴራል መንግስት መጀመሪያ በሀይል ጣልቃ ገብቶ ለማቆም ሞክሮ አልተሳካም ነበር። በመቀጠልም በመንግስት የተደረጉ የሰላም ኮንፈረንሶች መፍትሔ አላመጡም ነበር። በመጨረሻም መንግስት ሁለቱ ህዝቦች በባህላቸዉ እንዲፈቱ ዕድል ሰጠ። በዚሁ መሰረት ሁለቱ ህዝቦች ግጭቱን በጎንዶሮ ስርዓት ፈተዉ ለረጅም ዓመታት አንጻራዊ ሰላም ለመፍጠር ችለዋል። ይህም በሰላም ግንባታና በግጭት አፈታት ሂደት ዉስጥ ማህበረሰቡ በራሱ ባህላዊ ስርዓት መሰረት መሳተፍ ከላይ ከሚመጣ አሰራር የተሻለ ዉጤታማ መሆኑን ያሳያል፡፡

# አዳያኢቢያ

በምስራቅ ኢትዮጵያ የሚገኙ የኦሮሞ ሕዝቦች በማንኛውም ጊዜ የሚከሰቱትን ግለሰባዊም ሆነ ቡድናዊ ችግሮችን (ግጭቶችን) ለመፍታት ወይም መፍትሔ ለመሻት የራሳቸው የሆነ የሽምግልና ሥርዓት አላቸው፡፡ ይህ የሽምግልና ሥርዓት «አዳ ያኢ ቢያ»ወይም «ሴረ ኦሮሞን ኢቲቡልቱ» በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ሥርዓት በምስራቅ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ሌሎችሕዝቦች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ከሱማሌ የሽምግልና ሥርዓት «ሔር»ጋር አቻ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ በአዳ ያኢ ቢያም እንደ ገዳ ሥርዓት ሁሉ ዕድሜ ለማሕበራዊ ክንዋኔና ለሃላፊነት መለኪያ ያገለግላል፡፡ በአሁኑ ወቅት በምስራቅ ሐረርጌ ኦሮሞ ህዝብ መካከል የሚከሰቱ ማሕበራዊ ችግሮችን (ግጭቶችን) ለመፍታትይህ«አዳ ያኢ ቢያ» በመባል የሚታወቀው ባህላዊ የሕግ ሥርዓት ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡ በአካባቢው የከርክር ሥርዓት የሚል አቻ ትርጉም ያለው ይህ ባህላዊ ሥርዓት በማናቸውም ቤተሰቦች ወይም ጎሳዎች መካከል የሚፈጠሩ ማሕበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በአካባቢው የዕድሜ ባለፀጎች (ሽማግሌዎች) የችግሩ ምንጭ ተፈልጎ ችግሩ ሳይባባስ መፍትሔ ይፈለግለታል፡፡የችግር አፈታት ሥርዓቱም እንደሚከተለው ነው፡፡ በከርክሩ ወቅት ሽማግሌዎቹ ባህላዊ ፍርድ ከመስጠታቸው በፊት ከሁለቱ ወገኖች የተነሱ ፍሬ ሃሳቦች ወይም ጭብጦች በመስማት ቃላቸውን ይቀበላሉ፡፡ ቀጥሎም ከሁለቱ ወገኖች የሚነሱትን ቃልና እንደሁኔታው የምስክሮችን ቃል በመቀበልና አጠቃላይ ሁኔታውን በጥሞና ተመልክተውና መርምረው ፍትሃዊ የሆነ የፍርድ ውሳኔ ያስተላልፋሉ፡፡ በዚህ ባህላዊ የፍርድ ሂደት ላይ የሽማግሌዎቹ ጥልቅ የትኩረት አቅጣጫ ውሳኔ የመስጠት ጉዳይ ሳይሆን የውሳኔውን ፍትሃዊነት ማረጋገጥና ከአድሎና ከወገናዊነት ነፃ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ባህላዊ የሽምግልና ሥርዓት የገዳ ሥርዓት ቅሪት በመሆኑ የጋራ አመራርና የጋራ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡

# ሔር

ሶማሌዎች በርካታ ጎሣዎችና ንዑስ-ጎሳዎች ያላቸው ህዝቦች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ የዳሮድ ጎሣ (Darood) በኢትዮጵያ ከሶማሌ ብሄራዊ ክልል ከዘጠኙ ዞኖች በ7ቱ ይኖራሉ፡፡ ከነዚህ 7 ዞኖች ደግሞ ኦጋዴን (Ogaden) በስድስት ዞኖች የሚኖር በመሆኑ ሔር-ዳሮድ ሁሉም ኦጋዴኖች የሚጠቀሙበት ህግ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በተመሣሣይ ኢሳ ከሶማሌ ዋና ዋና ጎሳዎች መካከል አንዱ ሲሆን ጎሳው ማንኛውም የሚፈጠሩ ማሕበራዊ ችግሮችን የሚፈታበት ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት አለው፡፡ በዳሮድም ይሁን በኢሳ ጎሣዎችና ንዑሳን-ጎሳዎች መካከል የሚነሳ ፀብና አለመግባባት ሔር (xeer) ተብሎ በሚጠራ ባህላዊ ሕግ (አስተዳደር) መሠረት ችግሩ ተወግዶ መፍትሔ ያገኛል፡፡ ሞሃመድና ዘውዴ የሔርን አመጣጥ እንደሚከተለው አብራርተውታል፡፡ "ሶማሌዎች የራሳቸውን ጎጆዎች/ቤቶች በመስራት ይታወቃሉ፡፡ ቤቶቹ በርካታ ቁሳቁሶችን የያዙ ሲሆን እነዚህም ዙሪያቸውን ሄር በሚባል ረጅም ገመድ ይታሰራሉ፡፡ በተመሣሣይም ሶማሌዎች የሚጋጩ ፍላጎቶች ያላቸውን አባላት አንድ ላይ የሚያስተሳስሩት ሄር በሚባለው ህግ ወይም ስምምነቶች ነው" (2008:185-199)፡፡ ይህ ባህላዊ ህግ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን የተከተለና በማንኛውም ጊዜ መፍትሔ የሚያስገኝ ጠንካራ ህግ ነው፡፡ ህጉ ሚዛናዊ ከመሆኑ የተነሳ ሁሉም ንዑሳን ጎሳዎች ይዳኙበታል፤ ችግራቸውንም ይፈቱበታል፡፡ በዚህ መሠረት ማንኛውም አጥንቴ ተሰብሯል፤ ስጋዬ ተቆርጧል ያለ ሰው በሔር (xeer) መዳኘቱ ግድ ይሆናል፡፡ በሕጉ መሠረት በቀል የተከለከለ ሲሆን ሁለቱ የተጣሉ ወገኖች (ቡድኖች) በሕጉ መዳኘትና የሕጉን የፍርድ ውሳኔ መጠበቅ ግድ ይላቸዋል፡፡ ሕጉ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

# ሔር ዲብሌ (Xeer Dhiblee)

ይህ ህግ አራተኛው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሲሆን በዚህ መሠረት የሚፈታው ግጭት በማንኛውም ወቅት ከጎሳው ውጭ በድንበርና በሌሎች ምክንያት ከሌሎች ጎሳዎች ጋር የሚፈጠር ግጭትን ለመቀልበስ የተደነገገ የቆየ ባህላዊ ሕግ ነው፡፡ የብሔረሰቡ ሽማግሌዎች እንደሚናገሩት ሔር (xeer) ለእነሱ ከምንም በላይ ነው፡፡ የዚህ ባህላዊ ሕግ እያንዳንዱን አንቀጾች ያከብሩታል፤ ማኅበራዊ ችግሮቻቸውንም ይፈቱበታል፡፡ ሔር ዲሞክራሲን መሠረት ያደረገ ስለሆነ ፍትሐዊነቱ የጎላ ነው፡፡ በኢሳ ማሕበረሰብ መካከል የተነሳ ችግር (ግጭት) ከሔር (xeer) ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡ ሕጉ ሁሉን አቀፍ በመሆኑ ማንኛውም የማሕበረሰቡን ወግና ባህል የለቀቀ ነገር በሙሉ ይስተካከልበታል ሥርዓትም እንዲይዝ

ይደረግበታል፡፡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ለዘመናዊው የፍርድ ሂደት የራሱ የሆነ የጎላ ሚና እያበረከተ ነው፡፡ «ከገንዴ» ባህላዊ ፖርላማ እስከ መንደር ሽማግሌዎች ያሉ እርቅ አስፈጻሚ አካላት ሰላምን ለማውረድ የተጣለባቸውን ኃላፊነት ይወጣሉ፡፡ የዳኝነት ሥርዓቱ የሚካሄደው በዛፍ ሥርና በወንዞች አካባቢ ሲሆን ይህም ችሎቱን ለመከታተል በርካታ ሰዎች እንዲገኙ ያስችላቸዋል፡፡

# ማሮ

ማሮ በአፋር ክልል የአፋር ብሔረሰብግጭት ለመፍታት በዛፍ ጥላ ስር የተሰየመ የሽማግሌዎች ጉባኤ ወይም ሸንጎ ማለት ነው። በአፋር ባህል ግጭት የሚፈቱና እርቅ የሚያወርዱ ዳኞች ማካባን የባላሉ። ማካባኖች እጅግ ከተከበሩት ከጎሳ መሪዎች (ከዶ) ተብሎ ከሚጠሩት ጋር አብሮ በመሥራት የሕዝቡን ሰላም ያስጠብቃሉ። በመድአ ህግ መሰረት ማካባኖች (ዳኞች) ማንኛውንም ግጭት (የቤተሰብ፣ነፍስ ግድያና የጎሳ) ግጭቶችን የፈታሉ፣እንደዚሁም እርቅ ያወርዳሉ። በአንድ ጎሳ ውስጥ ግጭት ቢቀሰቀስ ገለልተኛ ማካባኖች ከሌላኛው ጎሳ ተመርጠው ያስታርቃሉ።የማሮ ተቋምና መድአ የፍትህ ሥርዓት የድንበር ዘለል ግጭቶችን ማለትም ከትግራይ፣ከኢሳና ከኦሮሞ ብሄረሰቦች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶችን ጭምር ይፈታሉ፤ እርቀ-ሰላም ያወርዳሉ። እነዚህ የፍትህ ስርአቶችና ተቋሞች በሁሉም ዓይነት የኅብረተሰብ ችግሮች ላይ መፍትሄ የሚሰጡ ዳኞች፣ ሱልጣኖች፣ የጎሳ መሪዎች በሚሰጡት ውሳኔ መሰረት ፀጥታ ማስከበርና ወንጀል መከላከል ያስችላሉ፡፡ ሥርዓቶቹ በአንጻራዊነት ያልተሸረሸሩ፣ አሁንም ድረስ በሥራ ላይ ያሉ፣ ሕዝቡ የሚያምንባቸው እና የሚገለገልባቸው ባህላዊ ተቋማት ናቸዉ።

# ፊእይማ

ፊእይማ የአፋሮች ማኅበራዊ ሀብት ሲሆን ዋና አገልግሎቱ እስላም ወይም የአፋር ብሔረሰብ አባል ያልሆነን ሰው የአፋር ጎሳ አባል አድርገው የሚያቀላቅሉበት ተቋም ነው። ፊእይማ እኩል እድሜ ክልል ዉስጥ ያሉ ግለሰቦች የሚፈጥሩት የወዳጅነት ጥምረት እንደመኾኑዓላማው በደስታና በሃዘን ግዜ ለመረዳዳትና እንዲሁም ጉልበት ለማሰባሰብ ይረዳል። አንድ የአፋር ብሔረሰብ አባል ያልሆነ ሰው ወደ አፋር መጥቶ ስርዓቱን በመፈጸም በፊእይማ ሥርዓት ባህሉንና ወጉን በሚገባ የሚከተል ከሆነ፣ሃይማኖቱና ብሔሩ ምንም ይሁን ምን ወዲያውኑ የአፋር ብሔር ወይም የአፋር ዜጋ ይሆናል። ግለሰቡ ባል/ሚስት እንዲያገባ ይፈቀድለታል፤መሬት፣ ከብት ወይም ግመልም ይሰጠዋል/ይሰጣታል።

# ከታይዛ

ኬታይዛ (ketayza) በአፋር ክልል የሃይማኖት እንዲሁምየጎሳ ወይምየብሄር ወሰንን ተሻግሮ ጓደኝነትና ወዳጅነትየሚፈጠርበት ተቋም ነው። ከታይዛ ለመሆን አንድ ሰው ከቅርብ ጓደኛው ጋር በቤተሰቡ እና በሽማግሌዎች ፊት መሐላ ማድረግ እና ስጦታ መለዋወጥ ይጠበቅበታል። አንዴ ይህ ሥርዓት ከተፈፀመ ሁለቱ ኬታይዛ (ጓደኛሞች) ይሆናሉ። እስከ ሞት ድረስ ለዘላለም የተጣመሩ ናቸው። በደስታ ወይም በሀዘን ጊዜ፣ በሀብት ወይም በድህነት ወቅት አንዱ ለሌላው ይቆማል፡፡ ይህ ድንቅ ባህል በአፋር ማኅበረሰብ ውስጥ እና በአፋሮች እና በአፋሮች መካከል፤ በተለያዩ የጎሳ አባላት መካከል ያለውን ማኅበራዊ ውህደት እና አብሮ መኖርን የሚያጸና ነው። ይህ እና መሰል ማኅበራዊ ሀብቶች ምንም እንኳን በከተሞች አከባቢ እየተሸረሸሩና በሌሎች ዘመናዊ ማኅበራዊ ትስስሮች እና እሴቶች እየተተኩ የሄዱቢሆንም አሁንም በገጠሩ ማኅበረሰብ ዘንድ እጅግ የሚወደዱና አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ሥርዓቶች ናቸው።

# ሉዋ

ሉዋ (Luwa) ሉዋ የሲዳማ ብሔር አባላት የሆኑ ወንዶች ከየጐሳቸው ተወጣጥተውና በትውልድ ዑደት ተደራጅተው በማኅበረሰቡ ማኅበራዊ፣አስተዳደራዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ የላቀ ተሳትፎ ለማድረግ የሚሰበሰቡት ባህላዊ ተቋም ነው፡፡ የሉዋ ሥርዓት በአባልነት የሚያቅፏቸው ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ጥንካሬን፣አርአያነትን፣ አስታራቂነትን፣ለሰላም መቆምን ወዘተ ያሉ በጐ ምግባሮችን እንዲቀስሙ ከማድረጉ ባሻገር በጎሳዎች መካከል መቀራረብንና ለአንድ ዓላማ መቆምን የሚያበረታታ ተቋም ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሕዝቡን ከውጪ ጠላት ወረራ የመከላከል ተግባር በሉዋ አባላት ይመራል፡፡ በአንድ የሉዋ ስልጣን ዘመን በማኅበረሰቡ መካከል ሰላም፣ ደህንነትና አንድነት እንዲሰፍን የሉዋ ሥርዓት መሪዎች በተለይም ጋዳና (Gadaana) ከፍተኛ ኃላፊነት ይጣልበታል፡፡ሉዋ በተለያዩ ማኅበራዊ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ማኅበረሰቡን የሚወክሉ አዋቂ ሰዎች የሚወጡበት ተቋም በመሆኑ ግጭት ለመከላከል፣ ለሰላም ግንባታና ለአብሮነት ያለዉ ሚና ከፍተኛ ነው። ሆኖም የሉዋ ሥርዓት በአሁኑ ሰዓት እየተዳከመና እየቀዘቀዘ የመጣ ስርዓት መኾኑ ይነገራል።

# ገትሴራ

ገት ሴራ በደ/ብ/ብ/ሕ በሀዲያ ዞን የሀዲያ ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር ሥርዓት ነው። ገትሴራ በሀዲያ ግጭትን ለመከላከል ጥቅም ላይ ከሚውሉ ሥርዓቶች መካከል አንዱ ሲሆን ሥርዓቱ መሀላ (ህድሮ/Hidiro) ይጠቀማል፡፡ ህድሮ በግጭት ወቅት የነፍስ ማጥፋት ወይም የንብረት ውድመት

ቢከሰት በቂም በቀል ስሜት ግጭቱ እየተስፋፋ እንዳይሄድና ተጨማሪ የህይወት መጥፋትና የንብረት ውድመት እንዳይከሰት በተጋጩ ቡድኖች እውነተኛ መከባበርና መተባበር እንዲሰፍን ተመሳሳይ ግጭት እንደገና እንዳይከሰት በማድረግ በጣም ውጤታማ የሆነ የሀዲያ ሴራ አካል ነው፡፡ በሀዲያ ጎሣዎች መካከል ህድሮ (ማሃላውን) በፈጸሙ ጎሣዎች መካከል ጋብቻ የሚከለክል ዝምድናን በመፍጠር የሚጠናቀቅ በመኾኑ የጎሳ ወሰንን ተሻግሮ አንድን ጎሳ ከሌላ ጎሳ የስጋ ዝምድና ያህል በጠበቀ ቁርኝት የሚያስተሳስር ስርዓት ነው፡፡ በመሀላ (ህድሮ) ወቅት ተቆጥሮ የተገባውን ቃል የማክበር ግዴታ ሴራው ተቆጥሮ ያስቀምጣል፡፡ የተደበቁና የሰፉ የግጭት ሚስጥሮችን በማውጣት የሚተነትኑ የወቅቱን ግጭት ድብቅ መነሻ የሚያሣዩ ትልቅ የአዕምሮና የአስተሳሰብ ብቃት ያላቸው ግለሰቦች ህራጋኖ ይባላሉ፡፡ እነዚህ ግለሰቦች እስካሁን በሕብረተሰቡ ዘንድ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ሴራው በግጭት የሚከሰት ሞት አይነቶችን በመዳኘትና በማስታረቅ በህብረተሰቡ መካከል የተፈጠረዉን አለመግባባቶች ቀድሞ ወደነበረበት ሠላማዊ ግንኙነት ይመልሳል፡፡ የሀገርሽ ማግሌዎች (ዳኞች) የሚያስቀምጡት ግዴታ ተፈፃሚነቱ ሠላምን ለማስቀጠል ሁነኛ መፍትሔ በመሆኑ ዘላቂ ሰላም ግንባታ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

# ግዲቾ ዎጋርሲ ጎንዶሮ

ግዲቾ ዎጋርሲ በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል በጋሞ ዞን የግዲቾ ብሔረሰብ ግጭት መፍቻ ሥርዓት ነው። የግዲቾ ማኅበረሰብ ከሌላ ብሔረሰብ ጋር ግጭት ሲገጥመው ጎንዶሮ በሚባል ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት መሠረት በባህላዊ መሪዎች አማካኝነት ይፈታል፡፡ ስርዓቱም የተጋጩ ወገኖች ዳግም እንዳይፈላለጉ የሚያደርግ ነው፡፡ የእርቅ አፈፃጸም ሂደቱም ከብት ከታረደ በኋላ በፈርሱ በመታጠብ የሚፈጸም ሲኾን በጊዲቾ ቋንቋ ኤንጌ (Enge) ተብሎ ይጠራል፡፡ ትርጉሙም ሁለት ወገኖች መካከል አለመስማማት መከሰት ማለት ሲሆን፣ በዳይ ተጸጽቶ ነገሩን ለሽማግሌዎች ካመለከተ በኋላ፣ ሽማግሌዎች ጉዳዩን በሚገባ በማጤን ግጭቱ ከሁለቱ ቤተሰቦችና ጎሳዎች አልፎ እየሰፋ ወደ ሕዝብ እንዳይገባ ጭምር የሚታመንበት ስለሆነ በፍጥነት በመመርመር እልባት የሚሰጡበት ሥርዓት ነው፡፡ ይህ እንደ አዲስ በማንሰራራት ላይ እንደሚገኝ የሚነገርለት ሀብት በጎሳ ውስጥና ከጎሳ ውጪ ያሉ ግንኙነቶችን የሚያጠናክር፣ መተሳሰብንና ይቅር ባይነትን የሚያጎለብት ከሰላም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ተቋም ነው፡፡

# ዴሃ እና ቅማዩማ (ቅሙማ)

ይህ እሴት በደ/ብ/ብ/ሕ ደራሼ ልዩ ወረዳ በዴራሼ፣ ሞስዬ፣ ማሾሌና ኩሱሜ (የአራቱም ብሔረሰቦች ተመሳሳይ ነዉ) ባህላዊ ሀብት ነው። ሞራ የሚባል በአራቱም ብሔረሰቦች (ደራሼ፣ ሞስዬ፣ ኩሱሜ እና ማሾሌ) ዘንድ ለወንዶችና ለሽማግሌዎች መዝናኛና ለቅማዩማ (ቅሙማ)/ ለሽምግልና እንዲሁም ለባህላዊ የዳኝነት ሥርአት የሚጠቀሙበት ባህላዊ ተቋም ነዉ፡፡ በዚህ በሞራላ ይቅሙማ/ሽምግልና ሥርአት ይካሄድበታል፡፡ ግጭት ሲከሰትም ሆነ አዲስ ዝምድናን ለመፍጠር ቅሙማ እጅግ በጣም ሰፊ ሚና አለዉ፡፡ ቅሙማ በአራቱም ብሔረሰቦች ተመሳሳይነት ያለዉ የግጭት አፈታት እና የሰላም ግንባታ ተቋም ሲሆን በማህበረሰቡ መካከል ግጭት ሲፈጠር ግጭቱ ተባብሶ እንዳይሰፋ በዳዩ ገና በማለዳ ቅማያ/ሽማግሌ ወደ ተበዳዩ ቤት ይልክና በዴሃ ድርድር ተስማምተዉ አብረዉ ቤት ያፈራዉን መብልና መጠጥ በመቃመስ ይለያያሉ፡፡ አሠራሩ እና የጊዜዉ ጉዳይ ልክ እንደተፈጠረዉ ግጭት መጠን የሚለያይ ቢሆንም ሂደቱና ሥርአቱ ግን ቅማዩማ (ቅሙማ) በመባል ይታወቃል። ቅማዩማ አዲስ ዝምድናን ለመፍጠር፣ የቀድሞዉን ሠላም እና አንድነትን ወደነበረበት ለመመለስ፣ ከሌላ ብሔር ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት እና ሌሎች ያለመግባባቶችን በዘላቂነት የሚፈታ መሆኑ ለሰላምና አብሮነት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። በተለይ በሥርዓቱ ተሣታፊዎች የንጉስ ዝርያ ያላቸዉ፣ የአባቶች መንፈስ ያደረባቸዉ ታዋቂ ሽማግሌዎች፣ የጎሣ መሪዎችና በሕብረተሰቡ ዘንድ እጅግ የተከበሩ ሰዎች መሆናቸዉ ግጭት ለመፍታትና እርቅ ለማውረድ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። በመጨረሻዉ የዕርቅ ቀን የጋራ ግብዣና የእርድ/የደም ማፍሰስ ሥርአቶች መኖራቸዉ ሥርዓቱን ተቀባይነት የጎላ ያደርገዋል። ይህ ባህላዊ ሀብት ለዘላቂ ሠላም ግንባታ ጉልህ ሚና አለዉ፡፡ ቅማዩማ እስከዛሬ ድረስ በሕዝቡ ዘንድ ወደር የሌሌዉ የግጭት አፈታት ስርአት ሲሆን ለዚህ ሥርአት የማይገዛ ማንኛውም ሰዉ በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ለቁም ነገር የማይበቃ እምነት እንደማይጣልበትና እንደማይረባ ሰዉ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በቅሙማ የተፈታ ግጭት ወይንም አለመግባባት አብሮ በመብላትና በመጠጣት የሚጠናቀቅበት ዋና አላማ የቀድሞውን አብሮነትና ወዳጅነት ሙሉ ለሙሉ የሚመልስ ስለሆነ ነው፡፡ እንደ ሥርአቱ አብረዉ የሚቃመሱት እህል እንኳ ቢጠፋ፣ ጨዉ ተወስዶ ሁሉም በአንድነት ቀምሰዉ ይለያያሉ፡፡ ከዚያን ሰዓት ጀምሮ ጥለኞች የነበሩት የቀድሞ ወዳጅነታቸዉ ይቀጥላል፡፡

# ቦኮ

ቦኮ በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል በአማሮ ልዩ ወረዳ የኮሬ ብሔረሰብ እሴት ነው።ይህ ባህላዊ ስርዓት የራሱ መሪዎች ያሉት የአንድ ባህላዊ አስተዳደር ወሰን ክልሉ ቀደምት ሰፋሪ ጎሳ ወኪሎች ተቋም ነዉ፡፡ እነኚህ የጎሳ መሪዎች የሚያቋቋሙት ከእያንዳንዱ ነባር ጎሳ መሪዎች ተዉጣጥተዉ የሚመሰርቱት በመሆኑ የሁሉንም ጎሳ አባላት ማሕበረሰብ በአንድነት በመያዝ አምባ (amba) የሚመሰረት ነው፡፡ ቦኩ ከሁሉም የጎሣ መሪ ሽማግሌዎች የተዉጣጣ ሕብረት በመሆኑ፤ በአማሮም ሆነ ኮሬ ሰፍሮ በሚገኝባቸው አዋሳኝ አካባቢዎች የኮሬ ብሔረሰብ አባላት ታላቅ ፍርሀትና አክብሮት ይሰጠዋል፡፡ ሕዝቡ ሁሉ ለአባቶች የሚሰጡት ክብር እጅግ ከፍ ያለ ስለሆነ የቦኮ ዳኝነትም ሆነ የእርቅ ሥነ-ስርአት በአካባቢዉ ከፍተኛ ተጽእኖ አለዉ፡፡ የግጭት አፈታት ሂደቱ ከቀላል እጅግ ዉስብስብ እስከሆነዉ ደረጃ ድረስ መፍትሔን ሊያመጣ የሚችል ከመሆኑም ባሻገር በሕብረተሰቡ ዘንድ ለጎሳ መሪ አባቶች የሚሰጠዉ ከበሬታ ለነገሮች መቃለል ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ በቤተሰብ ችሎት (ዛዋኦኄ) የንዑስ ጎሳ ችሎት (ካራኦኄ)፣ የአደባባይ/የማህበረሰብ ችሎት (ለዶኦኄ) እና ቤተ-መንግሥት ችሎት (ካሦኦኄ) በአራት አገር በቀል ችሎት ደረጃዎች ላይ በየችሎቱ ዕዝ ላይ ለማስቻል የባህል ሕጉ ሥልጣን ለሚሰጣቸው ወኪል የጎሳ መሪዎች ከተቀመጡ ኃላፊነቶች አኳያ በ24ቱም የግዛተ-ንጉሡ ግዛቶች በሶስት ክልሎችና 24 ቦኮዎች ዳኝነት፣ እርቅና ሠላም ሲወርድ ክፉን መርገም እና መልካሙን የመመረቅ ሥልጣን የቦኳደ ሥራ ነው!

ቦኮ እስካሁን ተቀባይነትና ተአማኒነት ያለዉ የግጭት አፈታት ሥርአት ነዉ፡፡ ብዙ ባህላዊ ሥርዓቶች በተለያዩ ሃይማኖታዊና ፓለቲካዊ አካሄዶች ሳቢያ ሲዳከሙና የቀድሞ ኃላፊነታቸውን ለመስጠት አቅም ሲያጡ አማችነትና ቦኳደኝነት ከዚያ ቤተሰብ በሥጋ አንጋፋ ሆኖ ምድሪቱን በማየቱ እጅግ በጣም የሚፈራና የሚከበር ባህላዊ እሴት ነው። ሕዝብን ከሕዝብ፣ ግለሰቦችንም እርስበርሳቸዉ እንዲቀባበሉ ስለሚያደርጋቸዉ ከቅድም-አያቶች ወደአባቶች የተላለፈዉ ይህ ባህላዊ ሥርአት ውጤታማነቱን ተከትሎ ሌሎች ጠቃሚ ባህሎች በሕዝቡ መቀባበልና አንድነት እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ ይህም ቀጣዩ ትውልድ ከአባቶች እንዲማር ይረዳዋል፡፡ አሁን በአካባቢው ያሉ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን ያለ ቂምና በቀል መፍትሔ የመስጠት ብቃቱን በመገንዘብ በማኅበረሰቡ ዘንድ መልሶ እያንሰራሩ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ አንዱ ነው።

በአካባቢዉ ቀጣይነት ያላቸዉ ስምምነቶች እና የሚመለከቱ ህጎችን፤ ሰብአዊ መብቶችን ጨምሮ የሁሉም ሰው መብቶች ተጠብቀዉ ሕዝቡ በሠላም እንዲኖር ዋስትና ይሰጣል፡፡ 109ኙም የኮሬ ጎሳዎች በአራት ነገዶች (ኮረሴ፣ካናኤ፣ማና እና ዎጋጨ ነገዶች) የሚታቀፈበትን ሁሉን አካታች ተቋም በመሆኑ ለሠላም ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። ሁሉ አቃፊ ብቻ ሳይሆን አንዱ ነገድ በጉባኤው ካልተሳተፈ የኮሬ ፍርድ የማይፀና ወይም ዋጋ የማይኖረው ስለሚሆን የአንደኛው ወገን ባለመኖር ምልዓቱ እንዳልተሟላ ስለሚወሰድ እንከን የሌለውን ፍርድ በመስጠት ለሁሉም የሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን ለተፈጥሮ፣ ለእንሰሳት፣ ደን፣ ለሚታየውና ለማይታየው ሁሉ በፈጣሪ ፊት ቅን ፍርድ ይሰጣል፤ ለፍትህና ለእውነት ይቆማል ተብሎ በጽኑ የሚታመንበት ተቋም ነው።

# ምርቃትና ጸሎት

በተለያዩ የሀገራችን ማኅበረሰቦችና አካባቢዎች ዘንድ ስያሜው ይለያይ እንጂ በእርቅና ሽምግልና ብሎም በልዩ፣ ልዩ ማኅበረ-ባህላዊ ሕይወት አካል የኾኑ ሥርዓቶችና ከበራዎች አካል የኾነ፣ የሥራዎችና ክንዋኔዎችን ማስጀመሪያና ማስፈጸሚያ ኹና እያገለገለ የሚገኝ ታላቅ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ሀብት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ስሙብዙ ነገር ግን ድንበር-ዘለል ሀብት በተለያዩ የሀገራችን ቋንቋዎችና ባህሎች ዘንድ ደግሞ የየራሱ ባህሪያትና ቀለማት ያሉት ሲኾን ለአብነት ያህል  በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ያለውን ምርቃትና ጸሎት እንመለከት፤

ኤባ እና ካዳና (Eebaa fi Kadhanaa)፤በኦሮሞ አመለካከትና እምነት ሰላም የሰዉ ልጆች እርስ በርሳቸዉና ከተፈጥሮ እንዲሁም ከፈጣሪና ከህዋዉ ጋር ተያያዥነት ያለዉ በመሆኑ ከሁሉ ነገር የበለጠ ትኩረት የሚሰጠዉ የስብዕና እሴት ነዉ። የሰላም ጽንሰሀሳብ በሁሉም ቦታ የሚነሳ ሲሆን፣ በዘፈን፣ በምርቃትና በጸሎት፣ በባህላዊና እምነታዊ ስነስርዓቶች፣ በንግግር፣ በተረት፣ በአስተዳደራዊና ህጋዊ/ፍትሃዊ ተግባራት ዉስጥ ሁሉ ለሰላም ያላቸዉን ቁርጠኝነት፣ ፍላጎትና ምኞት ይገልጻሉ። ምንም እንኳን ሁሉም የሰዉ ልጆች ሰላምን የሚፈልጉ/የሚሹ ቢሆንም ኦሮሞ ለሰላም የሚሰጠው ቦታ ልዩ/ከፍተኛ ነው፡፡ ሰላም የሞራል ግዴታ ከመሆኑም ባሻገር በህይወትና በነጻነት የመኖር ዋስትና በመሆኑ ሠላምን ከምንም በላይ ይወዳል፤ ያከብራ፡፡ የኦሮሞ አባቶች ፈጣሪ /ዋቃም/ ሰላምን እንደሚወድ፤ ሰላም ከሌለ ሞትና ሰቆቃ እንደሚነግስ እንዲሁም ለሰዎች ልጆች ዉልደት፣ ዕድገትና ልማት መሰረት በመሆኑ ሰላም ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል ይላሉ። በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ማናቸዉም ስብሰባዎች፣ ጋብቻ፣ የእርቅ ስነስርዓቶች፣ ሀይማኖታዊና ባህላዊ በዓላት፣ የገዳ ጉባኤዎች፣ ወዘተ በምርቃት ተጀምረዉ በምርቃት ይፈጸማሉ። በእነዚህ ምርቃቶች ዉስጥ የሰላም ጉዳይ ዋነኛ/ቁልፍ እሴት ነዉ። በምርቃትና በጸሎቱ ዉስጥ ለቤተሰብ፣ ለጎረቤት፣ ለጎሳ፣ ለአገር፣ ለዓለም ለሰዉ ልጆች ሁሉ የሰላም ምርቃት፣ ምስጋናና ጸሎት ይደረጋል። ሰዉ ከራሱ ጋርና ከፈጣሪዉ ጋር ሰላም እንዲኖረዉ ይመርቃል፣ ይለምናል። የሰዉ ልጅ እርስበርሱ ብቻ ሳይሆን ከተፈጥሮም ጋር ትስስር ስላለዉ ከሰዉ ልጆች አልፎ የተፈጥሮ አካባቢ፤ ለወንዞች፣ ለደን፣ ለአየር፣ ለዝናብ፣ ህይወት ለሌላቸዉ ነገሮች ጭምር ሰላም እንዲኖራቸዉ ይለምናል፣ ይጸልያል። ሁሉም ነገሮች ተያያዥነት ስላላቸዉ የአንዱ ሰላም ማጣት በሌሎች ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል ብሎ ያምናል። ስለዚህ ለኦሮሞ ህዝብ ሰላም ሁለንተናዊ ገጽታ ያለውና ምድራዊ ጸጋ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ እሴትም ነዉ። ኤባ (ምርቃት) ከትውልድ ወደትዉልድ ሲተላለፍ የመጣ ለሰላም ግንባታ መንፈሳዊ መሰረት የሚፈጥር ባህላዊ እሴት ነዉ። ምርቃት የሚካሄደዉ በአባ ገዳዎችና በአገር ሽማግሌዎች ነዉ። መራቂዎች የሚጠቀሙት ቃላትና ብሂሎች በዘመናት ተሞክሮ ዉስጥ በጥንቃቄ የተቀመሩና የተመረጡ ናቸዉ። ከተራ ንግግር የተለየ እንደየአካባቢዉ የታወቀ የድምጽ አወጣጥ፣ ለዛና ቅላጼ አላቸዉ። ይህ ማህበራዊ እሴት ዛሬም በመላዉ የኦሮሞ ህዝብ ዘንድ የሚተገበርና ማህበራዊ ቅቡልነት ያለው ነው። ኦሮሞ ሰላምን ለማስፈን ከህግና አስተዳደራዊ ተግባራት ጎንለጎን ስለሰላም አስፈላጊነት ህብረተሰቡን ማንቃትና ግንዛቤ መፍጠር ወሳኝ ነዉ ብሎ ያምናል። ምርቃትና ጸሎት በማህበረሰቡ ዉስጥ የሰላም መንፈስ እንዲኖርና ህዝቡ ሁልጊዜ ስለሰላም እንዲያስብ በማድረግ ለሰላም ግንባታ መንፈሳዊና የሞራል ስብዕና መሰረት መፍጠር ያስችላሉ። ስለዚህ ማናቸዉም ማኅበራዊ ክንዉኖች (ባህላዊ፣ ሀይማኖታዊና ህዝባዊ) ዛሬም በኤባ ተጀምረዉ በኤባ ይጠናቀቃሉ።

ዋቢዎች


Abraha Tesfay. 2012. "Dynamics of Inter-Communal Conflict in North-East Ethiopia: The Case of Wejerat People and Their Neighboring Afar." In: Anthology of Peace and Security Research, Vol 3. Insititute of Peace and Security Studies& Friedrich Ebert Stiftung, Addis Ababa.Pp. 1-70.

Areba Abdella & Birhanu Amenew (2008) "Custormary Dispute Resolution Institutions in Oromia Region: The Case of Jaarsa Biyyaa", In Grassroots Justice in Ethiopia, eds., Allula Pankhrust and Ge tachew Assefa, Centre français des études éthiopienness, Addis Ababa.

Asmerom Legese (1973) Gadaa: Three Approaches to the Study of African Society. The Free Press, New York.

Assefa Fiseha. 2016. "Traditional Mechanisms of Conflict Resolution: Case Study from Tigray." In: Tarekegn Adebo & Hannah Tsadik (eds.) Making Peace in Ethiopia: Nine Cases of Traditional Mechanisms of Conflict Resolution. Addis Ababa: Life & Peace Institute and Peace and Development Center. Pp. 136-168.

Bayisa Besie and Lemessa Demie 2008. "Customary Dispute Resolution in Beni-Shangul Gumuz with Emphasis on Shinasha Society" In: Alula Pankhurst and Getachew Assefa (eds.), Grass-roots Jus tice in Ethiopia: The Contribution of Customary Dispute Resolutio. Centre français des études éthiopiennes. Pp. 123-131. https://books.openedition.org/cfee/508.

Biruk Haile & Jira Mekonnen (2008) "Custormary Dispute Resolution in Harar", In Grassroots Justice in Ethiopia, eds., Allula Pankhrust and Getachew Assefa, Centre français des études éthiopienness, Addis Ababa.

Dessalegn Chemeda, et al (2007) "Indigenous Systems of Confllict Resolution in Oromia, Ethiopia" In Community-based Water Law and Water Resource Management Reform in Developing Countries, eds, B. van Koppen, M. Giordano and J. Butterworth, CAB International.

Flemmen, Anne Britt & Zenebe, Mulumebet. 2016. Religious Mahbar in Ethiopia: Ritual Eelements, Dynamics and Chalenges.Journal of Religion in Africa, 46: 3-31.

IIRR (2009) Culture at Crossroads: Ethiopian Women in Peace-building. International Institute of Rural Reconstruction, Nairobi.

Mohammed Mealin Seid & Zewdie Jotte (2008) "Customary Dispute Resolution in the Somali State of Ethiopia: An Overview" In Grassroots Justice in Ethiopia, eds., Allula Pankhrust and Getachew Assefa, Centre français des études éthiopienness, Addis Ababa.

Shimelis Gizaw and Taddese Gessese. 2008. "Customary Dispute Resolution in Tigray Region:
CaseStudies from Three Districts" In: Alula Pankhurst and Getachew Assefa (eds.), Grass-roots Justice in Ethiopia: The Contribution of Customary Dispute Resolutio. Centre français des études éthiopiennes. Pp. 217-236. https://books.openedition.org/cfee/508

Tilahun Bejtual and Moges Demissie. 2021. "The Case of Amhara Regional State", In Associational Life and Social Capital in Ethiopia, eds., Goitom Gebreleul, Hateta Policy Research, Addis Ababa, Ethiopia.

Tsega Endalew. 2002. Conflict resolution through cultural tolerance: an analysis of the Michu Institution in Metekkel Region, Ethiopia.Addis Ababa: Organization for Social Science Research in Eastern and Southern Africa

የሰላም ሚኒስቴር
MINISTRY OF PEACE

Sweden
Sverige

Life & Peace
INSTITUTE